# እ ሳ ት

# ወ ይ

# አ በ ባ

ከጸጋዬ ገብረ መድኅን

ሥነ ግጥም

ይህን መጽሐፍ በማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መሣርያ ለማስተላለፍ፣
ለማስቀመጥ፣ በፎቶ ኮፒ ወይም በሌላ መንገድ ለማባዛት፣
ለማሳተምም ሆነ ለመተርጎም፣
የባለመብቱን ፍቃድ እንዲጠየቅ ሕግ ያስገድዳል።

© 1999 የጸገመ ቤተሰብ

በመጀመርያ በ1986 ዓ.ም. በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

ለሁለተኛ ጊዜ በ1999 ዓ.ም. በግራፊክስ ማተሚያ ቤት ታተመ

All rights reserved. No pert of this book mey be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any meens, electronic, mechanical, photocopying or otherwise, without the prior permission of the publisher.

© 2007 TGM femily

First printed in 1973 by Berhanene Selem
Printing Press, Addis Ababa, Ethiopia

Cover Design: Assegid Gessesse

ISBN 978-0-9793201-0-1

Library of Congress Control Number 2007900859

www.tsegeye.org
info@tsegeye.org

ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን የበርካታ ተወዳጅ ሥነ-ግጥሞች ደራሲ ሆኖ ሳለ፣ "እሳት ወይ አበባ" ብሎ ከሰየመው ከዚህ መድብል ውሰጥ ከሚገኙት በቀር ሌሎች ግጥሞቹ በመፅሐፍ መልክ ለህትመት አልበቁም። "እሳት ወይ አበባ" ለመጨረሻ ጊዜ በ1966 ታትሞ ከወጣ በኋላ ባለፉት ዓመታት ጭራሹን ከገበያ ላይ በመጥፋቱ የጸጋዬን ሥራዎች ህያውነት የሚመኙ አድናቂዎች ቅሬታቸውን ገልጸዋል።

ጸጋዬ ገብረ መድኅን ባለፈባቸው የህይወት ውጣውረድ ከአዕምሮውና ከኅሊናው ሰርፀው፣ በርቱዕ ብዕሩ ነጥረውና ተውበው የተወለዱ በርካታ የአማርኛና የእንግሊዝኛ ግጥሞችና ትያትሮች አሉ። በህይወት ሳለ የጠነሰሰነውን፣ እነኚህን ሥራዎቹን አሰባስቦ የማሳተሙን ተግባር፣ ለ"እሳት ወይ አበባ" ቅድሚያ በመሰጠት ጀምረናል።

ቤተሰቦቹ

ጥር 1999

ለንርዐዮ ኢሳይያስ መታሰቢያ ይሁን።

# መግቢያ

## ሀ/ ሥነ - ግጥምን እንደባለድንጋጌ ታሪክ

አንድ ምእመን የሃይማኖቱን ድንጋጌ ከማተቱ ይልቅ በቀጥታ እግዚአብሔርን በእምነት ማገልገሉ እንደሚበልጥበት ሁሉ፤ ባለቅኔም የሥነ-ግጥሞችን የአደራደር ሥርዓትና ድንጋጌ (ፎርም) ከማተቱ ይልቅ ቅኔውን ተቀኝቶ ደርሶ ፍሬ ሃሳቡን (ኮንቴንት) ማበርከቱ ይበልጥበታል ቢያሰኝም፥ የግል አስተያየቱን ፈለግ ከጽሑፉ አነፃፀሮ በቅርብ መመልከቱ ደሞ የብዕሩን ዝንባሌ ፈር ሊያሳይ ይችላል ይባላልና፤ ሊሆን እንደሚገባው ሁሉ ሌሎች ያላቸውን ግምት ለሌሎቹ ትቼ፤ እነሆ እኔም ራሴ ስለሥነ-ግጥም አነሳስ ያለኝን አንዳንድ ሃሳብ አስቀድሜ ባጭሩ ልንገር። "ሥነ-ግጥም ከመሠረቱ ያው የገዛ ሕይወቱ ሂስ ነው፤" ይላልና ባለቅኔው ማቲው አርኖልድ።

በጠቅላላው የአለካኩ ሥርዓት እንደየምጣኔው ወይም እንደየስንኙ ቁጥር ልክ ዓይነተኛ ድንጋጌ ያደረገለትን ሃሳብ-ወለድ (ልብ-ወለድ) ሥነ-ጽሑፍ ብቻ ሳይሆን፤ ግጥሙ ቤት የሚመታ ወይም የማይመታን እንቆቅልሽ ሆነ ምሳሌና ተረት፤ እንዲሁም፤ በቃለ-ውበቱና በቃለ-ኃይሉ፤ ወይም በድቀቱ ሥምረት ለአእምሮ ለልቦናና ለስሜት የሚጥምን ባለስልትና ባለድንጋጌ የቋንቋ አደራደር ሁሉ፥ ሥነ-ግጥም (ፖኤትሪ) ይሉታል።

መቸም ኪነ-ጥበብ ሁሉ ንጥር የሕይወት አካል ነውና፤ ሥርወ-መነሾው በቀጥታ ከሰው የመሠረተ-ፍጥረት ደመ-ሕይወት ጋር ተጣምሮ ስለሚጠቃቀስ፤ የሥነ-ግጥምንም የመጀመሪያ ጥሬ መልክ፤ ያው እንደዳንስ፣ እንደሥዕልና እንደሙዚቃ ሁሉ፤ አስቀድሞ በሕፃናት ጨዋታ ሲጨፈር፣ ሲጫር፣ ሲተረብና ሲዘፈን እናየዋለን። ቀጥሎም፤ ኪነ-ጥበብ ከቀዋሚ የኑሮና የመደበኛ ሥራ ክፍሎችም ጋር እያደር ተደጋግፎ ሲጠና፣ እንደየሥራው አንፃር፣ ለምሳሌ፣ በሠርግና በቀብር ሥርዓት አማካዩን የዘፈንና

የሙሾ ግጥሞች፣ በግብርና የግብርና ጠቀስ ግጥምና ዜማዎችን፣ በሃይማኖትና በአምልኮ ባዕድም የኒሁኑ ጠቀስ ባሰመዝሙር፣ ባለጸሎት፣ ባለወረብ፣ ባለወሸባና ባለዝየራ ግጥሞችን ተከባክቦ ይታያል። እዚህ ላይ ዋና ዋናው ተግባር ያው ሠርጉ፣ ቀብሩ፣ ግብርናው፣ ሃይማኖቱና እምልኮ-ባዕዱ ሲሆን፤ ለየጉዳዩ የተደረደረው ግጥም ግን ለየተግባሩ ተቀጥላነትንና ማሞካሸትን ይዞ ኖረ ማለት ነው። ይሁንና፤ የሌላ ሥራ-ክፍል ጥገኛና ተቀጥላ ከመሆን አልፎ፤ ራሱን ችሎ፤ እንደገበሬው ግብርናና እንደ ካህኑ ሃይማኖት መደበኛ የኑሮ ተግባርነት ሲሉ፤ የሥነ-ግጥምም ተሰጥዎ ለሞያተኛው ዋናውና መደበኛው ተግባር ከመሆኑም ሌላ፤ ያው እንደየቋንቋው የአደራደር ሥርዓተ-ድንጋጌ የግል ዘይቤና የይዞታ ምዳቤ (ዲስፕሊን)፤ በጣዕሙ፣ በድቀቱ፣ በቃለ-ውበቱና በቃለ-ኃይሉ ወዘተ.፣ ለዕለቱ ብቻ ሳይሆን ለየጊዜው ሽግግርና ለየተከታታዩ ትውልድ ተቀባይነቱን አሰፈትኖ ሲደረጅ፥ ሥነ-ግጥሙ ዘላቂ ኪነት (እርት ወይም ጥበብ) ወደመሰኘቱ ቀዋሚ ደረጃ ደረሰ ማለት ነው።

በዚሁም ይዞታና ድርድር፤ በአንድ አንፃር፤ እንደሌሎቹ ኪነ-ጥበባት ሁሉ፤ ሥነ-ግጥምም ከየትውልድ ሀገሩና ከየወራሹ ወገን የሥልጣኔ ዘመናት፣ ግሥጋሤና ውድቀት ጋር ታድሞ፤ አብሮ ገሥግሦና አብቦ አብሮ ወድቆና ተደምስሶ፤ ወይም ደጋግሞ ታድሶ ወይም ከነአካቴው ጠፍቶ ቢቀርም እንኳ፤ አብዛኛውን ጊዜ የመሠረተ-ቋንቋውን ቅድመ-ድንጋጌና የራሱንም ስያሜ ይዞ እናገኘዋለን። ይሁንና፤ በሌላው አንፃር ደግሞ የግብርና ተግባር ሆነ የልቅሶ ሥነ-ሥርዓት፤ የእማካይ ሥነ-ግጥሞቹን የመሠረት ድርድርና ድንጋጌ ለይቶ ሳያስቀር፥ ያው እንደልጆቹ የየትውልድ ጨዋታና ተረብ፤ እንደጦርነት እስትራተጂና እንደወይዛዝርት የአለባበስ ወግ፤ አንዳንዴ ስያሜውን ከነድንጋጌው፥ አንዳንዴ ስያሜውን ይዞ ድንጋጌውን ብቻ፥ ወይም ድንጋጌውን ይዞ ስያሜውን ብቻ እንደየዘመኑ የሥልጣኔ ዕድገትና ውድቀት፤ የምርጫ-ውርስና የገድፎ-ውርስ (ሚዩቴሽን ኤንድ ሲሌክሽን) ጣዕምና ዝንባሌ፤ ለውጧል-ይለውጣልም፣ ተለውጧል-ይለወጣልም። ምክንያቱም፤ በጠቅላላው የኪነ ጥበብ ወይም በተለይ የሥነ-ግጥም ታሪክ፤ የየቋንቋውን የአደራደር መሠረተ-ድንጋጌ በየዘመኑ አበላልጦ ማርቀቁ ብቻ ሳይሆን፤ በየዘመኑ ከሚወራረሱት የሌሎች ቋንቋዎች ልዩ ልዩ የአደራደር መሠረተ ድንጋጌዎች ጋር፤ ከይዞታቸው ምዳቤና (ዲሲፕሊን)፤ ከየምዳቤአቸውም ቴክኒክ ጋር ያደረገው የዕድገትና የውድቀት ታሪክ ጭምር ነው መባሉ፤ "የኪነ-ጥበብ መልእክት ከሰው ተፈጥሮ ወደሰው" ሆኖ፥ ተቀባይነቱም እንደየዘመኑና እንደየትውልዱ የጣዕምና የዝንባሌ ዳኝነት የሚመጠን ስለሆነ ነው።

ለምሳሌ፤ ከክርስቶስ ልደት በፊት በሰባተኛው ዓመተ-ዓለም ግድም በሆሜር የተቀመረው የኢልያድና የኦዲሴ 'ኤፒክ' የተሰኘው የግሪክ ሥነ-ግጥም፤ አስቀድሞ የነማንን ሥርዓተ-አምልኮ-ባዕድ ተንተርሶ የተገኘ የዜማ ምዳቤ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፤ ከነማን ቋንቋ የግጥም ሥርዓተ ድንጋጌ ጋር ተወራርሶና ተዳቅሎ የወጣ መሆኑንም ጭምር፤ የቅድመ እሌናውያን ባለታሪኮች ሲነግሩን፤ መጀመሪያ ወዲያው የሆሜር 'ኢልያድና ኦዲሴ' ተቀምሮ ሠላሳ ዓመት ሳይሞላው ባለቅኔዎቹ ካሊኑስና ቲይራታኡስ የኤፒኪን "ሄክሳሚተር" (የኤፒክን የስንኝ ስልት ቁጥር) ድንጋጌ ለውጠው ወይም ቀላቅለው "ኤሌጂ" ባሰኙት የስንኝ ስልት ቁጥር ድንጋጌ ሲቀኙ፤ ደራሲው ሴፕሲስ ደግሞ ሰማንያ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ፤ ከሥርዓተ-አምልኮ ባዕዱ የዜማ መሠረተ-ምዳቤ ውስጥ የተካፋዮቹን እደራደር ቀይሶ ጻፈ። ዛሬማ፤ እንኳንና የነሆሜር 'ኤፒክ' የቀድሞው የአደራደር ሥርዓተ ድንጋጌ እያሌ ጊዜ መሰዋወጥ ቀርቶ፤ 'የምዕራባውያን ሥልጣኔ ምንጭ' ተብሎ የሚታመንበት ቋንቋው ጭምር እያደር ተትቶና በትውልድ ሀገሩ እንኳ ሳይቀር እጅግ እስከሚያሳስት ድረስ ቢቀያየርም፤ የኤፒክ ሄክሳሚተር የመሠረት ስንኝ ስልት ቁጥርና ስያሜው ግን እንደነበረ ለማታውቁ ያህል ያው አሁንም ይታወቃል። በቀድሞው ደረጃ ከቶውኑ አይሁን እንጂ በጥንታዊ የግሪክ ቋንቋ ጥናት ትውስታ ጊዜም ይሠራበታል። ነገር ግን፤ ከእያሌ ቋንቋዎችና ከየሥነ-ግጥማቸው የመሠረት ሥርዓተ ድንጋጌዎች ጋር ለእያሌ ምዕተ-ዓመታት ተወራርሷልና በቅድመ-ፍጥረት አባትነቱ ዛሬም ተከብሮ ይኖራል። በጊዜው እንደሱ ገናና ከነበሩትና፤ ለምሳሌም ክርስቶስ ራሱ መጀመሪያ ሰብኮበት ነበር ተብሎ እንደሚታመነው እንደአረማይክ ቋንቋ ግን ከነሥነ-ግጥም ድንጋጌው ጋር ጨርሶ አልጠፋም። የሁለቱ የታሪክ

ልዩነት ይኸ ነው። እንደዚሁም፣ የአክሱማውያን ሥልጣኔ ተነስቶ በደመቀበት ከክርስቶስ ልደት በፊት በስድስተኛውና በይበልጥም እስከ አራተኛው ዓመተ-ዓለም ግድም እንደነአስታርና አልሙጋህ ያሉትን የሳባውያን ሥርዓተ-አምልኮ-ባዕድምና የኩሽንም ወገን ሥርዓተ-አምልኮ-ባዕድ ተንተርሶ፣ ከኒህና ከሌሎችም ቋንቋዎች ተወራርሶና ተዳቅሎ የተፈጠረው የግዕዝ ቋንቋ፣ በየጊዜው ቀምሮት ከነበረው ከሥነ-ግጥሞቹ የመሠረት ሥርዓተ-ድንጋጌዎች ውስጥ፥ ዛሬም በኒሁ ቋንቋዎች በተለይም በኩሽና በሳባዊው የአረብ የስንኝ ስልት ድንጋጌዎች ውስጥ መገኛታቸው፥ የታሪክ እንጂ የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ አይደለም። ለምሳሌ፣ ከግዕዝ ቅኔ በተለይ የወል ቤት የምንለው ባለስድስት የስንኝ ስልት ቁጥር ድርድር፣ በአረብኛ፣ በሱዳኑም የዳንጉላዊስና የመሀስ የጥንት ኑባውያን፣ በሶማሌ፣ በኩሽ፣ በኢትዮጵያም የኩሽና የሴም ዲቃላ ቋንቋዎች የግጥም ድንጋጌ ውስጥ ልክ እንደግዕዙ ድርድር በጥራት ተሳክቶ እናገኘዋለን። 'አስታር' የተሰኘችይቱም የሳባውያኑ ሴቴ ጣዖት በሥርዓተ-አምልኮ-ባዕድ ዜማና በጽላትም ቅርፅ፣ ከጥንተ-ምሥርዋ ሴቴ-አምላክ ከ 'አስቶር' ጋር ስለምትመሳሰል የሚቶሎጂ ምሁራን መወራረሳቸውን ይነግራሉ።

እንግዲህ በጠቅላላው፣ በአንድ ፊት፣ እንደኪነ-ጥበባት ሁሉ፣ የሥነ-ግጥምን ድንጋጌ ይኸኛው ዓይነት ብቻ መሆን አለበት፣ ወይም ደግሞ ከዚህኛው የቋንቋ መሠረተ ድንጋጌ በተወረሰው ዓይነት ብቻ መመራት አለብን ብሎ መወሰን፣ ያው ከተወሰነ አእምሮ የሚወጣ ድፍረት ነው ብንልም፣ በሌላው መልክ ደግሞ፣ ቁጥሩን (ሚተሩን ወይም 'ምቱን') የተመደበ የስንኝ ስልትና ቤት ባልደነገገው የቃላት መረን አሂዶ እነሆ ሥነ-ግጥም ማለቱም የባሰ ጸያፍ ማስኘቱ ሳይሳነን፣ ከላይ እንደጠቀስኩት እንደምእመኑ ሃይማኖት ዓይነት፣ ባለቅኔም የሥነ-ግጥሞችን የአደራደር ድንጋጌ ከማተቱ ይልቅ ቅኔውን (ተቀኝቶ) ደርሶ ማበርከቱ ይበልጥበት ይመስለኛል። ስለሆነም ለምሳሌ፣ አብዛኛዎቹ የኔ ግጥሞች ካሁን ቀደም ብዙዎች ጠይቀውኝ እንደመለስኩት ሁሉ፥ እስካሁን ከተለመዱት ከዋነኞቹ ከግዕዝ እስከ አማርኛ ውርስ የሥነ-ግጥም ድንጋጌዎች ውስጥ፣ ማለት፣ የወል ቤት እንዳልነው ባለስድስት (ሁለት ባለሦስት ሐረግ)፣ እንደ ቡሄ በሉ ቤት ባለ ሁለት ወይም እንደ በገና እንጉርጉሮ



ቤት ባለ ስድስት (ሦስት ባለ ሁለት ሐረግ) እንደሆያሆዬና እንደ ሰንጎ መገን ቤት ባለ አምስት ወይም ከኒህ ከዋነኞቹ ተቀላቅለው በመዋለድ እንደተባዙት፣ ለምሳሌ እንደመዲና (ከነስሙ 'መዲና')፣ ከሰንጎ መገንና ከቡሄ በሉ ቤት አፈራርቆ እንደሚደረደረውና እንደሚደረደሩት ብዙዎች የኩሽና የሳባውያን አረብ ዲቃላ ቋንቋዎች የዘልማድ ሕግጋት ሳይሆን፣ የቁጥሩን መለያ መሠረት አንድ ራሱን በስምንት የስንኝ ስልት ድንጋጌ ላይ ስለምደረድረው ብቻ ነው። ይኸም በአደራደርና በሠረዝ ነጥብ ተከፍሎ ይታያል። አንዳንድ መምህራን የዚህን ድንጋጌ ዘይቤ (ስታይል) ስም ስላላገኙለትና እኔም ስላልሰየምኩት "የጸጋዬ ቤት" ይሉታል። ስምንቱን ስንኝ አብዛኛውን ጊዜ ቀዋሚ አድርጌ የምከፍለው በአራት-በአራት ሐረግ ነው። አልፎ አልፎ ግን፣ በሦስት-በሁለትና-በሦስት፣ በሁለት-በሦስትና-በሦስት፣ በሦስት-በሦስትና-በሁለት በማፈራረቅ እየከፈልኩ መደርደሩም የለውጥንና ያለማሰልቸትን ጠባይ ማስገኘቱን ስለገመትኩ ነው። በተጨማሪም፣ በተለመደው የወል ግጥም ድርድር የጻፍኳቸው ጥቂት ግጥሞች አሉ። ከዚህ ሌላ፣ ስለቦረንና ስለ ከፋ በጻፍኳቸውና በተረጎምኳቸው ሦስት ግጥሞች ብቻ፣ ያንኑ 'የኦሮሞን ኩሽ' "ማክማክሳና ሙርቲ" የተሰኘ፣ በሁለት-በአራትና-በአራት፣ በሁለትና-በአምስት፣ በሁለት-በሦስትና-በሁለት ሐረግ የሚፈራረቅ የስንኝ ስልት ድንጋጌ ተከትዬ፣ ለምሳሌ ያህል ያሰፈርኳቸው አሉ። እንግዲህ ቀድሞ እንደተባለውም፣ ባለቅኔም የዚያው የባህሉን ቅርስ አቆይቶና መግቦ ላወረሰው የገዛ ሕዝቡ የስሜት ጫፍ ተቀጥላ እንደመሆኑ፣ ከጆሮና ከአንደበቱ ድምፅ የቀመረውን ስልት በራሱ ዘይቤ እያስተጋባ ቅርሱን በልዩ የምስክርነት መለዮ ሲያድስና ሲገልጽ ቆይቶ-ኖሮ ማለፉ የተለመደ ሲሆን፣ ሁለት ባልቴቶችም ሦስተኛይቱ ቤት በቀመሱት የቡና ጣዕምና ቃና ባይስማሙ፣ የሕይወት አካል ኪነ-ጥበብም እንደ ሕይወት ቅመም ቃናው ለልዩ ቀማሾች የተለያየ ሆኖ መታየቱን እንጂ ባሕርዩ ከቶም ያልተለመደ ጉዳይ መሆኑን አይነግረንም። ይሁንና ባለ ቅኔው አልፍሬድ ሀውስማን "መድኃኒት ቀማሚዎች ጨው የሚለውን ቃል እንደሚያስቡት፣ እኛም 'ሥነ-ግጥም' የሚለውን ቃል እንዳናስበው አደራ እንጠብቅ!" ሲል በሌላ መልክ የዚሁኑ የነበረ የልዩነት ነፃነት መንገሩ ይመስለኛል። በዚህ

መጽሐፍ የተጠረዙት ግጥሞች ጠቅላላ የግጥም ሥራዎቼ ሳይሆኑ፤ ከድምሩ ውስጥ ከየዓይነቱ መርጬ ያቀረብኳቸውን ብቻ ነው። ከዚህም ሌላ ለአንባብያን ላስታውስ የምወደው፤ ለምሳሌ "እናት" ማለት "ህዳ" ለሚለው የኦሮምኛ የኩሽ ቃል፤ "ዳ" ለተሰኘው ትክክለኛ የልሣን ምልክት፥ በቀደምቱ በኢሮግሊፊክ ፊደል እንጂ በኋለኞቹ ወራሾች በሴማውያን፤ ወይም በግሪክና በላቲን ፊደሎች ውስጥ ስላልተመደበለት፥ እነሆ ለጊዜው "ደ" በተሰኘው የሳባውያን ወይም የግዕዝ ፊደል አናት ላይ "´" ይኽን ቁም-ሠረዝ በማከል "ደ́" እያሰኘሁ መጠቀሜን ነው።

## ለ/ ሥነ-ግጥምን እንደ ቃለ-ሕይወት ፈለግ ፍሬ-ሃሳብ

የኪነ-ጥበብ ፈለግ በሚውተበተብበት ዋዜማ ጠንቋይ ጠቢብ ነውና፤ በአፈ-ሊቃውንቱ ወረርሺኝ ብዛት እንደኮካ-ኮላ የማስታወቂያ ግጥም ዓይነቱ ጭምር የነገውን ትውልድ የሥነ-ባህል ሥፍራ ተክቶ፤ የሕፃናቱም አንደበት በእንቆቅልሹ 'አ-ቡ-ጊ-ዳ' ሲታጠንና ሲታነፅ እያየነው፤ የባለቅኔው ብዕር መልእክቱን ሁልጊዜም ወደተረሳው ወደአበው ጥንተ-ድንጋጌ እንጂ ወደ አዲሱ ዓለም ሕይወት አይላክ ብንል፤ ሌላው ቀርቶ እነድራይደን እንኳ፤ "የሞራል እውነታም የባለ ቅኔው ፍቅረኛ እኮ ናት፤" ይሉናል። ይህም ማለት፤ የዘልማድ ንፍገት ያጥላላውን እውነታ ደሞ አባብሰን በይበልጥ ለማጕልደፍ ሳይሆን፤ ይልቅስ፤ ውስጣዊና ሕያዊ ባሕርዩን መርጠ አንቅቶ፥ ውበት አክሎ፥ በአስተዋይ ኅሊናችን ውስጥ ቁሰሉን የመፈወሱም ጥረት፤ ለሥነ-ግጥም ያው የኖረ ጠባይዋና ደመ-ሕይወቷ ነው። መቸም ቢሆን የእውነት ፍቅር ያነጠራትን ዘለዓለማዊት ኪነ-ጥበብ አእምሮ የገራው ስሜት ይፋ ያወጣታል ይላልና ኮለሪጅ።

ግሪኮች ባለቅኔዎቻቸውን ለሁለት ከፍለው፤ የአንደኛውን ወገን ድንጋጌን ተከባክበው - እሚቀርፁ፤ ሲሏቸው፤ የሁለተኛውን ደግሞ ቃለ-ሕይወትን አንቅተው-እሚፀንሱ እንደሚሏቸው ይገልጽና ደራሲው ጊልበርት፤ "ሁለቱም ወገን እኩዮች ናቸው። ያም ሆኖ ያንዱ እኩያነት ከሌላው ያይላል" ይላል። የሥነ-ግጥም ኅሊና፥ በየትውልዱ የሕይወት ተአምር የመደነቅ ሕዋስዋን፥ እያደር ቆዳውን በሚቀይርባት ንፍገት ስትገደብ፥ ሁሉን-አወቅ የምጸተኝነት ባሕርይዋ ይተናነቃትና ለጋ ሃሳብ የምትፀንስበት ልቦናዋም እየጠበበ ትነጥፋለች። "ሁሉን-አወቅነት፥ የእኔነትን (የኢጎን) ሕልውና፥ ሁሉን-ጠየቅነት ደሞ የመፍጠርን (የልብ ወለድን) ፅንሰ-ሕልውና ያስከትላል፤" እንዲል ባለቅኔው ብሪጊን። ዘለቄታ የሚኖረው ሥነ-ግጥም የሰውን ልጅ ዘለዓለማዊ የሐቅ እውነታ ሊያቅፍና ሊያበሥር ይሻዋልና። ምርድስዋርዝ ለጆን ዊልሰን በጻፈለት ደብዳቤው ይኽን ጉዳይ ተመራምሮ ሲመልስ፥ የግጥም ኪነት ሰብአዊነታችንን የሚያስደስት ትርኢት ነው ስንል ሰብአዊ ፍጥረታችንንም የማይሸነግል መሆኑ ይታወቀናል፤ ካለ በኋላ፥ ይህንኑ እንዴት ከመንፈሳችን እንደምናገናዝበው ሲያስረዳ "....እርቃነ ልቦናችንን ወደ አልባሌው ሰው የየዕለት ሕይወት ገልጠን ተፈጥሮአችንን በተፈጥሮው ገጽ ከማስተዋል...." የምንቀምረው ሲሆን ነው ይላል። ሸክላ ሠሪ ጡቧን፤ ተፈጥሮ እኛን ከልዩ ትቢያ እንደምትቀርጽ ሁሉ፥ ባለቅኔም ኪነትን ከምርጥ ቃለ-ሕይወት ዳግመኛ ፈጠረ ሲባል፤ ተፈጥሮ የለገሠችው ዕድሜውንም በሕይወት ዋጋ ላይ እንደ ማዕድን ፈትኖና አንጥሮ ፍሬዋን ብቻ የማብሠር ግለኛ ጥረቱን፥ "ያ ለማንም ሰው ከሚሰማው ይፋ ስሜት፤ ለሕፃኑ እንኳ ከሚሰማው ይፋ ስሜት፤ ሌላው በተደሰተ ከሚያስደስተን፤ ሌላው ባዘነ ከሚያሳዝነን፥ ነፍሱን ከነፍሳችን ከሚያጣምረን 'የፈለቀ'፤ ያ ነው የኪነ-ጥበብ ደመ-ሕይወት፤" ይለዋል ቶልስቶይ። በኪነ-ጥበብ የተስጥዎ ግዳጁ ተዳክሞ ተጭለምልሞ ነፍሱን ሲያሳድፍና የስሙን ጨኸት በምጥ በማስተጋባቱ ብቻ ዕለታዊ ተደማጭነትን እንደጥቅም ሲቃርምና ሲዘርፍ ግን፤ '....ያማ የኪነቱን የእውነታ አቅጣጫ ስቶ ብዕሩንም አሳተ፤' ማለት ነው ይላል ብሮኖውስኪ።

ያም ሆኖ፤ በሌላ መልኳ፤ ሥነ-ግጥም ሕይወትን ተቻችሎም ሆነ አተኩሮ ለመዝለቅ ሲባል ኅሊናን በኅሊና የመፈተን ውጤት ስትሆን፤ አንዳንዴም ከብቸኝነት ሕልውናችን ውስጥ ብቻ የምትደመጥ ሙዚቃዊ ፊደል ናትና፤ የኑሮን

ውትብትብ ጠልቀን፣ ሠርሥረን ገብተን አገኘን የምንለውን ፍሬ-ሃሳብ መንጥቀን አውጥተን በአደባባይ ስንገልጥ፤ 'ቃልን' በውበት በድቀትና በአክብሮት እንዲንጸባረቅ ካደረግነው፤ የየፊንታችንን ፀንሰን አሳልፊነዋልና፤ 'ቃልን' ገደፍክ አንባልም። ቃል ኃይል ነውና። ቃል ውበት ነውና። ቃል እውነት ነውና። ቃል ሕይወት ነውና። "አስቀድሞ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዜብሔር ዘንድ ነበረ፤ ያም ቃል እግዚአብሔር ነበረ፤" እንዲል።

ጸ.ገ.መ.

# ማ ው ጫ


| አርእስት | | ገጽ |
|---|---|---|
| ይድረስ ለወንድሜ ለማላውቅህ | | 21 |
| ለበጌምድር ወይጦ ባላገር | ፲፱፻፷፫ - ደባርቅ | |
| አይ መርካቶ | ፲፱፻፷፰ - መርካቶ | 28 |
| ቃል ቃተተ | • | 33 |
| ለአበራ በነበር | ፲፱፻፶፯ - ጉለሌ | |
| የብዕር እሟሟት ሌላ | | 36 |
| ለካሣ ተሰማ | ፲፱፻፶፱ - ቆቃ | |
| ክልሰ አባ-ልበ-እግረኛ | | 39 |
| ለማዳም ሄለን ደጉ ወ/ጊዮርጊስ | ፲፱፻፷ | |
| መውደድ አባ ጸጸት | ፲፱፻፶፪ - ሁሱቃ | 45 |
| መተማን በሕልም | ፲፱፻፷፪ - እንዳሥላሴ | 49 |
| በቃኝ | | 51 |
| ለኢታፋ ዋላጋ | ፲፱፻፶፯ - ቀበና | |
| ቦረን (የሃዩ አባኬ ሊበን ቀረርቶ) | | 53 |
| ለእሥመሮም ለገሠ | ፲፱፻፷፪ - ሊበን | |
| ዋ! .... ያቺ ዓድዋ | ፲፱፻፷፬ - ዓድዋ | 56 |
| ሕይወት ቢራ ቢሮ | ፲፱፻፷፩ - ሰድሰት ኪሎ | 59 |
| መሸ ደሞ እምባ ልውጣ! | ፲፱፻፶፩ - ቢሾፍቱ | 65 |
| ማነው 'ምንትስ'? | ፲፱፻፷፫ - አዲሳባ | 86 |





| | | |
|---|---|---|
| 'እከካም ተማሪ' | | 78 |
| ለእንዲት የቅኔ-ምሽት | ፲፱፻፶፰ | |
| ረሃብ ሰንት ቀን ይፈጃል? | ፲፱፻፷፰ - ዋልዲያ | 87 |
| ምነው እምቦ? | ፲፱፻፷ - እምቦ | 90 |
| 'እቴቴ ዱብራ እሮሞ' | | 91 |
| ለእቴቴ ዱብራ እሮሞ | ፲፱፻፷፪ - ባሌ-ጎባ | |
| ምንም አልል | ፲፱፻፷፫ - 'ፒያሳ' | 94 |
| አዋሽ | | 96 |
| ሰጋማቹ ቃማሊት | ፲፱፻፷፬ - አዋሽ | |
| እግር እንይ! | | 103 |
| 'ለእግረተኞች' | ፲፱፻፷፫ - 'ፒያሳ' | |
| እንኮበር | | 106 |
| ለተፈራ ደገፌ | ፲፱፻፷፰ - ደብረ-ብርሃን | |
| ደኅና ዋይ እማማ | ፲፱፻፶፫ - ሎንዶን | 110 |
| ሊማ-ሊሞ | | 114 |
| ለፈረደ ዘሪሁን | ፲፱፻፷፫ - ተክሌ | |
| ጎል! | | 116 |
| ለኳሰ 'እርበኛ' | ፲፱፻፷ - አዲሳባ | |
| እዴ አዳዩ | | 119 |
| ለአደና ለጎሮምቲ ጉቴ ዳኛ | ፲፱፻፷ - በሎ | |
| የት አባቱ! ሞትም ይሙት! | ፲፱፻፷፫ - ዶርዜ ሠፈር | 128 |
| ሰቆቃው ጴጥሮስ | ፲፱፻፷፩ - ቀበና | 131 |
| እንቅልፍ ነው እሚያሰወሰድህ | | 136 |
| ለኤድዋርዶ ሞንድሌን | ፲፱፻፶፱ - ዳሬ-ሰላም | |

| | | |
|---|---|---|
| እባት ወይ አበባ | | 139 |
| ለእባምነው ገብረ ወልድ | ፲፱፻፷ - አራት ኪሎ | |
| አስቀመጡህ አሉ! | ፲፱፻፷፩ - አምቦ | 155 |
| አባይ | | 159 |
| ለየኔታ አሥረስ የኔሰው | ፲፱፻፷፱ - ቴቤስ ሙታን ከተማ | |
| መሄዱ ነው | ፲፱፻፷ - ቤልግሬድ | 164 |
| ዶጋሊ | ፲፱፻፷፭ - ጉርጉስም | 165 |
| ቦረን (የሙርቲ - ጸሎት - ጥሪ) | | 166 |
| ለማዳ ጋልማ-አባ ጋዳ | ፲፱፻፷፪ - ዲሬ | |
| ውሽታም | ፲፱፻፷፪ - ስድስት ኪሎ | 166 |
| ክፉ | ፲፱፻፶፱ - ጂማ | 170 |
| 'እሳት ዐመድ ወለደ' | ፲፱፻፷፩ - አዲሳባ | 171 |
| 'ለተማሩ'-ለማይምሩ አፈ-ሊቃውንት | | |
| ሐረር | | 174 |
| ለከበበው አሻግሬ | ፲፱፻፷፫ - ሐረር | |
| እውነት አሁን አንቺ እኳ ነሽ! | ፲፱፻፶፰ - አዳማ | 176 |
| በራ፣ የመስቀል ደመራ | ፲፱፻፷፫ - መስቀል አደባባይ | 179 |
| ጌራ | ፲፱፻፷፱ - ፓሪስ | 161 |
| ማይጨው | ፲፱፻፶፰ - ማይጨው | 190 |
| ድሬ-ዳዋ | ፲፱፻፷፭ - ድሬዳዋ | 192 |
| ተወኝ | ፲፱፻፶፯ - ኒውዮርክ | 194 |





| | | |
|---|---|---|
| ድንቅም አደል? | | 196 |
| 'ለብቸኞች' | ፲፱፻፶፱ - አዲሳባ | |
| እብረን ዝም እንበል | ፲፱፻፷፩ - ቆቃ | 196 |
| አሥመራ | ፲፱፻፶፰ - አሥመራ | 201 |
| ወንድ ብቻውን ነው እሚያለቅሰ | | 202 |
| ለዘውዱ ሸዋሞልቶት | ፲፱፻፶፭ - አምቦ-ኮልፌ | |
| ትዝታ | ፲፱፻፶፱ - ጋርባ ጉራቻ | 205 |
| እዘቦን ዳግም እየኳት | ፲፱፻፷፭ - መቀሌ | 206 |
| እንዳይነግርህ እንዳች እውነት! | ፲፱፻፷፫ - አዲሳባ | 208 |
| የቴዎድሮስ ለንብት ከመቅደላ | | 210 |
| ለዓለማየሁ ቴዎድሮስ | ፲፱፻፶፯ - ደሴ | |


---

በየግጥሙ እርእሰትና ጽሑፍ አቅጣጫና ግርጌ የተጠቀሰው ቀንና ሀገር እያንዳንዱ ግጥም የተደረሰበትን ጊዜና ቦታ እንጂ፣ በመታሰቢያነት የሠፈረላቸውን ሰዎች አይጠቅሰም።

## ይድረስ ለወንድሜ ለማላውቅህ

ይድረስ ላንተ ለማላውቅህ
ለወንድሜ ሩቅ ለማልፍህ
ለምታውቀኝ-ለማላውቅህ፣ ለምታየኝ-ለማላይህ....
ማነህ ባክህ?
ላትወደኝም ላታምነኝም፣ እጢነህ ለምትፈራኝ
ለናገርህ አጠንቅረህ፣ አተኩረህ ለምትሰማኝ....
ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፣ ለአረህ ሂሪው ለገታሩ
ለሩቅ ገጠሬ ነባሩ
ለማላውቅህ ለዳርዳሩ፣....
ማነህ
ከሩቅ የምታስተውለኝ
የማልለይህ-የምትለየኝ
ተግተህ የምትገምተኝ፣ ያላየኸኝ አስመስለህ
አቀርቅረህ ተግ ብለህ
ባንደበትህ የእርግማን መርዝ፣ በልብህ ትእዝብት ቋጥረህ....
የፀጥታው የዋሻው ሱቅ
ማነህ አንተ የቅርቤ-ሩቅ
ማነህ....
ከረን ነህ መለሎ ብሌን
ከአሰብ ወደብ እስከ ሰሜን

ስትሳብ ስትሰበሰብ

ሽንጠ ሰንበሌጠ-መርገብ

ከኡሙ-ራ ነህ ከመረብ

እኑእከ ነህ ወይስ ገለብ

ከዘር ተገፍተህ ተሰደህ

በሐሩር ሰደድ ተጥለህ

በንዳድ መቀመቅ ታጥረህ

በእልቂት አፋፍ ፈፋ ያለህ

ማነህ

'እጋው' ነህ ወይስ ሺናሻ

ቅማንቴ ነህ ወይ ፈላሻ

ስምህ የሆነብን ግርሻ፣

ግራ ጉንደር ነህ መተከል

ባላዋቂ የምላስ ቅርስ፤ የዘር ንፍገት ስትቀበል

ያለዕዳህ ስምህ ሲበከል

እምትችል እምትቀበል፣ እማትሞት እማትነቀል

ማነህ

ቆለኛ ሽከላ ሠሪ ነህ

ያገር ዕድል ያገለለህ።

ለጥበብህ እንደመካስ

በደባትር ትንታግ ምላስ

ዘለዓለም ልብህ የሚላስ



ማነህ

ግባር ነህ የሙከት ሳቢ

አረኛ ነህ የከብት አርቢ

አራሽ ነህ ያገር ቀላቢ

አማል ነህ የግመል ሳቢ ....

ባክህ ማነህ ወንድምዬ፣ አንድም ቀን የማንወያይ

በውል፣ በጣይ፣ ባደባባይ

በፎቶ ግራፍ ዓይን እንጂ፣ ዓይን ለዓይን የማንተያይ

እኔ ለወሬ አንተን መሳይ፣ አንተ ለጭንቅ እኔን መሳይ።

ማነህ እኮ የማላውቅህ

ማዶ ለማዶ ሩቅ ለሩቅ፣ በመኪና ዓይን የማይህ

የማትቀርበኝ የማልቀርብህ

ጠረንከን የምጠየፍህ

በጋዜጣ በመጽሔት፣ ወሬህን የምተርክህ

ሥዕልከን ፎቶግራፍከን፣ ላገር ጉብኚ የምሸጥህ፣

ማነህ አንተ ወንድምዬ፣ የማላውቅህ የምታውቀኝ

ሶዶሬ ማዶ እምታልፈኝ

በዝምታህ የምትከሰኝ

ባይንህ ጦር የምትገሥፀኝ

የሆድከን የማልጠይቅህ፣ የሆድከን የማትነግረኝ፣

ማነህ

ቦረን ነህ አባ ጋናሌ

የኛጻ ጠር አባ ጣሌ
ወይ 'ላፋር' ንጥረ ሶማሌ፣
ከረን ነህ ወይስ ዳንካሌ
አፋር ነህ አባ ቱማታ
ማታሐራ ወይ ከምባታ
ወይስ ኩናማ አባ ዱታ፣
ማነህ ጉበዝ ማነህ እያ
ኢማኑ ነህ አባ ራያ
ወይስ ኢቱ አባ ሎቲ
የአዳል ሞእ የአዳል ሞቲ፣
እኮ ማነህ ሩቅ ያለኸው
ማንነትከን የማላውቀው
እማልሰማ እማልጠይቅህ
እማትነግረኝ እማላውቅህ፣
ማነህ ጉበዝ ሳስተውልህ፣ አተኩረህ ጭጭ እምትል
እማትታጠፍ ቅምጥል
መሃል አገር ያልሸተተህ
ባሻገር ዙር ድንበር ያለህ
የእህል ደላላ እሚበላህ
ባለሚዛን እሚያዋካህ፣
ማነህ
የዝምታ መደብር ነህ?....



እኮ ማነህ ስምህ ማነው
የዘር ግንድህ የሰየመው
ተበጥሶ ያልተቀጠለው
ሥርህ ማነው?....
በልቦናህ የምታማኝ
ታዝበህ የምትስማኝ
ባትወደኝም ባታምነኝም፣ አጢነህ የምትፈራኝ
ማክበር እንጂ እማታስጠጋኝ፣
ማንነትከን ምንነትከን፣ ላልሰማህ የምጠይቅህ
ለጉልበት ለላብህ በቀር፣ ላንተነትህ የማልቀርብህ
ከዓይን-ጥላዬ እምትሸሸኝ፣ ከዓይን-ጥላህ እማልርቅህ
ላፌ እንጂ ለልቦናዬ፣ የማትመስለኝ የማልመስልህ
ከመንፈሴ እምገልልህ
ከሕሊናዬ እማሸሽህ
ቦታህን የማትረሳ፣ ቦታህን የማስታውስህ....
ማነህ
ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፣ ሕመምከን ለማታዋየኝ
በጸጥታህ ለምትወቅሰኝ
ጉፈሬህን እንደአባትህ፣ እንደሞያህ አጎፍረህ
በወለባ አንቆጥቁጠህ
ሎቲ አጥልቀህ ጠር አንግበህ
በመኪና እግር እማልፍህ

የማትጠራኝ የማላውቅህ፣
ማነህ
በየቱሪስቱ ካርድ ላይ
ከቦህ ሰማያዊ ሰማይ
አተኩረህ የምትታይ
ውሸትክን ፈጠህ ሳቅሁ ባይ፣
እንደቴከኖክራሲ አግቦ
ዙሪያህ በህሰት ጌጥ ታጅቦ
እፎይታ ያቀፈህ መስለህ
ትእዝብት በዓይንህ ጦር አዝለህ
ርቀህ ተቀብረህ ሰንብተህ
የቱሪስት ካርድ የሳበህ
አንተ ማነህ?
እኮ ማነህ ወንድምዬ፣ ደራሲ የሚቀኝብህ
ሠዓሊ የሚነድፍብህ
ቀሲስ የሚቀስስብህ
የቱሪስት የጋዜጠኛ፣ ካሜራ እሚጋበዝብህ
የሚተች የሚተረጉም፤ የሚነድፍህ የማንም እጅ
የማነህ ደም የማነህ ቅጅ?....
አንተ የማማ ኢትዮጵያ ልጅ
እኔማ ሆኜብህ ፈረንጅ
አሳብ ለአሳብ ስተጣጣን
ምን አጣላን ማን አጣላን



ማን እንዳንወያይ ገራን
እንደባቢሎን ኬላ ግንብ፣ ለመተላለፍ የቀባን
አንተን የዘልማድ ዘላን፣ እኔን የመኪና ዘላን
እንድንሆን የገፋፋን?
ማነው ምንድነው ወንድሜ፣ ሆድ ለሆድ የሚያናክሰን
ሳንርቅ የሚያራርቀን፣ ሳናኮርፍ የሚያኳርፈን!....
ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፣ ለምትሳብ ናዳ ጥጉን
ፈፋ ዙሪያ ሸንተረሩን
ሸለቆውን ፈረፈሩን
ዳር ድንበሩን ሩቁን-ሩቁን፣
ከዘር ተገፍተህ ተሰደህ
በሐሩር ሰደድ ተጥለህ
በንዳድ መቀመቅ ታጥረህ
በእልቂት አፋፍ ፈፋ ላለህ....
እኛ መሀል ለሌለኸው
ታሪክህ ለተሸፈነው
ሁሉን ከሩቅ አብሰልስለህ፣ አጠንቅረህ ለምታየው....
ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፣ ለምታየኝ ለማላይህ
ለምታውቀኝ ለማላውቅህ
ማነህ ባክህ....
ማነህ

ለበጌምድር ወይጦ ባላገር - (፲፱፻፺፫ - ደባርቅ)

# አይ መርካቶ

አገር ከየጐራው ወጥቶ
አንቺን ብሎ ነቅሎ መጥቶ
ግሣንጉሡን ጓዙን ሞልቶ
ጐልቼ መሣፍርትሽ ፈልቶ
ባንቺ ባዝኖ ተንከራትቶ
እንደባዘቶ ተባዝቶ
ተንጠራውዞ ዋትቶ ዋትቶ
አይ መርካቶ፥
የምድር ዓለም የእንጀራ እናት
ላንዱ ርካሽ ለሌላ እሳት
ላንዱ ፍትሃት ላንዱ ምትሃት
ላንዱ ሲሳይ ላንዱ ፍርሃት
ላንዱ ተስፋ ላንዱ ሥጋት
የግርግር የሆይታ ቋት
አይ መርካቶ፥
ያንዱን ወስዶ ላንድ ሰጥቶ
ያንዱን ገፍፎ ላንዱ አብልቶ
አንዱን ነስቶ ላንዱ አድልቶ
ስንቱን ፈርቶ ስንቱን ሸሽቶ
ባፈ-ጮሌ ተሸልቶ



አይ መርካቶ፥
ቢያዋጣ ወይ ባያዋጣ
ከስንቱ ተንጣጥቶ ጣጣ
ተነታርኮ ተገዛግዞ
ተብለጥልጦ ተበዛብዞ
መርካቶ ያገር ድግሱ
የገጠር ስንቅ አግበስብሱ
ለከተሜው ለአባ ከርሱ
በትሬንታው በአውቶቡሱ
በቁሳቁስ ግሣንጉሱ
ለቱጃር የጥጋብ ቅርሱ
ለኔ ብጤም የቀን ጉርሱ
አባ መስጠት እጦት ቢሱ
አይ መርካቶ፥
ተሻምቶ ተገበያይቶ
ወይ ተፈራርሶ ተጣልቶ
በእንካ ስላንቲያ ተማትቶ
አንዳንዴም ተፈነካክቶ
ወይ ተመራርቆ ተስማምቶ
አይ መርካቶ፥

የኤስፔራንቶ የቋንቋ አገር
ያ ሲነገር ያ ሲሰበር
የስንቱ ልሣን ሲቀመር
ያንዱን ሲያከር ያንዱን ሲያቀር
ያንዱን ሲያውስ ያንዱን ሲያስቀር
ያ ሲደቀል ያ ሲፈጠር
የልሣን ሸማች ለብቻ
ከዕቃው ጭምር በስልቻ
ሲመዠርጥ እንደግቻ
ቶሎ በል ቶሎ በል ብቻ፣
ዝግ በሉ እማይባልበት
መርካቶ የእንደበት ፍላት
ግርግር እሚባልባት
ክርክር እሚሞቅባት
ወዝ እሚንጠፈጠፍባት
ሽቀጥ እሚታመቅባት
ደላላ የሚያውጅባት
ቸርቻሪ እሚተምምባት
ሌባ ላብክን የሚያልብባት
እይ መርካቶ፣
መርካቶ የገበያ ጎራ
ላንዱ ምድር ላንዱ ጣራ



ያ ሲዘረፍ ያ ሲደራ
ያ ሲወስን ያ ሲፈራ
ያ ሲሸሽግ ያ ሲያወራ
የንግድን ጠፍ ወይ የአዝመራ
የነጋዴን ምጥ መከራ፣
የከበረ እንደመረዋ፣ ረብጣ አፍኖት ሲያስገመግም
የከሰረ እንደ ፈላስፋ፣ በቁም ቅዠት ሲያልጐመጉም
የኔ ብጤም ጠብሻን መቶት፣ በየጥሻው ሲያስለመልም
ቸርቻሪ ዝርዝሩን ቋጥሮ፣ ቅንጣቢውን ሲቃርም
የወር ሸማች ስንቁን ጭኖ፣ ሲመርቅና ሲረግም
ግጅራት መቺ ከጀርባው፣ ጥሻውን ዘሎ ሲያዘግም
ከዚህ በርሮ እዚያ ሰብሮ፣ ያዝ ሲባል ሲሸሽ ሲጣጣር
ካማኑኤል እራጉኤል፣ ሾልኮ ዶሮ ማነቂያ ዳር
ከመስጊድ እስከበረንዳ፣ ከአራተኛ እስከነፍስ ይማር
የኡኡታው የጡሩምባው፣ የጩኸቱ የፊሽካው ሣግ
የሰው የመኪና የከብት፣ የፍግ የቁሳቁስ ትንፋግ
ሲገፋተር ሲመዠረጥ፣ ላቦት ለላቦት ሲላላግ
ትንፋሽ ለትንፋሽ ሲማማግ
እባ ሽብሩ መርካቶ፣ ያለውን በገፍ እጣጥቶ
የሌለውን ከሌለበት፣ እስጐልጉሎ እስወጥቶ
ስንቱን ከዳር ዳር እዛምቶ
በግድም በውድ እስማምቶ

አገርን ካገር አካትቶ

ሁሉን አቀፍ ባይ መርካቶ

ያቻችለዋል አሻምቶ፥

አይ መርካቶ

፲፱፻፹፩ - መርካቶ



## ቃል ቃተተ

ቃል አይሞትም ይሏል እንጂ፥ እስትንፋስ ይሞታል ቅሉ

ቃሌ በፅንሱ በነነ፥ እፍ አልሺውና በሽሉ።

ለካስ በቁጠማ ነዶ፥ ዕርግብ ፍላፃ ደብቃ

በንሥር ልቦና መጥቃ

አለሳልሳ አማቅቃ

አምኗት ሲታበይ ነበረ

ያየር ያድማሳት ገሞራው፥ ያ እንደጋሬጣ የሾረ

ርቱእ ጥፍሩ የነፈረ።

ፍጡርሽን መለኮት ብዬ፥ በሥጋ ለበስ ዝንጋኤ

እንደ ብሩክታዊት እንባ፥ ተማጽኜሽ በሱባዔ

'ዝውእቱ ዳግማዊት ሞት፥ ወእስመ አልቦ ትንሣኤ'።....

ምጤን ጭንቄን እንደአንክርት፥ በልቦናሽ አጠንጥኜ

ከባዕድም ከወዳጅም፥ ዓይንና ጆሮ ሸፍኜ

እንደጉድ ፍቅሬን ቀብሬ፥ በእምነትሽ ጥላ ከድኜ

የአንጀት ፍሜን ነበልባሌን፥ አዳፍኜ ተዳፍኜ፥

እዩ ሥጋ ለበስ ተሰፋ

እንዲህ ላም አለኝ በሰማይ፥ የምኞት ዘር አሳቅፋ

ያም በምድረ-በዳ ፈፋ

ካልሳምናት የዕፀ-በለስ ዛፍ፥ ከማንደርለባት ተቀርፋ

በሕልም እንኳ ግጠን ሳንወጣት፤ በቁም ቅዠት ስታስለፋ....

ምነው ረቂቅ ሽል መቅጠፉ? የውን ውላችንስ ይጥፉ
ቃላችንን ካስጐሰበትን፣ እንደ ሥራ-ቤት ልፈፉ
እንደቀፈፉ አቆማዳ፣ ምሥጢር ካፎቱ ከሰፉ
እንደባሰጌ መቀነት፣ ውሉ በልፊያ እየገፉ
እንደአቃቢት ግብር ውሀ፣ ገበና የትም ሲደፋ፤....
ብቻ ጡሩ የግፍ ግፉ
ከበደልም በደል ዕድፉ
ከቶም ረቂቅ ሽል መቅጠፉ።
ገና በቆባው በእምቡጡ
ቡቃያው ከማቆጥቆጡ
ገና በሽል ገና ባፍላ
ዓይኔ ከዓይንሽ ብሌን ጥላ
የቋጠረው ወዝ ሳይሞላ
ሕልሜ ብልጭታው ሳይጠራ
ጭላንጭል መቅረዝ ሳይበራ
ሲቃዬ እስትንፋሱን ሳይረጭ
ደሜ፣ የልቤ ፅንስ እንጭጭ
ምነው ሳይፈጠር ይቀጭ?
በመዳፍሽ የጠለሰው፣ የዕንባ ወዜስ ይምከን፣ ይምጠጥ
የብሌንሽ ወላፍን እጭ፣ እርግብግቢቱ እንዴት ይፍረጥ?....
ለካስ በቁጠማ ነዶ፣ ዕርግብ ፍላፃ ደብቃ
በንሥር ልቦና መጥቃ



ሕዋሱን ደባብሳ አድቅቃ
አሰሳልሳ አማቅቃ
እምኗት ሲታበይ ነበረ
ያ በሞገድ ድባብ መጥቆ፣ ሁሉን ቁልቁል ያተኮረ
እናምርትን ነጌያትን፣ እንስሳትን ያሸበረ
አእዋፍን በደመና፣ አውሬን በደን ያስገበረ
በነበልባል አክናፉት ጦር፣ ያየርን ሰርጥ የሰበረ
የየብስ የአድማሳት ገሞራው፣ ያ እንደ ጋሬጣ የሾረ
ፍላፃ ዓይኖቹን ታውሮ
ርቀእ የጦር-ጥፍሩን ነፍሮ
አውራ-ገነን ከብሩን ከስሮ
ቅስሙን ውጦ፣ ባከኖ አፍሮ
ኩፍ እንዳለች ዶሮ፣ ጓሮ
ሊለቅም ግብስብስ ጭሮ
የጀግና ሐሞቱ ታልቦ
ገሞራነቱ ተሰልቦ....
እምኖሽ ሲታበይ ነበረ
የየብስ ያድማሳት እሳቱ፣ ያ እንደ ጋሬጣ የሾረ
ፍላፃ ዓይኑ የታወረ?
ርቀእ ጥፍሩ የነፈረ?
ገሞራነቱ የከሰረ?

ለአበራ በነበር - (፲፱፻፺፮ - ጉለሌ)

## የብዕር አሟሟት ሌላ

የቃለ-ልሣን ቅመሙ
የባለቅኔ ቀለሙ
ነጠበ እንጂ ፈሰሰ አንበል፣ ቢዘነበል እንኳ ደሙ
ሰከነ እንጂ ከሰሰ አንበል፣ ቢከሰከስ እንኳን አፅሙ
የቃለ እሳት ነበልባሉ
አልባከነምና ውሉ
የዘር-ንድፉ የፊደሉ
ቢሞት እንኳን ሞተ አትበሉ።
እስካልተዳፈነ ፍሙ
እስካልተሰበረ ቅስሙ
እስካልተቀበረ ስሙ
የደራሲ ዐፅመ-ወዙ
የብዕር ቀስተ-መቅረዙ
ሕዋሳቱ እስካልቀዘዙ
አልፏልና ከሥጋ-ሞት
በቃሉ ሚጠት ስልባቦት
በፊደሉ አድማስ-ፍኖት
በኅብረ ቀለሙ ማኅቶት
በሥነ-ግጥሙ ምትሃት
በግሡ ንጥረ-ልሳናት



በነባቢቱ ነፍስ እሳት
ይነዝራልና ደም-ሥሩ፣ አይሞትምና ፀዳሉ
ቢሞት እንኳ ሞተ አትበሉ ....
የብዕር አሟሟት ሌላ፣
ሲፈስ የብሌኑ ኬላ
የፊደል መቅረዝ አሟሟት
ከውስጥ ነው እንደጋን መብራት
በቁም ነው እንደቁም ፍትሐት
የሚያጨልም የነፍስ እሳት፣
እንጂ ብዕር ሞተ አትበሉ፣ እሳቱን ሳያስለመልም
ነበልባሉን ሳያከስም
ውጋጋኑን ሳያጨልም፤
ቃለ-ምንጩን ካልመሰነ፣ ሥሌቱን ካልጐለደፈ
መቅረዙን ካልተዳፈነ፣ ከፊደሉ ካልነጠፈ
ዐፅመ-ወዙን ካልደረቀ፣ ጧፉን ቀልጠ ካልሰፈፈ
ጡጠ እንደጠፋበት አራስ፣ ቁም ተዝካሩን ካልሰፈፈ
ብዕሩ ቀርቶ ምላሱ፣ በሃሜት ካልተንጠፈጠፈ፣
የቃለ-እሳት ነበልባሉ
የድምፀ ብርሃን ፀዳሉ
የኅብረ ቀለማት ኃይሉ

አልባክነምና ውሉ
የዘር-ንድፉ የፈደሉ
ቢሞት እንኳን ሞተ አትበሉ።

ለካሣ ተሰማ - (፲፱፻፶፱ - ቆቃ)



# ክልስ - አባ - ልበ - እግረኛ

ከብቸኞችም ብቸኛ
ያንድ ሃሳብ-ግዞት-ቁራኛ
ከግለኞችም ግለኛ
ክልስ አባ-ነፋሱ-አትተኛ
የመንፈስ-ራብ ግዞተኛ
ባክኖ በእምነት ፈለግ-እርከን
የወዳጅ ቀፋፊው ዘላን፤
ክልስ የእምነት-ምስኪን ድንዝዝ
ግንጥል የቂም-ቁስል ምርቅዝ
ግንዝ+ ክልስ ፍቅረ ግንዝ፤
የበቀል ነፍስ-ጡር ትኩዝ
ግልል ያገር ሕመም ግዑዝ
ብቸኝነት ያስጨከነው
ያም ያን ሲለው ያም ያን ሲለው
ከብቸኛ ልቡ ሌላ+ ወዳጅ ያለው የማይመስለው፤
ከቆዳው ወይ ከምላሱ
የማይረሳለት ድጉሱ
ከሁለት ዘር መታመሱ
ከሁለት ደም መደገሱ፤
ያየኝ እስታወሰኝ ብሎ+ የነፍሱን ቁስል ደብቆ

በሥጋና በወዝ ቀርቦ፥ በውስጠኝነቱ ርቆ
በግለኝነቱ ማቅቆ
ከሁለት እንደወደቀ፥ ነፍሱን ከነፍሱ አስተራርቆ
አንዳንዴም ልቡን አግዞ
አንዳንዴም ቂሙን አርግዞ
ያቺን የሰው እምነት ራቡን
የብቸኝነት እርቃኑን
በእድሜ የተጥላላች ነፍሱን
ተገንጥላ እንደዋተተች፥ በእምነት ረሃብ ስትገረጣ
ብድሩን ሊከፈልላት፥ እንደተቀጣች ሊቀጣ
በብሩ ወይ በሥልጣኑ፥ የማታ ማታ ሊወጣ
እምነቱ እንደተባዘተ፥ ድንጉጥ ባንዳ ሊያነበንብ
እንደቤት-ውልድ የበቀል ልብ፥
ያን የመንፈሱን ቀፎነት፥ በገንዘብ ጠግኖ ሊከብ
እንደጠበቃ በድብቅ፥ እንደሞኛ በክንብንብ።
አንዳንዴም ባለቤት ሆኖ
በተቆርቋሪነት ገንኖ
ሕዝባዊነቱን አጋኖ
በአደባባይ አስተማምኖ
ሊፈወስ ሲል ከቂም ድኖ
ባሉ-ቧልታ ምጸተኞች
በወግ ታዛቢ. አፈ-ጊንጦች



ተጠልፎ በወጥመዳቸው፥ በሰው ሊቃ ቀለብተኞች
እፍ ላፍ ሲመሰጣጠሩ፥ በፈገግታ በዓይን-ጥቅሻ
በውስጠ-ዘ ከንፈር ንክሻ
በሱነቱ እንዳይታመን፥ የልብ እርካታ እንዳይሻ
በግንባር እሱን ጠቁመው
ተጠቃቅሰው እሱን ጠቅሰው
በምጸት ልቡን ፈርፍረው
የምላቸውን አቁለለው
እንዳላየም ሆኖ እንዲያየው
እንዲያውቀው እንዲያስታውሰው
መለየቱን እንዲለየው።
ብግም ለሱው ቁጭተኞች፥ መስለው ቀርበው እንዲያድጉበት
በእእምሮው ወይ በገንዘቡ፥ ወይ በሥልጣኑ ሊያውቁበት
ጠላታቸውን ጠላቱ፥ አርገው ጠላት ሊገዙለት
ወዳጃቸውን ወዳጁ፥ አርገው ወዳጅ ሊሸጡለት
እምነቱን ሊታመኑበት
ድጉቱን ሊታደጉበት
ውስጡን ሆድ ለሆድ ሊሰቁ
ለሆዳቸው ስላወቁ
እሱ ውሉን መጠበቁ
ለነሱ ልቡን ማውለቁ
የግፍ ድርብ እሳልቋቸው፥ በሱው ስለሚደነቁ፥

ዘንግተውት ወይ አውቀውት
ኀሊናቸውን ሰልበውት
የእምነት ከልሶች እነሱ
በመሆን እንደሚብሱ
ተሸነጋግለው ሊረሱ፥
ያንዱ ርቆት ያንዱ ንቆት፥ ከሁለት ወገን መውደቁ
የዘር ሕመም መነጠቁ
ስለማይመስላቸው ብቁ
የግል ሕመሙን ሳያውቁ
ጥቃቱንም ሳይጠቁ
ለጥቅማቸው እንጂ ለሱ፥ እንዳችም ሳይጨነቁ
የምጸቱ ሞያተኞች
የኀሊና ጃንደረቦች
መሆናቸውን ሲረሱ
እሱ ሳይቀር ማስታወሱ
ጠርጣሪ ሆናበት ነፍሱ፣
አንዱ ስሙን ሲያልከሰከስ
አንዱ ደሙን ሲያቀናንስ
ሌላው ቅስሙን ሲያከሳክስ፣
ከልሱን እንደዘር-ቅዳጅ
'የቤት ውልዱን' ፍናጅ-ቅናጅ
ከማለት ሳይታገዱ፣ ሳይቀር ያፈ ልማዱ ጠንቅ



ያም የቆሸቱን ቁስል ሳይድን፣ ከቂም ፅንሱ ሳይላቀቅ
አድርገውት ፍቅረ-በድን
ከመንፈሱም ሕመም ሳይድን
መለዮው ከቶ ተቃርኖ፥ እውነታው ከቶ ተማጥቆ
ባቀፈው ቂሙን አምቆ
በጣሉት ልቡን-አሙቆ
ሲያርቁትም ባፍ-አጥላልቶ፥ ሲያቀርቡትም ውስጡን ንቆ
ከዓለም ተጣራሪ ጠባይ፥ ያለውዱ የፈለቀ
ከሁለት ዛፍ የወደቀ
አንድ የጣለው ካንድ የራቀ፣
ክልስ አባ-ልበ-እግረኛ
ያንድ ሃሳብ-ግዞት-ቁራኛ
ከግለኞችም ግለኛ
የወዳጅ ቀፋፊው ዘላን
ባከና በእምነት ፈለግ-እርካን
ያም ያን ሲለው ያም ያን ሲለው
ብቸኝነት ያሰጨከነው....
ያለግዞተኛ ልቡ፥ ወዳጅ አለኝ የማይለው፤
ክልስ ግውዝ
ክልስ ትኩዝ
ግንጥል የቂም ቁስል ምርቅዝ
ግልል ክልለ ፍቅረ-ግንዝ

የመንፈስ-ራብ ግዞተኛ

ከግለኞችም ግለኛ

ከብቸኞችም ብቸኛ....

ከልስ-አባ-ልበ-እግረኛ።

ለማዳም ሄለን ደጉ ወልደ ጊዮርጊስ - (፲፱፻፹)



## መውደድ አባ ጸጸት

ዋሽቼ እንደነበር+ ምነው ባወቅሽብኝ

ጉዴን ባየሽብኝ።

"በቃኝ!" ስልሽ ሙኬ+ መርሬ አማርሬ

አርሬ አሳርሬ

"እክ እትፍ!" ስልሽ+ ስተፋሽ አንቅሬ+

ምነው ባወቅሽብኝ

ጉዴን ባየሽብኝ።

"ዱታው ዘራፍ" ስልሽ....

"ገነን በዬኝ" ስልሽ+

ወይ አለማየትሽ

ወይ አለማየቴ

ባላንጣ እንደሆነኝ+ የገዛ አንደበቴ+

በገዛ ልሳኔ+ ያንጀቴን ማነቁ

ወይ አለማወቅሽ+ ወይ አለማወቁ....

ለካስ አፍ ባዳ ነው+ የልብ እውነት ደፍኖ

የላንቃን አጋኖ

ያንጀትን አባክኖ....

በቃ እንግዲህ በቃን+ አንቺም ሸር እኔም ሸር

አንቺም ብር እኔም ብር+

አንቺ ቢል!

እኔ ቢል!
አንቺ እርር!
እኔ እርር!
ዕድሜ ድንብር ግትር
“ሳይቾግር ጤፍ ብድር”
እውነት ያፍ እፍ ሆኗል፣ የልባችን ይቅር።
‘ብጥስ ቅንጥስ ነው! ታድያስ! ኧረ ንሳ!’
“ወጉስ-ማዕረጉሳ!”፣....
ሆኖስ፣ ምን ተረፈን?
ሆያ ሆዬው ብቻ፣ ፋንፋና ጨረሰን!....
ተስፋ መፍለቅለቋ፣ ከነምንጯ ሲበልዝ
ነፍስ እርግብግቢቷ፣ ከደም ሥሯ ሲቀዝ
ሕልማችን ከዋዥ፣ በሕሊናችን ከስ
ዓይን ያይን ዓዋጅ ነው፣ አንጀታችን ያልቅስ።
የገደል ማሚቶው፣ እፍ በተነፈስ
“ክብሬን ነከቶ!” ብለን፣ ልጅነት ፈረሰ።
እውነት ደፈረሰ
“ዳቦ ተቆረሰ”
እውነት ያንጀት እውነት፣ እንቆቅልሽ ሆነ
እንደ ዓመድ በነነ፣
ያለእምነታችን ባሕል፣ ጊዜ ያስአባዳጊ
የስማሽውን ነው፣ ‘ሆዴ ምን ታረጊ’....



ወሬ ካሸነፈን
ጉራ ግርግሩ፣ ‘ኤክስፖው’ ይማርከን?
ጠፋን ላሉ ቧልታ
ለይስሙላ እምቢልታ?....
ተሸጠ እንደ ተረብ
በቧልት ሊነበብ
የነፍሴ የነፍስሽ፣ ገበና ታተተ
በመበለትና፣ ባዋጅ ተተረተ
አንቺም የኔ እፍታ፣ ወዝሽ ተጨለፈ
አበባሽ ረገፈ
ልጅነት አለፈ
መውደድ አባ ጸጸት፣ በዕድሜ ተቆለፈ
ጠና፣ ጐሰደፈ
ጫጩ፣ ገረጀፈ።
መውተርተር ተረፈን፣ ቢያስጠቃም ቢያስከፋም
“እንግዲህ ልጅነት፣ ተመልሶ አይመጣም።”....
“አልወድሽም ያልኩሽ፣ ውሸቴ ውሸቴ”
“ሳይሽ ብንን፣ ብንን ይላል አከላቴ”
ሳጣሽ እርር ኩርምት፣ ይላል ሆዴ አንጀቴ፣....
ወይ አጉል እርግማን፣ ወይ ከንቱ መገደር
ያንጀቴን ቀብሬ፣ ያፌን ብቻ ነበር፣....
ወይ በነቃሁብሽ ፣ ወይ በነቃሽብኝ

ዋሽቼ እንደነበር፥ ምነው ባወቅሽብኝ
የሆድሽን ባየሁት፥ ሆዴን ባየሽብኝ።

፲፱፻፺፯ - ሁሉቃ



## መተማን በሕልም

መተማ የጎንደር ዘማች
ተቾግሮ በሕልም አፋች
ትርጉሙ ተወሳሰቦበት
የሄሮድስ ልጅ ሰሎሜ፥ ተገልጣ ገለጠችበት።
እንዲህ ስትል:-
"ሟች የገዛ ሕልሙን ሥዕል
ቀን እያስታወሰ ሲስል
ትርጉሙን መፋጠጥ ባስቶ፥ ያልመሰለው እንዲመስል
ሐቁን በተስፋ ሲያጣጥል
ቆሜ እሻል ሞቼ እሻል እንዲል፥
እንደሞት ሁሉ ላንድ ሞት፥ መተማ ሁለት ፊት ትገል
ያንዱን ዕድል ለሌላው ድል
ለታሪክ ኀሊና ቁስል
በዕድሜ ምዕራፍ ስታዋውል፥
ሐለስተ-ዓጸት መተማ
ጊዜ ባንቺ ቀን ታድማ
ነጋ-ጠባ ስታቅማማ
ደማች የፋሲል ከተማ።"....
ከራስ ዳሽን አድማስ ግርጌ፥ ከዞብል መቃብር ማዶ
መተማ የተኛ ዘንዶ

ተምዘግዝጐ ጠረፍ ንዶ
እንደሰሎሜ ምሳሌ፥ እንደሂሮድስ ሴት ልጅ ሽንጥ
በኖባ ተራራ ጥምጥም፥ ሠራ-አካሉን ቢያንቀጠቅጥ
እርበድብዶ ቢያቅበጠብጥ
ጎንደር ይዟት የብቻ ምጥ፥
አዋላጂቱ ሰሎሜም፥ ሰቧት የግዝፈቱ ግርማ
የመጥምቅ ደም ብትጠማ
የጂሃድ ሰይፍ አቅዘምዝማ
ዮሐንስን በመተማ
ባረከች ፋሲል ከተማ።
ጎለተ-ዝሙት ሰሎሜ
አድራ ከደርቡሽ ቅማሜ
ከቅንዝር በቀል ሰያሜ
ምሰለ በለሰ የእንስት እሣች
ሕልሙን ለጎንደር ሰው ዘማች
መቅደላ ላይ ፊት ያማታች
በመተማ ቆርጣ ፈታች።

፲፱፻፸፱ - እንጳሥላሴ



# በ ቃ ኝ

በቃኝ የኑሮ አጉራህ ጠናኝ፥
እፎይ የዕድሜ-አዚሜ ጠራኝ።
እስለመለመ መብራቱ
በሕይወት የመዋተቱ
ከነግ-ነግ መንከራተቱ
መንከላወሱ ልፋቱ....
መከራ ሻማዋ ጠፋ
መሸ ቀኔ ላንቀላፋ።
የዕድሜ-ጀምበሬ ጠለቀች
ቅድመ-ፍጥረቴ አሸለመች
ልደቴ ተረመረመች
ተጭለመለመች በበርኖስ
እንደጭጋግ ዶፍ ጥቀርሻ፥ ተዳፍና የዕድሜዬ ፋኖስ
ጠራኝ፥ የዕድሜ አዚሜ ጠራኝ
እኔም በቃኝ እፎይ በቃኝ፥
መሸች ጠለቀች ፀሐዬ
የሕይወት ክረምቴ ወጣች፥ ጉም ተላበሰች ጥላዬ
እረፍቷን ተከናነበች፥ ተሰለመለመች ዕጣዬ፥
በቃኝ ትግሌን ተገላገልኩ
ውጣ ውረዴን አከተምኩ

እፎይ ደከምኩ አስለመለምኩ....
ተሸነፍኩ አዎን ተሸነፍኩ+
የከበደኝ ጣር ቀለለኝ
ያታከተኝ ያደከመኝ
ያሰለቸኝ ዕድሜ ተወኝ
እፎይ ቀለለኝ ቀለለኝ....
ባለወር ተራ ተተካ
ተቀበለኝ ትግሌን እንካ+
ማነህ አንተ ባለላምንት
ያሰጠምድህ ባስራ ለድስት
በዕድሜህ ያሰጠምድህ....ወይኔ
በልደትህ ያስፈርድህ....መጥኔ
ለኔስ መሽቶልኛል ቀኔ።
በቃኝ የኑሮ አንራህ ጠናኝ
እፎይ የዕድሜ-አዚሜ ጠራኝ።

ለኢታፋ ዋላጋ - (፲፱፻፺፮)



## ቦረን (የሃዩ አላኬ ሊበን ቀረርቶ)

ዳምባል!  ጋላልቻ ሬሮ!
ኢማጂ ዲና!  አባ ጋናሌ!
"ዳምባል!" እለ
("የሀሪያውን" - የዕድሜ እኩያ ጓዱን ስያሜ ነው)
ዳምባል!  እንዲያው በስመ ዳምባል
የከረምቱን ጐርፍ አይደል....
የዘንካቶቹን እንጂ
የአሬሮን ምንጭ ቅጂ
የነጋላልቻን ቅጂ!
የዲናው መቅሠፍት እሳት
ዱታው የነጉዮ አባት
ዳምበል!  ድምፀ አባ ሮሮ
እንደምንሸር አምሮ
ሸንቃጣው ግዳይ-ጣሌ
ሮሮዬም እንደቃሌ
ዳምባል!  አባ ጋናሌ!
መልሼ መላልሼ
ደጋግሜ አሠልሼ
ደጋግሞ ገዳይ ሾጤ
መላልሶ ጣይ ሰተቴ

ብላ ወልዳኝ እናቴ
ዳምባል ገደል-ከሣቴ!
እንደአይጥ ፈፋ ምሶ
እንዳይሞት ትቢያ ልሶ
ሲቀር በጉዲፈቻ
ነበር ያረኩት አቻ።
ዳምባል! የሚያውቅ ይወቀኝ
ወትሮም የቦረን እሳት፥ እምበኘው እኔ ነኝ!
የሚያውቀኝ ወትሮም ያውቃል፥ ዱታው የነዲና ጣር!
የማያውቀኝ ያው ይማር
ያውሬን ጭለማ ጠስል
የደኑን ዋሻ ገደል
መንጥሮ-ገባን ዳምባል!
ባንዲት መካን ሴት ኩራት
እልሰማ ብዬ ጥቃት
የቆንጨሮ ፍም እሳት
ሌሊት ጀምበር ሳትወጣ
ገባሁት በጨበጣ!
ጨረር ሳትቀላ በደን
በዋርሲቱ ልጆች ቀን
የሰባት ጓድ ሁለት ረድፍ
ጭለማ ለብሶ ሲከንፍ



እኔ የመቅሰፍት እጁ
ከነጐልማሳ ልጁ
ተግ ሲል እንዳየሁት
በገዛ ደሙ አጠብኩት!
ስመለስ ቀን ሳይነጋ
ብቻውን ካውሬ መንጋ
ጥንድ አውራሪስ አድፍጦ
ቢጋፈጠኝ አፍጥጦ
በከረዮ ሴት ኩራት
አልኖር ብዬ በጥቃት
ቤቴን በረቴን ትቼ
ሎጋ ጦሬን እንግቼ
በዳምባል ስም እንደማልኩ
ኮርማ አውራሪስ ተንተራስኩ።
ሸንቃጣው ግዳይ-ጣሌ
ዳምባል አባ ጋናሌ!

ዳምባል! ሮሮምሳ ጲራ!
ዳምባል! ጋላልቻ ሬሮ!
ኢማጂ ዲና! አባ ጋናሌ!

ለአሥመሮም ለገሠ - (፲፱፻፷፪ - ሊበን)

# ዋ! .... ያቺ ዓድዋ

ዋ! ....
ዓድዋ ሩቅዋ
የዓለት ምሰሶ አድማስ ቀጋዋ
ሰማይ ጠቀስ ጭጋግ ዳስዋ
ዓድዋ ....
ባንቺ ብቻ ሕልውና
በትዝታሽ ብፅዕና
በመስዋዕት ክንድሽ ዜና
አበው ታደሙ እንደገና....
ዋ!
ዓድዋ የዘር ዐፅመ ርስትዋ
የደም ትቢያ መቀነትዋ
በሞት ከባርነት ሥርየት
በደም ስነፃነት ስለት
አበው የተሰውብሽ ለት!
ዓድዋ
የኩሩ ትውልድ ቅርስዋ
የኢትዮጵያነት ምስክርዋ
ዓድዋ
የኩሩ ደም ባንቺ ጽዋ



ታድማ በመዘንበልዋ
ዐፅምሽ በትንሣኤ ነፋስ
ደምሽ በነፃነት ሕዋስ
ሲቀሰቀስ ትንሣኤዋ
ተግ ሲል ሲንር ትቢያዋ
ብር ትር ሲል ጥሪዋ
ድው-እልም ሲል ጋሻዋ
ሲያስተጋባ ከበሮዋ
ሲያስገመግም ዳኘው መድፍዋ
ያባ መቻል ያባ ዳኘው
ያባ ነፍሶ ያባ ቃኘው
ያባ በለው በለው ሲለው
በለው-በለው-በለው-በለው!
ዋ! .... ዓድዋ ....
ያንቺን ጽዋ ያንቺን አይጣል
ማስቻል ያለው አባ መቻል
በዳኘው ልብ በአባ መላው
በገበየሁ በአባ ጐራው
በአባ ነፍሶ በአባ ቃኘው
በለው ብሎ፥ በለው-በለው!

ዋ! .... ዓድዋ ....

ዓድዋ የትላንትናዋ

ይኸው ባንቺ ሕልውና

በትዝታሽ ብፅዕና

በመስዋዕት ክንድሽ ዝና

በነፃነት ቅርሰሽ ዜና

አበው ተነሡ እንደገና።

.... ዋ! .... ያቺ ዓድዋ

ዓድዋ ሩቅዋ

የአለት ምሰሶ አድማስ ጥግዋ

ሰማይ ጠቀስ ጭጋግ ዳስዋ

ዓድዋ ....

የካቲት - (፲፱፻፷፬ - ዓድዋ)



## ሕይወት ቢራቢሮ

ቢራ ቢሮ ከአበባው ላይ፥ ምን አይተሽ ነው ከቅጠሉ

ከቄጠማው፥ ከለምለሙ፥ ሰምረሽ፥ አቅፈሽ መመሰሉ

ለምንድነው ቢራ ቢሮ

አበባሽ ከአበባው ሠምሮ፥

በፀደይ ከዐደይ ጋር ፈክቶ

በርቶ፥ ተጥለቅልቆ ደርቶ

እንደ ጮራ ተንዠርግጎ፥ በመንጸባርቅ ተንጣሎ

ፀደይ አክሎ ፀደይ መስሎ

ውሎ፥ .... ኋላ ቀኑ ሲመሽ

ፀሐይ ግንባሯን ቀልሳ፥ ከጭለማ ክንፍ ስትሸሽ

ብርሃኗ በሌት ተዳፍኖ፥ ዓይኗም ፈገግታዋም ሲሰንፍ

አዝርእቱ እርጭ ብሎ፥ ጸጋውን ከመልኩ ሲገፍ

አበባው ምድሩን ሲንተራስ፥ ያፈር ጽዋ ዕረፍቱን ሲገድፍ

ቢራ ቢሮ ያንቺስ ሞገስ፥ ለምንድነው አብሮ እሚረግፍ? ....

ምን አይተሻል ከቄጠማ፥ ምን አይተሻል ከለምለሙ

ቀን አብረሽ አብበሽ ውለሽ፥ ሲመሽ አብረሽ መለለምለሙ? ....

አስተምሪኝ ቢራ ቢሮ፥ ሰው ለመባል አለኝታዬ

ቀድሞ የት ነው መነሻዬ

ሲመሽ የት ነው መድረሻዬ? ....

ሲተረትማ ሲወጋ፥ ከየብልጭታው ውጋጋን

የሰው የአራዊት የአእዋፍ፥ ውስብስብ ነገደ ጉንዳን
ሲነሣ ሲሮጥ ሲደፋ፥ ሲያጋድል ሲያዛባ ሚዛን
በማይመጠን ታላቅ ኃይል፥ በተፈጥሮ ግዙፍ ሥልጣን
ሲፍተለተል ይወለዳል፥ ሳይነቃ ይወድማል ይባላል
ልደቱ ዕድሜና ሞቱ፥ አለማቋረጥ ይጓዛል፥
ይኸ ይሆን አልፋ-ኦሜጋ? ይኸ ይሆን አስቀድሞ ቃል? ....
ያንቺሳ ምሥጢር ምንድነው፥ ቢራ ቢሮ እንወያይ
አንቺ የዕፀዋት አዋዋይ
ከፀደይ ጋር ፀደይ መሳይ
ከአበባም አበባ መሳይ....
ምን አለበት ላንዲት ሰሞን
ቢራ ቢሮ እኔ አንቺን ብሆን
በፍስሃሽ ብጥለቀለቅ፥ ብነግሥባት ባንቺ ጽዮን?
ጸጋ ሞገስሽን ለብሼ፥ እኔ ባንቺ ስም አልፌ
እኔ ባየርሽ ሰፍፌ
እኔ በአክናፍሽ ክንፌ
ምን አለበት ቢራ ቢሮ፥ .... አንቺ ቀለም ለበስ ቅጠል
የብርሃን ጮራ ጠለል
ተወርዋሪ ሚሳይ መስል፥
ምነ አለበት ቢራ ቢሮ፥ ዕድልሽን እኔ ብታደል? ....
ትንኞች፥ ዝንቦች ያሙሻል
ወረተኛ ነሽ ይሉሻል፤



ከአበባ አበባ መክነፍሽ
ከፀደይ በጋ መዝለቅሽ፥
ከሾህ፥ ከጉድፍ ስትስቂ
ከየስንጥሩ ስትወድቂ
ስትሳዳሪ፥ ወግ ስትነጥቂ
እያወቅሽ እንዳላዋቂ
የወረት ነው ብለውሻል፥ ቢራ ቢሮ ተጠንቀቂ።
የበጋው እንኳ ግድየለም፥ የሀጋይ አሰድ አሳቱ
ቢያነድሽ፥ ቢያክነፈንፍሽ፥ ቢያጤንብሽ ትኩሳቱ
ተፈታትኖሽ ነው ፍትወቱ
አለውልሽ መዋተቱ
ከጉድፍ ጋር መጋጨቱ።
ምነው ታድያን ቢራ ቢሮ፥ በዝንቦች ወራት በበልጉ
አበቦች ሲጠወልጉ
መስኩ ቦዘን ሲከናነብ፥ በትንኝ ጪስ ሲታፈን
አረንጓዴው ሲገረጣ፥ ያሸበረቀው ሲሸፈን
ፀሐይ የኀዘን ማቅ አጥልቃ፥ በጉም በርኖስ ስትጻፈን
እንደ ደስታዋ ጊዜ፥ መከራዋን ሳትካፈይ
ጭንቋን አብረሽ ሳትቀበይ
ከትንኝ ጋር ስትጋፊ፥ አልቀመጥ ብለሽ አርፈሽ
ይኸው አጉል ስም ተረፈሽ።
ቢራ ቢሮ ተናገሪ፥ ሞያው እንዲህ ነው ባንቺ ዓለም

ከፀደይ የፀደይ ቀለም፣ ከበልግም የበልግ ቀለም
ከአበባውም፣ ከጉድፉም፣ ከትንኙም መስሎ መግጠም?
ለካ እንዲህ ነው ያማርሽባት፣ የሕይወትን አገም ጠቀም
ቢራ ቢሮ ሆኖ እማይበር፣ ፀደይ ሆኖ የሚዘልቅ የለም?!
ላንቺ ይብላኝልኝ እንጂ፣ ለኔስ ክረምት ደረሰ
በሰማያት ዕንባ ምድርን፣ ሊጠርግ እያጓበሰበሰ፣
አበባውን እንደጉድፍ፣ ጉድፉን ከዝንብ ጋር ሲያስስ
ሁሉን እኩል ሲያግበሰብስ
አጥርና ጐጆ ሲድስ
ሜዳውን በደለል ሲምስ
ግንዱን በዶፍ ሲገረስስ
ክረምት አያ እናት አይምሬ፣ ማመዛዘኛም የለህ ወይ?
ጉድፍ፣ ጽጌ-ረዳ፣ ዐደይ
ማንንም ከማንም አትለይ?
አየን የሁሉ እኩል ቤት ወግ
መደምሰስ፣ መገርሰስ፣ መጥረግ!
ቢራ ቢሮ እንዴት ነበር፣ ያንቺስ የክረምቱ ውሎ?
መቸስ ለይቶ ፈጥሮሻል፣ ከሁሉ አድረሽ ኑሪ ብሎ
የመመሰል ሞያ ክኖ፣ የመጠጋት አቅል አድሎ ....
ክረምሽ አሉ እንደ ሌት ወፍ
ተለትመሽ ከቤት ክፈፍ፣
እንደ ግንደ-በል ምስጦች፣ ከምሰሶ ተገን መግባት



በየጣራ እንደ ሽረሪት፣ በምድሿ እንደ እሳት እራት
ዕድልሽ የዋዛም አደል
ከፉ ፈተና ነው መምሰል ....

በርቺ እንግዲህ ቢራ ቢሮ፣ ክረምት ላንች ብቻ አለፈ
መስሎ አላድር ያለውማ፣ በጐርፍ ዘቅጦ ጐረፈ
ለካ ምሥጢርሽ ይኸው ነው። በቃኝ እኔም አልሳሳት
ሲነገር እንደሰማነው፣ ከየብልጭታው ውጋጋን
የሰው፣ የአራዊት፣ የአእዋፍ፣ ውስብስብ ነገደ ጉንዳን
በማይመጠን ታላቅ ኃይል፣ በተፈጥሮ ግዙፍ ሥልጣን
ሊፍተለተል ይወለዳል፣ ሳይነቃ ያልፋል ይባላል
ልደቱ ዕድሜና ሞቱ፣ አለማቋረጥ ይጓዛል
ይኸው ነው አልፋ-ኦሜጋ? ይኸው ነው አስቀድሞ ቃል?
በኀሊና መሳከሩ፣ ላይሆን የቆሸት ሕመም ማብቀል
በአለብላቢት መለብለቡ፣ ልቦናን በሣግ መቀቀል
ይሁን ያለን ዲበ-ኩሉ፣ የኑሮ ግማደ መስቀል
ለካ እንዲያው ነው መርበትበቱ፣ ሥረ-ቃሉ ላይነቀል? ....

በይ ብር በይ ቢራ ቢሮ፣ ክረምት ላንቺ ብቻ አለፈ
ሌላው በጐርፍ ጐረፈ
ሞተ፣ በተኛበት ረጋ ....
ፀደይ ላንቺ ብቻ ነጋ
ሽር ብለሽ መንቆጥቆጥ ነው፣ ከዚያም፣ ከዚያም፣ ከዚያም ሠምሮ

አወቅሁብሽ፣ ነቃሁብሽ ፣ አንቺ ሕይወት ቢራ ቢሮ ....
ቀናሁ መሰል አንች ወላዋይ?
ነይ ብር በይ እንወያይ
አንቺ የዕፅዋት አዋዋይ
ከፀደይ ጋር ፀደይ መሳይ
ከአበባም አበባ መሳይ ....
ምን አለበት ላንዷት ሰሞን
ቢራ ቢሮ እኔ አንቺን ብሆን?

፲፱፻፹፩ - ስድስት ኪሎ



## መሸ ደሞ አምባ ልውጣ!

እምባ ወጥቼ እኩለ-ሌት፣ ስለት ገብቼ በስሟ
ከርሞ ሰይጣን በሷ አስቶኝ፣ ልገላገል ከሕመሟ
ጠበሏ አፋፍ በጨረቃ፣ ደጋግሜ፣ ማሕሌት ቆሜ
ሆዴ ቃትቶ ባር ባር ብሎ፣ እርቃኔን ከሷ ታድሜ
ደጀ ሰላሟን በአራት እግር፣ ተንበርክኬ ተሳልሜ
በሥጋዬ እሚነደውን፣ በጸሎት ላቤ አጣጥሜ
እፎይ ብዬ አመስግኜ፣ ውዳሴዋን ደጋግሜ ....
ገና ከደጅዋ እልፍ ሳልል፣ ደሞ ይምጣ የቁም ሕልሜ?
ሌት በጥምቀቷ የነጣው፣ ነጋ፣ ደፈረሰ ደሜ።
ለሷ እንጂ ለኔ አልያዘልኝ፣ አዬ የስለት አታምጣ!
በውጣ ውረድ በጠበል፣ ባሣር ወዜ ቢገረጣ
ልክፍቷ እንደሁ አልለቀቀኝ፣ መሸ ደሞ አምባ ልውጣ!

፲፱፻፺፩ - ቢሾፍቱ

# ማነው .... 'ምንትስ'?

ያው መቸም እኔም እንደሰው
አንዳንዴ፣ አንዳንዴ ብቻ፣ ሕሲናዬን እውነት ሲያምረው
ሰብሰብ ብዬ እማሰበው
"ቀድሞስ ቢሆን ለኔ ብጤ፣ ለኔ ብጤ የሔዋን ዘር
አዳሜ በኔ ላይ በቀር፣ ለኔ መስክሮ አይናገር"
ብዬ ከልቤ ለማክር
እኔው ከኔው ስከራከር
ተጨብጨ እማብላላው
ያው መቸም እኔም እንደሰው
የሐቅ ራብ ነፍሴን ሲያከው
ልቤ ልቤን ሲሞግተው ....
"እውነትስ ምንትስ ማነው?"
እያለ ነው። ....
ያም ሆኖ ነገሬ ከልብ
ያልወጣ ነውና ለሕዝብ
ለማንም ያልተገለጠ፣ የራሴ ድብቅ ሱባዔ
ልቤ ከልቤ ጋር ብቻ፣ ያረገው የዝግ ጉባዔ
ከቶ የናንተን ዳኝነት፣ አልጠይቅምና ሰሙኝ
ፋይል ከፈች እንዳትሉኝ። ....
ያው ብቻ በዘልማድ ሕግ፣ በእንቶ-ፈንቶአችሁ ልረታ ....



እውነቱ ከእውነት ተፋጭቶ፣ ሐቅ ሆኗልና ሽውታ
ስለዚህ አንዳንዴ ብቻ፣ አልፎ አልፎ ብቻ ላንዳፍታ
አሳቤም ሥጋዬም አብሮ፣ ትንፋሼም ሲያገኝ እፎይታ
ምንትሶች ለምትሉን፣ የለንምና ጸጥታ
ከዚያ ከሌት ውጣ ውረድ፣ ከቀን መኝታው ድውታ
ላመል ታህል ብቻ ድንገት፣ ለሃሳብ ንቃት ለትዝታ
ገለል ቀለል ሲለኝ፣ ከስንቱ ሆይታና ዋይታ
'ከዳር ዋጋው ካንድ ጊዜው'፣ ከሂሳብ ዛቻው ቆይታ
ከግራ-ማ-ፎን ቀረርቶው፣ ከድም-ድሙ ካካታ
ከሙዚቃው ሆያ ሆዬ፣ ከናላ-ወቀጣው ፋታ
ከዳንኪራው ውትር ግትር
ከመጠጡ ብዥ ድንብር
ትንሽ የሕሊና ሰላም፣ አገኘሁ ስል .... የሚለኝ ቅር
እንደገና ለብቻዬ፣ የልቤን ቁስል የሚያጭር
አለብኝ የሐቅ ብትር
ነፍሴን ከስሶ እሚያከራክር
እንደዛር እሚጐነትል፣ ሐቅ እንድጠይቅ የሚያስጥር፣
ያራቡኝን፣ ያጠሙኝን፣ የነሱኝን የሐቅ ዕድር
እንድጠይቅ፣ እንድጠይቅ፣ የሚያረገኝ እርር ክርር
ነፍሴን ከልቤ እሚያሟግት፣ በሐቅ ራብ እለካጣጥር

መንፈሴ ውስጥ የሚያቃጭል
'እውነትስ ማነው ምንትስ?'፣ እስቲ እንጠያየቅ የሚል ....
ሕመም አለኝ፣ .... ይኸም ሆኖ፣ እግዜር ያሳያችሁ ላልል
ለይታችሁ አጥራችሁኝ፣ ከዳኝነታችሁ ባሕል
ከፍርድ አደባባይ ክልል፣
ለኔ ከቶ ላታውቁልኝ
ነውር በቀር ላታዩብኝ
ጠር በቀር ላታስቡብኝ
የሕሊናችሁን በደል፣ በኔ ለምትወጡብኝ
ምንትስ ከማለት በቀር፣ ሌላ ምን ላታስገኙልኝ
መቸም ቢሆን እኔ እናንተን፣ እግዜር ያሳያችሁ ላልል
እዘልቃት እንደሁ ነው እንጂ፣ ከልቤ ጋር ሳብሰለሰል
ምንም! ቃል ለምድር ለሰማይ
ያሳያችሁስ ብላችሁ፣ አየን ላትሉ አለብካይ ....
መሃላ አለኝ፣ ትናንት እንኳ፣ የእህቴ ልጅ እንኳ ትላንት፣
የሥጋ የዘመድ ያጥንት፣ የደም መተሣሠር ገፍቷት

አገር አቋርጣ ልታየኝ
ልታጫውት ልትጠይቀኝ
ልታዋየኝ ልታቀርበኝ
ችግርሽ ገባኝ ልትለኝ
ከዘመድ ልትደባልቀኝ
የወግ መሰላል ልትሆነኝ



ካገር ልታመሳሰለኝ
አዲስ ዘዴ ልታሳየኝ
እንደመጻሕፍቷ ብርሃን፣ አርቃ ልታሳሰበኝ
በመንፈስ ውድቀት እንዳልርቅ፣ በርቺ ልትል ልታቀርበኝ
መጣች ብዬ ሳሳስቃት
ሳጕርሳት ስገባብዛት
ልቤ ፈክቶ ሳዳምጣት፣
....የእህቴ ልጅ እንኳ ትላንት
ለካ እሷስ 'ቦይ-ፍሬን' ብጤ፣ 'ዳር-ልግ' እምትሉት ሽቷት
ምሥጢር የሚያመሣጥራት
አሳስቧት፣ አስኝቷት
የሚያሳውቅ፣ የሚያስተምር፣ ልቦና የሚከፍትላት
ለጊዜው፣ ለጊዜው ብቻ፣ በኔው ቴፕ እያራመዳት
በኔው መጠጥ እያጣጣት
በኔው ሶፋ እያስጠናት
ችግሯን ከተረዳላት
ኋላ .... ደብተር መግዣ እሚላት
አስኝቷት፣ አሳስቧት
ነበር ለካ የደከመችው
ያገርን የወግ ድልድል፣ ድንበሩን የዘለለችው
የባሕሉን የሥርዓቱን፣ ክልል የተሻገረችው
የሥልጣኔ መጽሐፏን፣ ድርሳኗን የዘረጋችው ...

እና አንዳንዴ፥ አንዳንዴ ብቻ፥ እኔው ከኔው ስመካከር
ከልቤ ጋር ስከራከር
ያው መቸም እኔም እንደሰው
የሐቅ ራብ ነፍሴን ሲያመው
እኔንስ ያሉትን አሉኝ፥ "ግን የእውነት ምንትስ ማነው?"
እያልኩ ነው።
ይህ ነው አንዳንዴ እሚያጽናናኝ
ከሃሰት ሃፍረት የሚያዋጣኝ
ከንፈሩን ለሚመጥልኝ፥ ለሚያዝንልኝ እንዳዝንለት
ከንፈሩን ለሚነክስብኝ፥ በሚያዝንብኝ እንዳዝንበት
ለወረት ይፍታሽ ስሚለኝ፥ ወረት ይፍታህ እንድልበት
በሚያሾፍ እንዳሾፍበት
በሚስቅ እንድስቅበት
በቀን ለሚንበላጠጡ
በሌት ለሚብለጠለጡ ....
እንደቀንድ እውጣ ሰንኮፈን፥ እንጭጭ ሕሲና ያወጡ ....
የሴቶች አብሮ አደጎቼም፥ ባሎች እየፈረጠጡ
በጭስማ እየወጡ፥ እያዋጡ እየዋጡ
ሁሉም በተራ ከመጡ
በወሬም በማሽቃበጡ
በኔው ሥራ እኔን ሲበልጡ
ሴቶቻቸው ፈንታቸውን፥ ከኛው ጋር ሲበላለጡ



ስይሰሙላ ለወግ ብቻ፥ እኛኑ እያሽሟጠጡ
ስልካቸውን መዋዋያ፥ እያረጉ ቢያሽቃብጡ
ቢሮአቸውን ሱቅ እድርገው፥ እየዋሉ ቢጋለጡ
ያው አልፈው በወረታችን፥ በእንጀራችን ላይ በመጡ
በገንዘቡም በሌላውም፥ ስጦታ እየተሰጣጡ
በምሥጢር ሲቀማመጡ
ባልና ሚስቱ በገሃድ፥ በንግዳችን በገቡብን
ገቢያችንን ወስደውብን
ስሙን ብቻ በተውልን ....
በዚህ ላይ ጩኸታችንን፥ ጭምር ነጥቀው ሲጮኹብን
መልሰው ደሞ ሲያዝኑልን
ለወግ ሲመጻደቁብን ....
ሕሊናቸውን ባይሹት፥ ኀዘን የሚሹት እነሱ
ለሰባት እምነት ሲምሉ፥ በሰባት ምላስ ሲያወሱ
ባንደኛው ሲነካከሱ
በሌላው ሲሞጋገሱ
በሦስተኛው ሲካሰሱ
ሌት ዓይኑን ላፈር ያሉትን፥ ሳይነጋ የሚያወድሱ
እነሱን አርጐብን ጨዋ፥ የሸንጐ የባሕል አዋይ
የሥነ-ሥርዓት ደላዳይ
መራጭ ቆራጭ ቀናን ከአባይ
ጨዋ መሳይ፥ ንጹሕ መሳይ

ከኔ ምንም ሳይሻሉ፥ ደሞ እኔን ምንትስ ባይ!

"ከሌባ ሌባ ቢሰርቀው

ምን ይደንቀው" እንደሚባለው

እኔንም የሚያስደንቁኝ

ከኔ አንሰው እኔን ሲያወግዙኝ፤

በገዛ ስማቸው እኔን፥ ባፍ ሙሉ ምንችስ ሲሉኝ፤

ይደነቅላቸው እንጂ፥ ያም ቢሆን በቃንጣይሉ

ወኔአችንን ካልበከሉ

በሥጋችን እንደጣሉን፥ መንፈሳችንን ካልጣሉ

ቅስማችንን ልባችንን፥ ሌት-ተቀን ካላቃለሉ

ዓሜን ብለን እስክናምን፥ ምንትስ ነን በሉ እያሉ

ሲያሽቃብጡ ሲያዳልሉ....

ስንቱን በኛ ላይ ማጋፈር፥ ለይስሙላ መካካሻ

ወይ ለንዴት መቀነሻ

ወይ ለበቀል ማስታገሻ

ወይ ለመሣላ ማፍረሻ ....

ኧረ ስንቱ፥ ሞልቶ ስንቱ፥ ብኩን የመንፈስ ምንትስ

ለሥጋውም አብሮን ወድቆ፥ ዳግም በአእምሮው ሲረክስ

በልቦናውም ሲሴስን፥ በሕሊናው ሕግ ሲድስ

'ፍራ-ደሜ' ነው እያለ፥ የኔኑ ደም ሲያልከስክስ

በቃሉና በመንፈሱ፥ ወድቆ ደቅቆ ሲበሰብስ

ቴህ ወዲያ ማነው ምንትስ!



ከሥጋው አልፎ በአእምሮ

ዘሙቶ ወድቆ ተሰብሮ

ከኔ እኩል ለገንዘብ ሰክሮ

በቃልና ባንደበቱ፥ ከኔ ይበልጥ አመንዝሮ

ገበናው እንዳዋጅ ቅዳጅ፥ ከቤት ሾልኮ የትም ሲታይ

ልቅሶ ላይ ሆነ አደባባይ

ጕረቤት ሆነ ገበያ፥ ቤተ-ታቦት ቤተ-ጠንቋይ

በመኪና ወይ በጫካ፥ በጭለማ ወይ ጣይ ለጣይ ....

ዝም ብንል ብናደባ፥ ዘመን ስንቱን አሸክሞን

የጅልነት እኮ አደለም፥ እንድንቻቻል ነው ገብቶን

ገልጦ ታይቶን ሁሉ ታውቆን

እንጂ፥ አደለም ተሰኖን

ጨዋ እሚባል ማን አለና፥ ደሞ ማን ምንትስ ሊሆን፥ ....

  እማማና አባባ እንኳ፥ የልቤን የምነግራቸው

  ምንም የማልደብቃቸው

  አንዳንዴም ሲቸግራቸው ....

  ገንዘብ ቋጥሬ ይዤላቸው

  መጠሪያ የሚሆናቸው

  ድካምና ሽምግልና፥ ጕረቤት ፊት ሳይጥላቸው

  ጕጆ ልቀልስላቸው

  የግብር ልከፍልላቸው

ሄጄ፥ ዘመድ አዝማድ መሃል፥ ተፈራርቀው ሲመርቁኝ

ጉልበታቸውን እንደሳምኩ፣ ቡራኬአቸውን ሳይሰጡኝ፣
…. አባባና እማማ እንኳን፣ ካንድ ልቤ …. እኩል የሚያውቁኝ
ዝቅ እንዳልኩ ሳልነሳ፣ ተንበርክኬ ሲመርቁኝ
እዚያው ተጠቃቅሰው አሙኝ፣
በዓይንና በግንባር ጥቅሻ፣ ከዘመድ አዝማድ ጋር በሉኝ፣
ጉድ ብለው እያስታወሱ
በገጻቸው እያወሱ
ከንፈር እየተናከሱ
በዓይን እየተጠቃቀሱ
የልጅነቴን ሳይረሱ
ከጐረቤቱ መሃከል፣ እነማን እንደሰመኑኝ
እምቢ ሰልም የሰደቡኝ
እሺ ሰል ጉድ-ፈላ ያሉኝ
ወይም ከኔው አድረው ውለው፣ ኋላ ያች ምንትስ ያሉኝ
እነማን እንደነበሩ፣ ሁሉንም አስታውሰው አሙኝ፣
በጐረቤቱ መሃከል፣ እንዳችም ወሬ ሳይረሱ
በዓይን እየተጠቃቀሱ
ከግራቸው ሥር ሳልነሳ፣ ቡራኬውን ሳይጨርሱ ….
አሙኝ
ሥጋዬን ከተፉኝ
ከዘመድ አዝማድ ጋር በሉኝ።….

ታዲያን እኔንም እንደሰው



አንዳንዴ፣ አንዳንዴ ብቻ፣ ሕሊናዬን ሀቅ ሲያምረው
ዳኝነት የእግዜር ነውና፣ ልቤን ፍረደኝ የምለው
“እውነትስ ምንትስ ማነው?”
እያልኩ ነው። ….
ግን አንዳንዴ እምዘነጋው፣ ሳሰታምም የሰሜን ቁሰል
እሰነሱም የለኝም ብል
ቢያሙኝ ነውና የባህል ….
ምነው በተለይ በነሱ፣ ብቻ ለምን ይቅርባቸው
እያልኩም ነው።
…. ደሞ ያባባም የእማማም፣ እልፍ ቀርቶ ደሞ ዛሬ
እንዲህ የስም ማቅ ሰብሼ፣ ነፍሴን ጭምር ተዘክሬ
ተገንጥዬ ተነውሬ
እይሰበሩት ሰብራት፣ የሰም ቅጭት ተሰብሬ
ክብሬን አንገቴን ቀብሬ
አንድ ልጄን አሰተምሬ
አሰጨርሼ ተቸግሬ
እልፍ፣ ‘ግራ-ዱኤት’ ሲሆን፣ ደሞ አዲስ ችግር ያሳየኝ!
የሥርጉ ዕለት ከእጮኛው ጋር፣ ጠርቶ እንዳያስተዋውቀኝ
….. ማን ይበለኝ፣ ምን ይበለኝ
ስም አጠረው፣ ስም አጠረኝ።
እኔን፣ ልጄን፣ ግራ ይግባኝ!
እኔን እናትክን ስም ይጥፋኝ፣

አትጥራኝ አልኩት፥ አትጥራኝ
አታስታውሰኝ አልኩት እርሳኝ ....
ይህም ሆኖ እኔ ልጄን፥ እግዚአብሔር ያሳይህ አልል
ቢከብደው ይሆናልና፥ ማለፍ ከትምህርቱ ከልል
ከሥልጣኔውን ኬላ ደፍ፥ እሱም ከሱ ዘመን ባህል፥
እግዜር ያሳይህም ብለው፥ ቢጥርም ሊያሳየኝ ላይችል
በእውቀቱ ብስለት ተቆርጦ፥ ተበጣጥሶበት የኔ ውል
እንደገና የሱም ዘመን፥ አዲስ ባወጣው ድልድል ....
ታጥሮ የኔ ዕድል ከሱ ዕድል፥
እና ምንም ቢሆን ልጄን
ፍቅሬን የመጨረሻዬን
ስም ያጣልኝን እንድዬን
ባላዋሰኝ ውል እንዳልውል
ያውጣህ እንጂ ከዚህ እከል
ይኸው ቃል ስምድር ለሰማይ፥ እግዜር ያመልክትህ ላልል!

ብቻ እንዳንዴ እየረሳሁት
እንዳንዴ እኔም እንደሰው፥ ልቤን እያስዘነጋሁት
ለትንፋሽ ያህል ለእፎይታ፥ ፋታ ብጤ እየሰጠሁት
ከዳንሱ ዳንኪራ ርግደት
ከሙዚቃው ዋይታ ግዝፈት
ከፍካሬ ኢየሱስ ጥሪ፥ ከፋንፋር ነጋሪት ግለት



ከሃሳዊ መሲሃን ጩኸት
ከነጉግ ማንጉግ መለከት
እኔም እንደሰው እንዳንዴ፥ ልቤን እያስዘነጋሁት
ሕሊናዬ እያመለጠኝ፥ ያ በመጠጥ የሸፈንኩት
በውስኪ እንፋሎት ያፈንኩት
በዕድሜ ቁሰል የጠቀምኩት
ተግ ይልና፥ ብቅ ይልና፥ በገሃድ እያስተዋልኩት
የሐቅ ራብ እንደፈራሁት
ግትር ብሎ ግንባሬ ላይ፥ በቁም እየተፋጠጥኩት
ልቤ ልቤን ሲያማክረው
"በቁም መረሳት፥ መጥፎ ነው!"
እንኳ ቢለው
ዳኝነት የእግዜር ነውና፥ እኔም ፍረደኝ የምለው
"እውነትስ ምንትስ ማነው?"
እያልኩ ነው።

፲፱፻፹፫ - አዲሳባ

## 'እከካም ተማሪ'

አንባቢው ጀመረ፣ ደብተሩን ጨበጠ፣
ገጽ አገላበጠ፣
በቃላቱ ምትሀት፣ ሃሳቡ ተዋጠ፣
አንባቢው ጀመረ፣
እኔም ቢራዬን ያዝኩ፣ አበባ አየሁ አለ፣
እያሰላሰለ፣ ይተች ጀመረ፣
ያነብ ጀመረ፣
እኔም ቢራዬን ያዝኩ፣ እየተመቻቸሁ፣
ሃሳቤን ጠቅልዬ፣ እየተጐነጨሁ፣
ትዝታው ፈለቀ፣ እያሰላሰለ፣
አበባ አየሁ አለ።
ታምሜ ተኝቼ-ሆስፒታል ገብቼ
አበባ አየሁ አለ፣
አንዲት ውብ አበባ፣ ስም ያወጣሁላት፣
ውብነሽ እሰኝቼ፣ ብቻዬን ተኝቼ
አበባየሁ አለ!
እንደእንቁጣጣሽ ቀን፣ እንደመስቀል መዓልት
ስም ያወጣሁላት፣ እንደ አበባ ወራት፣
አበባየሁ አለ። ብቻዬን ተኝቼ፣
ሆስፒታል ገብቼ።



እኔም ቢራዬን ያዝኩ፣ በሃሳቡ እየተያዝኩ
እንደሱ እያስታወስኩ፣ እንደሱ እያስተዋልኩ፣
እንደሱ ትዝ አለኝ፣ እንኳን እማውቃቸው፣
እማላውቃቸውን፣ ጭምር አስታውሰኝ፣
አበባ አየሁ ሲለኝ፣ ግጥሙን ሲደረድር፣
ቅኔ ሲደረድር፣
እማላውቃቸውን፣ ጭምር አስታወሰኝ፣
ቢራዬን እንደያዝኩ፣
እንደሱ አያስተዋልኩ።
እኔንም ትዝ አሉኝ፣ በድምፁ ተሰሙኝ፣
በከንፈሩ ሳሙኝ፣ በዓይኖቹ አልፈው አዩኝ፣
ጐንጨት፣ ጐንጨት እያልኩ፣ እንደሱ አያስተዋልኩ።
እኔንም ትዝ አለኝ፣
እንኳንና እማውቀው፣ እማላውቀው ታየኝ፣
በከንፈሩ ሳሙኝ፣
በዓይኖቹ አልፈው አዩኝ፣
በድምፁ ተሰሙኝ።
ዳባ የለበሱ፣ አቆማዳ የያዙ፣
በትረ-አሮን፣ መቋሚያ፣ የተመረኮዙ፣
ከከ የወረሳቸው፣ ከቶ እማላውቃቸው፣

በድምፁ ተሰሙኝ፣ በዓይኖቹ አልፈው ታዩኝ።
ደሙ የቆረቆዘ፣ ወዙ የቆረቆዘ፣
በትረ-አሮን፣ መቋሚያ፣ የተመረኮዘ
ዳባ የለበሰ፣ አቆማዳ የያዘ፣
ልብሱ የታረዘ። ዳባ ያጠለቀ፣
በርኖስ ያጠለቀ፣ እከካም ተማሪ፣
አንጀቱ የራቀው፣ በራብ የደቀቀ፣
ታየኝ በአንባቢው ዓይን፣ ግጥሙን ሲደረደር፣
በድምፁ ተሰማኝ፣ ሳመኝ በሱ ከንፈር።
ያ ለማኝ ተማሪ፣ እከካም ተማሪ፣
በሱ ተመስሎ፣ ባንተ ተመስሎ፣
እሱ ኖሯል ኗሪ፣
እሱ ኖሯል ቀሪ።
በኛ ተመስሎ፣ ባንተ ተመስሎ፣
ዳግመኛ ተፈጥሮ፣ ሁለተኛ በቅሎ፣
አበባው ሲዘራ፣
የግጥም አዝመራ፣
የቅኔ አደባባይ፣ ገበያው ሲደራ።
አንባቢው ቀጠለ፣
እያስላሰለ፣
አበባየሁ አለ!
"ኢዮሃ አበባዬ፣ መስከረም ጠባዬ!"



ዳባ የለበሰ፣ ማኅደር ያነገተ፣
በጭቶ የነከተ፣ በእከክ የነከተ፣
'እኮ ዘተምህረ፣ ይከውን መምህረ'
አንባቢው ቀጠለ፣
አበባየሁ አለ!
ፊት-ለፊቴም ያለው፣ ጭጭ ብሎ አዳመጠው፣
ዘጉ ቅንድቦቹ
ለዘብ አሉ ዓይኖቹ።
ለሽ አሉ፣ ፀጥ አሉ፣ እርጭ አሉ፣ ተኙ፣
በባሕረ-ሃሳብ ስጥመው፣ ጠልቀው፣ ቀዝፈው ዋኙ፣
በቁም ሕልሙ ምሥጢር፣ ተአምር ሊናኙ።
ወይስ ለሱም ታዩት?
ዳባ የለበሱት።
ጢማሙ ከጐኑ፣ ዓይኖቹን ቀልሶ፣
በከናፍሩ ጫፍ፣ ትምባሆውን ነክሶ
ተከዝም እያለ፣ ፈካ እያለም ጥርሱ
ያንባቢውን ግጥም፣ ላሟው ከነጢሱ፣
እለ ግን አምሳያ፣ በአንባቢና በሱ፣
ግጥሙን ሲደረድር፣ ሲያነብ አንበልብሎ፣
"የባሕር ቅርድዶች፣ የፍቅር ቃጠሎ"
ሲያነብ አንበልብሎ፣ ሲተች ዝግ ብሎ።
ቢራዬን እንደያዝኩ፣ እንደሱ እያስተዋልኩ፣

ያ ባለአቆማዳው፣ እከካም ተማሪ፤
በዚህ ተመስሎ፣
በዚያም ተመስሎ፣
ያ ለማኝ ተማሪ፣ ቅማላም ተማሪ፣
በኔም ተመስሎ፣ እሱ ኖሯል ኗሪ፣
እሱ ኖሯል ቀሪ።
ያ ዳባ ለባሹ፣ እከካም ተማሪ፣
አለ መሃላችን፣ ከኛ ተመስሎ
ምንተ-ማርያም ባዩ፣ የሌለው ማደሪያ፣
አለ መሃላችን፣ በዛሬው ገበያ
በግጥም ድርድር፣ በቅኔ ገበያ፣
በአእምሮ መስተዋት፣ ራስን በመለያ
ራስን በማወቂያ፣ ራስን በመለኪያ፣
በቅኔ አደባባይ፣ በቅኔ ገበያ
በየአንዳንዱ መንፈስ፣ በየአንዳንዱ ማሳ፣
ምሥጢር ሲያቆጠቁጥ፣ ተአምር ሲዘራ፣
አደባባይ ቆሞ፣ ገበያው ሲደራ፣
በየአንዳንዱ መንፈስ፣ በየአንዳንዱ ማሳ፣
አለ ያ ተማሪ፣ አለ ያ 'ኮሳሳ'።
ባንተም በኔም በሱም፣ እየተመሰለ፣
አንባቢው ጉን ባለው፣ እየተመሰለ
ሕልም አየሁ በሚለው፣ እየተመሰለ



አንባቢው ጉን ሆኖ፣ እያለሳለሰ፣
ሕልም አየሁ እያለ፣ ትዝ አለኝ እያለ
የልጅነት ገጹን፣ የልጅነት ወጉን፣
ያን የድሮ ሕልሙን፣
እያለሳለሰ፤
በቅኔው መስተዋት፣ ዛሬ እያስተዋለ
ትዝ አለኝ እያለ፣ ሕልም አየሁ እያለ።
ከሕልሜ ነቅቼ፣ ያለምኩትን ልነድፍ፣
ልቃኘው ቅዠቴን፣ ላስቀምጠው በረድፍ፣
ከሕልሜ ባንኜ፣ ከእንቅልፌ ነቅቼ፣
እርሳሴን መዝዤ፣ ደብተሬን ዘርግቼ፣
የግጥም ድርድር፣ ገበያው ሲደራ፣
ሲደራ - ሲደራ - ሲደራ-
አሁን ያለምኩትን ከሃሳቤ ላውጣጣ፣
ልነድፈው-ልነድፈው-ልነድፈው ስቃጣ
ያን የቅዠት ፍሬ፣ ደብተር ላይ ልዘራ፣
ገበያው ሲደራ፣ ጉባዔው ሲደራ
....ብዥ ይልብኝ ጀመር፣ ሕቅ አለኝ - አነቀኝ!
አልፈጠር አለኝ፣ አልወለድ አለኝ።
ባምጠው ባምጠው፣ አልወለድ አለኝ!
አንባቢው ጉን ሆኖ፣ እያለሳለሰ፣
እያቅበጠበጠው - እያቁነጠነጠው-

እያበሻቀጠው - ላቡ ችፍ እያለ፥
እንደዚያ ሲያወጋ፣ ሕልም አየሁ እያለ
የልጅነት ገጹን፥ የልጅነት ወጉን፥
በቅኔ መስተዋት፥ ሲያስተውል ራሱን፥
ያ ባለ አቆማዳው፥ እከካም ተማሪ፥
"እኮ ዘተምህረ ይከውን መምህረ፥
ብዕሲት እእመረት፥ ተማሪ እእመረ፥"
በሱ ተመሰሎ፥ በዚያ ተመሰሎ፥
ዳግመኛ ተፈጥሮ፥ ሁለተኛ በቅሎ፥
ያ ለማኝ ተማሪ፥ ቅማላም ተማሪ፥
በኛ ተመሰሎ፥ እሱ ኖሯል ኗሪ፥
እሱ ኖሯል ቋሚ፥ እሱ ኖሯል ቀሪ።
ደሞም ጉኔ ያለው፥ ዓይኖቹን አጉልቶ፥
ድምፁን አጎርንቶ፥
ከባለቅኔዎች፥ ራሱን አስተያይቶ፥
በሕይወት ካሉትም፥ ካሱትም በመንፈስ፥
"ቻሌንጅ" ነው አለ፥ እንዴት? ከማ ልነስ?
ራሱን እነጻጽሮ፥ ከነሱ ተዋህዶ፥
ቻሌንጅ ነው አለ፥ ማ ለማን ተዋርዶ?!
ውድድር ነው አለ፥ መዝኖ፥ አስተውሎ፥
እኛን ተወክሎ፥ ራሱን ተወክሎ፥
ተማሪውን መሰሎ፥ ተሜም እሱን መሰሎ፥



ያ እከካም ተማሪ፥ ያ ዘኬ ለቃሚ፥
ያ ዐርብ ሮብ ጧሚ
ያ በተከሲያን ሳሚ፥
እኛን ተመሰሎ፥ እሱ ኖሯል ቋሚ፥
በእንባቢው ዓይን ያየኝ፥
በግጥም ድርድር፥ በቅኔ ገበያ፥
በየእንዳንዱ መንፈስ፥ ተአምር ሲዘራ፥
ምሥጢር ሲያቆጠቁጥ፥ ገበያው ሲደራ፥
ምንተ-ማርያም ባዩ፥ የሌለው ማደሪያ፥
አለ መሃላችን፥ በዛሬው ገበያ፥
በያንዳንዱ ቅዠት በቅኔ ገበያ
በእእምሮ መስተዋት፥ ራሰን በመለያ
ራሰን በማወቂያ፥ ራሰን በመለኪያ፥
በየእንዳንዱ ምሥጢር፥ በየእንዳንዱ ማሳ፥
አለ ያ ቅማላም፥ አለ ያ 'ኮሳሳ'፥
በእንባቢዬ ቅኔ፥ በእንባቢዬ አሰማት፥ በሃሳቡ እንደተያዝኩ፥
ቢራዬን እንደያዝኩ፥ እንጸሱ እያስተዋልኩ፥
ያ ከካም ተማሪ፥ አቆማዳ ያያዘ፥
በትረ-አሮን፥ መቋሚያ፥ የተመረከዘ፥
ያ ዘኬ ለቃሚ
እሱ ኖሯል ቋሚ፥
ዳግመኛ ተፈጥሮ፥ ሁለተኛ በቅሎ፥

እሱ ኖሯል ቀሪ፥ እኛን ተመስሎ፣
ያ እከካም ተማሪ።
እኛን ሆኖ ኗሪ።

ለአንዷት የቅኔ ምሽት - (፲፱፻፺፩)።



## ረሃብ ስንት ቀን ይፈጃል?

ረሃብ ቀጠሮ ይሰጣል?
ወይስ ቀን ቆጥሮ ይፈጃል?
"የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል"
ይባላል፥ ድሮም ይባላል፥
ይዘለዝላል ይከትፋል
ብቻ እስከሚጨርስ ድረስ፥ ሆድ ለሆድ ጊዜ ይሰጣል?
ወተት እንጀት ነጥፎ ሲላብ
ሆድ ዕቃ ደርቆ ሆድ ሲራብ
ተሟጦ እንጀት በእንጀት ሲሳብ ....
የጣር ቀጠሮው ስንት ነው
ለሰው ልጅ ሰው ለምንለው
ላይችል ሰጥቶት ለሚያስችለው
ስንት ቀን ነው? ስንት ሌት ነው? ....
የማዕዱ ወዝ ሳታጥጥ
አድባሩ አብዳ ሳትፈረጥፃ
ጥንብ ሳይተርፋት ሜዳ-ኢይጥ
የቤት ድመት ሳታማምጥ
በእመቤቷ እስከሬን ብካይ
እሷም ዋይ አንጀቷም ዋይ-ዋይ
ውሻም በጌታው ሥጋ ላይ

ቸነፈር በጣሰው ሲሳይ
አይ! ....
ስንት ቀን ትሆን የራብ አዋይ? ....
እስቲ እናንተ ተናገሩ፥ ተርባችሁ የምታውቁ
ከቸነፈር እምልጣችሁ፥ ተርፋችሁ እንደሁ ሳታልቁ
ትንፋሽ ቀርቷችሁ እንደሆን፥ ያስችላችሁ እንደሁ ጥቂት
ቀጠሮ ይሰጣል እልቂት?
ስንት መዓልት? ስንት ሌሊት?
ጥንብ አንሳው ሳይወርድ በፊት፥ ሳይሞዠርጣችሁ ጥፍሩ
በጣረ-ሞት አከናፋቱ፥ እንዣቦ በመቅሰፍት እግሩ፥
አንደበት ተርፏችሁ እንደሁ፥ ሳትነግሩን ከምትቀሩ
ካስቻላችሁ ተናገሩ።
ቆሽት-ሲቃው ሳያጣጥር፥ ሰቀቀኑን ሳያጋግል
እስትንፋስ ስልምልም ሳትል
ቀጠሮ ይሰጣል ረሃብ? ለስንት ቀን ለስንት ያህል?
ስንት ሰዓት ነው የራቡ እቅሙ?
ስኔ ብጤማ ትርጉሙ
የሁለት ፊደል ድምፅ ነው፥ 'ራብ' የሚሉት ከነስሙ
እንጂ የኔ ብጤውማ
የት አውቆት ጠባዩንማ፥
ብቻ ሲነገር ይሰማል
ይህንን ሁለት ፊደል ቃል፥ ....
ቃሉማ ያው በዘልማድ፥ ይነገራል ይሰፈፋል
ይተረካል ይዘከራል



ይደጋገማል ይተቻል
እንጂ እንኳን ጠባዩንና፥ የራብ ዕድሜውን የት ያውቃል? ....
እና እምታውቁት ንገሩን፥ እውነት ራብ ስንት ቀን ይፈጃል? ....
በጣር እፋፍ ላይ ያለህ ሰው፥ ራብ እንዴት ነው የሚያዛልቅ
ለስንት ቀን ቀን ይሰጣል፥ አንደበትክን ሳይሸመቅቅ
ሽረሪት በልሣንህ ላይ፥ የድር ትብትቡን ሳይሠራ
ቁራና ቀበሮ በቀን፥ ከቀየህ ድባብ ሳይደራ
ጥንብ አንሳ ሲጭር ሳይመጣ፥ ቅምቡርስ ከጉጅህ ጣራ
እንደፍካሬ ኢየሱስ ቃል፥ በጣር ምፅአትን ሳትጠራ
እንደበት ሳለህ ተናገር
የምታውቅ የራብን ነገር
እስከሬንህ ከየጥሻው፥ ተርፎ እንደሁ ሳይቀረቀር
ስንት ደቂቅ ስንት ፋታ፥ ቀጠሮው ስንት ትንፋሽ ነበር
ቆሽት አርሮ ሳይፈረፈር
ትናጋህ በድርቀት ንዳድ፥ ጉሮሮህ ሳይሰነጠር? ....
የሆድ ነገር ስንት ያቆያል? ቀጠሮ ይሰጣል እልቂት?
ስንት መዓልት? ስንት ሌሊት?
ስንት ሰዓት ነው ሰቆቃው፥ ስንት ደቂቃ ነው ጭንቁ
እሰቲ እናንተ ተናገሩ፥ ተርባችሁ የምታውቁ

ስንት ያቆያል? ስንት ያዘልቃል? ....
እውነት ራብ ስንት ቀን ይፈጃል?

ጥር - ፲፱፻፹፭ - ዋልዲያ

## ምነው አምቦ?

ምነው አምቦ ....
የደማም አምባዎች ቁንጮ፣ እንዳልነበርሽ የደም ገንቦ
እንዳልነበርሽ ንጥረ-ዘቦ
ዙሪያሽ በምንጭሽ ታጅቦ
በተራሮችሽ ተከብቦ
ከጠበልሽ ሚሳይ ታልቦ
ከአዝርእትሽ ፍሬ ዘንቦ
ከዓመት ዓመት ጤና አብቦ
ሕይወት ደርቶ ሰላም ቀርቦ ....
የአየር ትፍሥሕት እንዳልነበረሽ፣ የዘር ሆነ የእሸት የአትክልት
ከመጫ እስከ አዋሽ እምብርት
ምንጭሽ ሲያጥጥ ሲፍለቀለቅ፣ ከዳንዲ እስከ ዋንጪ እትብት ....
እንዳልነበርሽ የምድር እድባር፣ የዘር ድባብ ያገር ችቦ
ዛሬ እንደዚህ ምነው አምቦ
የቀትር ጥላሽ ተስቦ
የጡቶችሽ ወዝ ተሰልቦ
ውስጥ አንጀትሽ ተለብስቦ
የመዓዛሽ መፍለቅለቂያ፣ መንጸባርቅሽ ተሸብቦ
ተረምርሞ ተተብትቦ ....
ምነው? .... ምነው አምቦ?

፲፱፻፰ - አምቦ



## "እቴቴ ዱብራ እሮሞ"

ለካ እንደትዝታ አስታምሞ
እንደዘነጉት የእናት ጡት፣ ከዘመን ጋር አገግሞ
ምንም ቢርቅ ምንም ቢሸሽ፣ ሕልሜ ከሕልምሽ ተዛሞ
በዓይንሽና በዓይኔ መሃል፣ የሃሰት ሥልጣኔ ቆሞ
ባንተያይ ባንወያይ፣ እቴቴ ዱብራ እሮሞ
እንደልጅነት ሰመመን፣ ለካስ ዕድሜም ያማል ከርሞ።
ተግ ሲል ያንቺ ሽውታ
ብኸ ሲል እንደአድባር ጥሪ፣ እንደተረብ ቅርስ ሽታ
እንደእሳት ዳር ተረት ግርሻ፣ እንደእንቆቅልሽ ትውስታ
የጥቅምት እሸት አወደ፣ ነቃ ደሞ ያንቺ ትዝታ ....
እውድማው ተንደረከከ
ሰንበሌጥ ተንተረከከ
ነይ እከርማ እንነቃቀል፣
ከወንዛችን ሾላ ጠስል
ነይ ጢሎሽ እንንጠላጠል፣
መስኮቻችን ሰብሎቻችን፣ ግጦሾቻችን አባቱ
የእቴቴሽ ላሞች አጋቱ
በሮቻችንም እንጉሩ፣ ኮርማዎቻችንም ነቁ
ጊደሮቻችን ለጥቃት፣ ለይዘታ ለከብደት በቁ
የሁዳድ ድርቆሽ ሠፈር፣ ጥገቶቻችን በረቁ፣

እቴቴ ዱብራ ኦሮሞ፣ እጄን በትዝታሽ ያገርኝ
በሕልም ጣቶችሽ ሳቢኝ
መቸም .... በውን አልሆንሽም፣ እንዲያው በሰመመን ዳሺኝ።
የኔ እጅ እኮ እርፍ አይጨብጥም
የኔ ክንድ ተልም አይተልምም
የኔ ጣት አረም አይነቅልም
በፊደል መፈደል በቀር፣ ጉልጓሎ እኮ አይጐለጉልም
ለስልሻለሁ፣ ሠልጥኛለሁ፣ ሰይጥኛለሁ አልሆንሽም፣
እቴቴ ዱብራ ቦረና
መቸም ሁሉን ቻይ ነሽና
አጥንቴ ከአጥንትሽ ማዕድን፣ ቢመነጭም ተቀምሞ
ከ"ሀና" ከ"አሐዱ" በፊት፣ ከቃል በፊት አስቀድሞ
ዛሬ በዓይንሽ በዓይኔ መሀል፣ አጉል ሥልጣኔ ቆሞ
ሰየጠንኩና አልሆንሽ አልኩ፣ እቴቴ ዱብራ ኦሮሞ፣....
አዎን መቻል ባንቺ ያምራል፣ ያን የትዝታ ሰቀቀን
ያን የልጅነት ሰመመን
ምንም በውል ባንደርስበት፣ ጭላንጭሉ እየታወሰን
ውል ሲል እንዳልጠፋ ቀን
ከዓመት ዓመት ተሽጋግረን፣ አዳዲስ ዘመን ሲሰለፍ
ስንበሌጡ ሲንተረከከ፣ የአዝመራ እሸት ሲትረፈረፍ
የማር እሸት እንቁረጥ ተይ፣ የጥቅምት አበባ እንቅጠፍ
ነይ ሸንዩ አብረን እንግዘፍ



ጣት ለጣት እንቆላለፍ
በዓይን ጥቅሻ እንገራረፍ
ከእውድማችን አፋፍ ለአፋፍ፣ በዳሰሳ እንጠላለፍ
ተይ ፍቅር እንዘራረፍ
በሕልም እንኳ እንተቃቀፍ፣ ....
እቴቴ ዱብራ ቦረና፣ እቴቴ ዱብራ ኦሮሞ
የቀን የጊዜ እንቆቅልሽ፣ በሕልም መርፌ ተጠቅሞ
በየመከሩ ተተልሞ
ከትዝታ ጋር አስታምሞ
እንደዘነጉት የእናት ጡት፣ ከዘመን ጋር አገግሞ
ምንም ቢርቅ ምንም ቢሸሽ፣ ሕልሜ ከሕልምሽ ተዛሞ
በዓይንሽና በዓይኔ መሃል፣ አጉል ሥልጣኔ ቆሞ
ባንተያይ ባንወያይ፣ እንደጥንቱ እንደቀድሞ
እንደልጅነት ሰመመን፣ ዕድሜም እኮ ያማል ደሞ....
አዎን ዕድሜም ያማል ከርሞ ....
"እቴቴ ዱብራ ኦሮሞ።"

ለእቴቴ ዱብራ ኦሮሞ - (፲፱፻፺፪ - ባሌ-ጎባ)

# ምንም አልል

እሺ እንግዲህ በዝምታ
የልቤን ደም ሥር ትርታ
የደቂቅ ዕድሜን ትዝታ
ትር ሰትል አፍታ ለአፍታ
እያዳመጥኩ እያሰታመምኩ፥ ጊዜዬን እያሰላሰልኩ
ሳልናገር ሳልጋገር፥ እየደገምኩ እያሰለሰኩ
ሳልሰለች እየመላለስኩ ....
እሺ እንግዲህ በጸጥታ
የልቤን ደም ሥር ትርታ
የእስትንፋሴን ቃል ጉምጉምታ
ትር ሰልት አፍታ ለአፍታ
ሳልሰለች እየደጋገምኩ
በእግረ ሕሲና እያደቀቅኩ
እየቋጠርኩ እየቆጠርኩ ....
እሺ እንግዲህ አልናገርም
በአንደበቴ አልተነፍስም
በልሳኔ አልመሰክርም
አልልም። ምንም አልልም
እንዲያው ዝም እንጂ ዝም ዝም ....
የልቤ ደም ሥር ሲያቃጭል



ልሳኔን ሲያስነሳ ሲያሰጥል
ቃላቴን ሲቃኝ ሲያጋግል
ትንፋሼን ሲያንር ሲያዳውል
ክል ሲል ትር ድም ሲል
ማዳመጥ ማሰታመም እንጂ፥ ሌላ ምንም ምንም አልል።

ጥቅምት - ፲፱፻፸፫ - 'ፒያሳ'

# አ ዋ ሽ

እስከመቼ ይሆን አዋሽ? ....
አዋሽ፥ የመጫ ሥር ፍሳሽ
የለም አፈርሽ ደም ቅናሽ
የሸዋ የእምብርትሽ ላቦት፥ የምንጮችሽ የምጥ እማጭ
የአለትሽ የተራሮችሽ፥ የጉልጥምጥሚትሽ ፍላጭ፤
አዋሽ ሕመምህ ምንድነው? ሕመምክስ አንተስ ምንድነህ?
ከውህ ወዝ የተለየ፥ መቸስ ልዩ ንግርት የለህ
እንደ-ሴቱ ሽረሪት ፅንስ፥ ራስክን በራስህ ዋጥ ያለህ፤....
እስከመቼ ይሆን አዋሽ? ሲያሳድድ ሲያቅበዘብዝህ
ላትዘልቀው ሳያዛልቅህ፥
አሸዋ ለአሸዋ ድኸህ
ውስጥ ለውስጥ ምስህ ጠልቀህ
የምድርን ማኅፀን ቦርቡረህ
ዋልታዋን ቁልቁል ሰንጥረህ
እናትህ ውቂያኖስ ማኅፀን፥ ላትገባ ትባክናለህ፥....
እስከመቼ ይሆን አዋሽ?.... አዋሽ ቡርቃው፥ መጫ ምንጬ
ዳዳ ፅንሱ ሸዋ ፍንጬ
ውጠህ፥ ተውጠህ እርጬ
የንዳዱ የበረህ ዕጬ
ንግርትህ ምድነው አዋሽ፥ አባ ብቻ አባ እቅጬ?



ዘለዓለምክን ፈስስህ ባታልቅ
ምነው ተስፋ መቁረጥ አታውቅ?
እስከመቼ ይሆን አዋሽ? .... አዋሽ በቃኝ አትል ቆራጥ
ማን ያስተማረህ ፈሊጥ ነው፥ እረህ ለማለምለም መዋጥ
አሻቅበህ ወደ ምሥራቅ፥ ወደ ጅምበር መውጫ መናጥ
ሰምጠህ ልትቀር በሀሩር ማጥ?
አዋሽ፥ ቡቡ ሮሮ ብርቁ
የዘለዓለም ንዳድ ሰንቁ፥
አዋሽ አባ ብቻ ጉዞ
ዘለዓለም ብሶት አርግዞ፥
እነዋቤ ሸበሌማ፥ ሰብረው ውቅያኖስ ሲዘልቁ
እነግዮን ወርደው አልፈው፥ ሱዳንን ምሥርን ሲያጠምቁ
ምነው ያንተ ጉዞ ብቻ፥ በረሃ ላይ መታነቁ?
እስከመቼ ይሆን አዋሽ? .... ወዝክን አሸዋ ሲውጥህ
ደምክን በረሃ ሲመጥህ
ዘለዓለም ሲመዘምዝህ
መች ይሆን በቃኝ እምትል፥ መች ይሆን በቃኝ እሚልህ?
እስከመቼ ይሆን አዋሽ?....
አዋሽ የመጫ ሥር ፍሳሽ
የዳዳ የቱለማ ደም

በረሀ እምትደመደም?

የሰባት ቤት ጉራጌ አድባር

የከረዩ ቅቤና ማር

ፈሰሰህ ለአሸዋ እምትጻር?

እሰቲ አንዴ እንኳ እንደነዋቤ፣ ባክህ ሂድ ውቅያኖስ ግባ

ዘለዓለምክን በአሸዋ ሆድ፣ ተውጠህ ከምታነባ፣

ቆራጡ እንኳ አንተ ነበርክ፣ የጀግኖች መፍለቂያ ኩሬ

የሠንጋ ፈረሰኞቹ፣ የነአርዶፋ ጨንገሬ

የሰንቱ መጠጊያ ዋሻ፣ አዋሽ ደኔ አዋሽ ዱሬ

የጥንተ ፍጡራን መደብ፣ የቅድመ ማልካ ካንቱሬ፣

አዋሽ በቃኝን አታውቅም?

በምድር ማኅፀን ከአድማስ አድማሰ፣ ዘለዓለምክን ሰታዘግም

ወርደህ፣ ሟጠህ፣ ተንጠፍጥፈህ፣ አሜን፣ ታከተኝ አትልም?

መጫ ቋጥሮ ሸዋ ፀንሶ፣ ሰባት ቤት ጉራጌ አርግዞ

ከዳዳ ምንጭ አሩሲ እምብርት፣ ከነቅሪቱ ተጉዞ

ከአላባ ጣፋ ሼህ ሁሴን፣ አዳል ሞቲ ሽሉን ይዞ

ከከረዩ ማታሐራ፣ ከኢቱ እሰከአፋር አምጦ

አሸዋ ነክሶ ቀረ አዋሽ፣ ላይገላገል ሽምጥጦ

እንደወላድ ሳይታረዝ፣ ከነፅንሉ አረህ ሰምጦ

በምድረ በዳ ጉረሮ፣ በረሃ ላንቃ ተውጦ።

እሰከመቼ ይሆን አዋሽ? .... አዋሽ አባ ሮሮ ቅርሱ



የዘለዓለም ንዳድ ጉርሱ፣

አዋሽ ቡቡ በረኸኛ

የአረሀ ሸለቆ በረኛ

የአሸዋ ዋሻ መተኛ

የበረሀ ዋነተኛ

የምድረ በዳ ብቸኛ

የዘለዓለም መንገደኛ፣....

የአበቅቴ መወራረሻ፣ የዕፀዋት ዕድሜ መቁጠሪያ

በፀደይ የአልባሳት ማዕጠንት፣ የዘመን ላቦት ወዝ ማጥሪያ

የእንቁጣጣሽ ማዳበሪያ

የአዝርእት ሰብል ማጥለያ፣

በክረምት የዶፍ ረከቦት፣ የሰማይ ምጥ መቀበያ

የደመና እምባ ማጠቢያ፣ የማዕበል ሰደድ ማከያ

የተራሮችን ለቅሶ ቻይ

የጅረት የምንጮች አዋይ፤....

ጭምት መሳይ፣ ያለዐመሉ

ዘራፍ ባይ በመሰክ ሙሉ፣

አባ ጭራቅ-አክናፍ ቀንዶ

አዋሽ ዘጠኝ ራስ ዘንዶ

ቁልቁል እንደምሽት ጥላ፣ ከሰማየ ሰማይ ወርዶ

ሞልቶ ተንደላቆ ኮርቶ፣ የሰንት ዓለም ምድር ጉርዶ

ቀይ ደመና ተከናንቦ፣ ጋራ እንደአሻንጉሊት አዝሎ

ስንቱን በረት እንደጉድፍ፣ አውተፍትፎ አንጠልጥሎ
አውድማውን አንገዋልሎ
ወርካውን ግቻ አሳክሎ
አመንምኖ አስልሎ
እንደዘጠኝ በገና አውታር፣ በየረድፉ ተሰድሮ
በአገር ምድር ዙሪያ ጥምጥም፣ እንደመቀነት ተቋጥሮ፣
አዋሽ ቁጣ አባ ዱታ
የሰማይ ጥጉ ቱማታ፤
አዋሽ አባ ሻኛው ጋራ
ኩሩ እንደነማታ ሐራ፣
የግርማ ሞገስ መርገፉ
እስከነምድረ-አቀፍ ዘርፉ
አባ ገርሰስ ሞልቶ ደራሽ፣ አባ አደፍርስ አባ ኩርፋድ
ከተፍ እንደመብረቅ ግማድ
በምድር ቁና ድንገት ሲጣድ፣
አዋሽ ንፉግ አባ መዓት
የገጠሬ አታምጣ ምጣት፣
አዋሽ ደርሶ-ቀማው-መብረቅ
አባ መዝረፍ-መውሰድ-መንጠቅ
ግሣንግሱን አግበስብሶ፣ በምድረ በዳ ለማጨቅ
ሀሩር ጉረሮ ለማመቅ
የአሸዋ ሆድ ለመጠቅጠቅ



ሀራም ብሎ አብሮ ለመጥለቅ
እምድረ ከርስ መቀመቅ፣....
እስከመቼ ይሆን አዋሽ? .... አዋሽ ብኩን ምሥጢረኛ
የጠፍ-ፋኖ አባ ብቸኛ
የበረሃ መንገደኛ
የጨረቃ ግዞተኛ፤
ካገር ሞት ወዲያ ላትሞት፣ ካገር ምጥ ወዲያ ላታምጥ
እስከመቼ ይሆን አዋሽ፣ ራስክን በራስህ እምትውጥ?
አዋሽ አባ ሮሮ አገሩ
ያሸዋ ማኀፀን ድንበሩ
የምድረ ዓለም ኬላ በሩ
ኩሩ፣ ብሶት እንደልቡ
ቅምጥል የሸዋ ቡቡ
የሰማይ አድማስ ግድቡ
ንዳድ ስንቁ አረሀ ግቡ፤
እስከ መቼ ይሆን አዋሽ? .... አዋሽ ቡቡ አባ ብሶት
የሰው ችግር ሳይደርስብህ፣ ሳይቸግርህ የእውነት እጦት
ላትዘልቀው ላያዛልቅህ፣ ለማንም የትም እምትሞት?
ታድያ እስከመቼ ነው አዋሽ?
አዋሽ፣ የመጫ ሥር ፍሳሽ፣
የሸዋ የእምብርትሽ ላቦት፣ የምንጮችሽ የምጥ አማጭ
የአለትሽ የተራሮችሽ፣ የጉልጥምጥሚትሽ ፍላጭ፣

እስከመቼ ይሆን አዋሽ፥ ወዝክን አሸዋ እሚውጥህ?
ደምክን በረሃ እሚመጥህ
አጥንትህን ምድረ በዳ፥ ሀሩር እሚመዘምዝህ?
መጫ ቋጥሮ ሸዋ ፀንሶ፥ ሰባት ቤት ጉራጌ አርግዞ
ከዳዳ ምንጭ አሩሲ እምብርት፣ ከነቅሪቱ ተጉዞ
ከአላባ ጣፋ ሼህ ሁሴን፥ አዳል ሞቲ ሽሉን ይዞ
ከከረዩ ማታ ሐራ፥ ከኢቱ እስከ አፋር አምጦ
እንደወላድ ሳይታረዝ፥ ከነፅንሱ አረህ ሰምጦ፥....
በምድረ በዳ ጉረሮ፥ በረሀ ላንቃ ተውጦ፥....
አሸዋ ነክሶ ቀረ አዋሽ፥ ላይገላገል ሸምጥጦ።
እስከመቼ ይሆን አዋሽ፥ ተስፋ መቁረጥን እማታውቅ?
ፈስስህ ተሟጠህ እማታልቅ?
ጉዞህ በረሃ ሲታነቅ
ሀሩር ጉረሮ ሲታጨቅ
አጥንትህ ጉልጥምጥሚትህ፥ እምድረ-በዳ ሲታመቅ
እስከመቼ ይሆን አዋሽ፥ ቆርጠህ ቀይ ባህር እማትዘልቅ?
እስከመቼ ይሆን አዋሽ? ..... መቸም ሌላ ንግርት የለህ
እንደ ሴቴ ሽረሪት ፅንስ፥ ራስክን በራስህ ዋጥ ያለህ፥
እስከመቼ ይሆን አዋሽ? ....

ሰጋማቹ ቃማሊቲ - (፲፱፻፹፬ - አዋሽ)



# እግር እንይ!

አርቀን ማስተዋል ማለት፣ የኛን ሥልጣኔ ድልድይ
እግር ማየት ነው ብለዋል፥ እስቲ እንግዲህ እግር እንይ!
ያባቶችህ ያይን ድንበር፥ ከተረከዘ ሎሚ ሳያልፍ
አንተ ግን ጆቢራው-ዘራፍ
ጠረፍ አይወስንህ ጉብል
ጥሎህ በዘመንህ ዕድል
ዓይንህ ባት አልፎ እንዲዋልል፤
ቴህ ወዲያ ጀግንነት የለ፥ ተዚህ የከረረ ግዳጅ
ባደባባይ የዱር ገደል፥ ስትናደፍ የእግር አዋጅ
ሌሊቱን በየሌት- 'ግስብ'፥ ቀኑን ጭምር በጠራራ
ሲነጋ እንደዉት ጆቢራ
በከተማህ ስታቅራራ
በዕድሜህ መንከራተት ሥራ፥
ካንዱ ቢሮ ሌላው ቢሮ፥ አቦል በረካውን ብለህ
ያገሩን ወሬ ተንትነህ
ተጨቃጭቀህ ተስፋልፈህ
አመሳጥረህ አቆላልፈህ፥ የዚያን ጉዳይ ከዚህ ጉዳይ
ዘጋግነህ በቡና ምገህ፥ አምተህ ደክመህ ስተለያይ፥
በዚህ ብቻ ሳታስቀረው፥ ደሞ አዲሱን የአገር ጠባይ
ከልማድ የቡና ሱስ ጋር፥ የዘመኑን ሳትለያይ

እስቲ ደሞ እራዳ ወጥተህ፣ በከተማው አደባባይ
ያንዷን ካንዷ ዳሌና ባት፣ እግሯን ከእግር ጋር አስተያይ!
ደርቶልህ ያገር ልጅ ቅልጥም
ዳሌው ባቷ እስኪፈረጥም
እየናረ እስኪያስገመግም
አንተ አድፍጠህ ከኋላዋ፣ በዓይንህ ሣግ ስታነፈንፍ
ያቺን ልክፍ ያቺን ንድፍ
እያረክ ስታሾልቅ፣ አንዷ ፈርታ አንዷ ስታፈጥ
ተጠግታህ ባቷ ሲያገምጥ
"ዘራፍ" ቀርቶ ቀልብህም "ውይ!"
እያለ ወኔህ እግር ይይ!

"በሠየጠኑትማ ዘንድ
አንዱም የባላንጣ ዘዴ፣ የባዕዳን ሥውር መንገድ
ዘመናይ ጦር መሣሪያ ነው፣ ታዳጊ አገር ለማንጋደድ
እምነቱን ለማወናበድ
ያንድን ትውልድ የሕልም አቅጣጫ
ወደፊት ሳይሆን ወደታች፣ አመንምኖ ማቀጨጫ!"
ቢልህ ፈጥጦ በግልምጫ
ስኅሲናህ ማጋለጫ
ናቀው እርግፍ እርገህ ተወው፣ ቴህ ብጤው ጋር አትንጫጫ።
ሠልጥነን ንቀን አልፈነው፣ የይሉኝታን መቀጣጫ



የኛ ዓይን የእግር ነው እንጂ፣ በቅቶት ጎሊና መግለጫ።
እርቀን ማስተዋል ማለት፣ የኛን ሥልጣኔ ድልድይ
እግር ማየት ነው ብለናል፣ አሜን በቃን እግር እንይ!

'ለእግረተኞች' - (፲፱፻፹፫ - 'ፒያሳ')

# አንኮበር

አንኮበር የእምሣየስ በር
አድማስ-ፈጠር ኬላ-ሰበር፣
አንኮበር የአምባ ላይ አገር፣
የኮረብታ ዲብ ያድባር ዛፍ
አንኮበር የአለት ላይ አጥናፍ
ስውር ምድር የአድማሳት ጫፍ፣
ባሥራ ሁለት እግር ሺዋ፣ እንዳሞራ ከግንድ አፋፍ
የተንሠራፈትሽ እመቤት፣ እንደታቦት በእምነት ድጋፍ
እንደራዕይ በክንፍ እርካብ
እንደጽላት በአየር ድባብ፣
አቀበት የደመና አዘል
መቀመቅ ዝንጀሮ ገደል
የመዲኖች ጭፍግ ጠሰል።
መንዝህ ይጫ ጌራ ምድር
ሮይ-አንጀትላ ላሎ ቁጥር፣
ከወልቃ በር እስከጠራ
ከደንገዜ እስከአፍቀራ
ባለመጣቀሻ ነፍጥሽ፣ ከካራ-መገን አይራራ፤
ግድም ኤፍራታ አንጾኪያ
የጎበዛዝሽ መፍለቂያ፣



ከተጉለት ዳር እስከ እንሣሮ፣ ከነይገባዋል መግቢያ
ከጉራች በመለስ ማዶ፣ ከሙቀጪት ጅረት ወዲያ
ከጀራ እስከሰላላ፣ እስከጥዱ ሞረት አገር
አንኮበር የአለት ድንበርሽ፣ የምድረ ገጽሽ ፈረፈር
ከመልከአ-መሬት ደርዝ ጋር፣ አምባጓሮ እንዳለሽ ነገር
እንደአዞ መጋዝ መንጋጋ
ከኤፍራታ እስካርጐባ፣ ከቆላ እስከወይናደጋ
ከቤቶ እስከሸበቶ፣ ከጥቁር አባዬ ቡልጋ፣
ከወላስማ እስከንሣሮ
በፈፋሽ አነባበሮ
ዙሪያ ጥግሽ ተተርትሮ
ሽቅብ ቁልቁል ተከርክሮ
ተረተርሽ ተቦርቡሮ
መቀመቅሽ ተሠርስሮ፣
አንኮበር የአምባ ላይ አገር
አድማስ-ፈጠር ኬላ-ሰበር፣
ጠራ-ሲቄ የሠረቁ፣ ጠራ አምሃራ የእምሣየስ
የኩሩ አገር ጋሜ መሰስ
የገር አገር ዳባ ለበስ
የነቸር አምሣ ፈስስ፤

አንኮበር 'ያታከልት' አገር፣ የነእምዬ ምኒሊክ ፍንጭ
የመርድ ዘሜ ቅኔ ምንጭ፣
ለወረ-ሴክ መገናኝ፣ ለነጣይቱ ስያሜ
በመላክ-ሣንቃ ጎዳናሽ፣ ለጎንእደሬ ለጎጆአሜ
ለትግራይ አባት ለአጋሜ፣
በሞፈር ውሀ ክናድሽ
በቀጭኔ ጅረት ሽንጥሽ
ከመገዘዝ ይፋት ግርጌ
የነወልዱን መርሐቤቴ፣ ከአርግቢያት እስከገደልጌ፤
ሰነፍ የዶባ ሰው ሲሉ፣ ላም የጋላሞታ ሲሉ
ከአባ ዳኘው ከሥዕሉ
እንደአባ-ጉራች ጉዲሳ፣ ሺዋን ሲፈጥራት በምስሉ
ኃይለ-መለኮት ፀበሉ
ዕድልሽ ሆኖ ነው ውሉ
"አንኮበር ዕደግ" መባሉ?....
አንኮበር የኬላ ሰበር
ከዓይኔ ከተማ ዳር-አገር
ዘመን ወደ አንቺ ሲሻገር
የነበርሺው ደን ውድማ፣
እትብትሽ እንዲህ ሲለማ
ማማ ምድርሽ መንዝህ ማማ
ጌራ ምድርሽ መንዝህ ይጫ፣ ላሎ ምድርሽ መንዝህ ጭማ
ከማፉድ እስከሮቢት ዳር፣ እስከ ዶቃቂት ከተማ፣
ከሾላ ሜዳ እስከዓዋዲ፣ ከጣርማ-በር እስከአራድማ



ከገፈገፍ እስካንጋቻ፣ ከይፋት እስከወላስማ
ከአውሳ አብዬስ ግሼን ማዶ
በደጋሽ አናት ላይ በርዶ
ጉንሽ ቡልጋ ተገድግዶ
ፍርኩታ ንዳድ ተወርዶ
በከሰም በረሃሽ ነዶ፣
ከሸንኮራ እስከምንጃር
አንኮበር "የመሂዴ" አገር-
ከመረሬ አፋፍ መልሶ፣ እስከጨበሬ ምሑይ ዳር
ከወግዳ ከነባሮ አገር፣ ከታላቅ እምባ ነጭ ሣር፤
አንኮበር የአለት ላይ እጥናፍ
ስውር ምድር የአድማሳት ጫፍ
የኮረብታ ዲብ ያድባር ዛፍ፣
እንደራዕይ በክንፍ እርካብ
እንደጽላት በአየር ድባብ፣
አቀበት የደመና አዘል
መቀመቅ ዝንጀሮ ገደል
የመዲኖች ጭፍግ ጠለል፤
አንኮበር የአምባ ላይ አገኗ
አድማስ-ፈጠር ኬላ-ሰበር
አንኮበር የአምሃየስ በር።

ለተፈራ ደገፌ - (፲፱፻፷፩ - ደብረ ብርሃን)

# ደኅና ዋይ እማማ

እዬ፣ እማምዬ፣ ደኅና ዋይ
ያሳወረሽ አሳወረኝ፣ ቀን የተማባብን ሥራይ።
ዓይኔ ዓይንሽንም አያይ ....
        ያለ ጠር መማረር ዕዳ፣ ወይ ያለባላንጣ ግዳይ
        አቆላልፎን፣ አቆራርጦን፣ በዕንባ በትካዜ ብካይ
        ዘመን የተፋው ሾተላይ፣
        እዬ፣ በቃሽኝ፣ በቃሁሽ፣ ዓይኔስ ዓይንሽንም አያይ....
በቃ እማማ እናት ዓለም፣ እማትነፍጊ እማታቅማሚ
እማታሳጪ እማታሚ
እኔን በራበኝ፣ በጠማኝ፣ እንዲያ አብረሺኝ ስትጠሚ
ምነው ወተቴን ከጡትሽ፣ በጊዜ-ገፊ ታስቀሚ?

        አንጀቴ ያንጀትሽ ቁራጭ፣
        አጥንቴ ያጥንትሽ ፍላጭ
        ሕይወትሽ የሕይወቴ ምንጭ፣ ወዜ የፍቅርሽ ወዝ ምጣጭ
        ማኅፀንሽ የፍጥረቴ አማጭ....
        ከእንግዲህ በቃሁሽ፣ በቃኝ፣ እማማ የነፍሴ ቁራጭ
        ይበጠስ ውልሽ ከውሌ፣ ቃሌ ከቃልሽ ይፈለጥ
        ዓይንሽ ባይኔ ትል ዘነበ፣ በቃኝ፣ የኔው ብሌን ይፍረጥ
        ብቻ በምን አንጀቴ ነው፣ አንጀቴን ባንጀቴ እምቆርጥ?



ይቆረጥ እንበል፣ ይገርለስ?
ይረሳ፣ ይሙት፣ ይደምሰስ?
እርም አፈር እንበል ይበጠስ?
ማኅፀንሽ ጽዋው መረዘኝ፣ ዘጠኝ ወር ያጠባኝ ገንቦ
ጡትሽ የደም ወተት ዘንቦ
ሆድሽ የቁስል ምጥ ታልቦ
ባዳ ቅሪት ተመትሮብሽ፣ የእንብርቴ እልባት ተሰብሮ
ደሜ በፋፋበት እትብት፣ ገፊ ዲቃላ ተቋጥሮ።

በቃ እማማ፣ እማማዬ
መቀነቴ፣ ገበናዬ
በቃሁሽ አድባሬ፣ መቅኔ
ከእንግዲህስ ላንቺ መጥኔ
እዬ ላንቺ እዬ ለኔ ....
ጫቅላዬን ባዘለ እቅፍሽ
ገፊ ጉግ ማንጉግ መፅነስሽ
ጉምቱ ሾተላይ ማብቀልሽ....
አይሆንም አንጂ ከሆነሽ፣ ካለልሽ ካዘለቀልሽ
እግዚአብሔር ያሳድግልሽ።
አዎን፣ ቃል ለምድር ለሰማይ

ደኅና ዋይ፥ በቃ፥ ደኅና ዋይ
ዓይኔ ዓይንሽንም አያይ፤
ከፋም በጐም አናስማ
እንዲያው ደኅና ዋይ እማማ
እናት ዓለም የስሜ አርማ
የሕይወቴ ወዝ የዓይኔ ማማ
እማትነፍጊ እማታቅማሚ
እማታሳጪ እማታሚ
እኔን በራበኝ በጠማኝ፥ አብረሽኝ እምትጠሚ
ጥቃቴን እምትጠቂ፥ ቁስሌን እምትታመሚ
ፍሥሃዬን፥ ፈገግታዬን፥ ሳቄን ብቻ እምታልሚ
አንቺ እማማ
አንቺ የነፍሴ ልብ ዓልማ
የዓይኔ ማማ....
ምነው ጡትሽ ተጣረረኝ?
በጊዜ-ገፉ ለወጠኝ?
እንዴት ይንጠቀኝ ሾተላይ?
ቀን የተጣባብን ሥራይ
ያለኝታ ኅብስተ-መና፥ የወገን የእጥንቴን ሚሳይ
የደሜን ምንጭ የሕይወቴን ማይ
የማኅፀን የእትብቴን አዋይ?....



አዎን፥ ይብቃን እናት ዓለም፥ አንጀቴ ባንጀቴ ይቆረጥ
አጥንቴም በአጥንቴ ይድፈጥፈጥ
ቃሌም ከቃልሽ ይፈለጥ
የዓይኔም ውሃ በዓይንሽ ይፍረጥ
ይረሳ፥ ይጥፋ፥ ይደምሰስ
እርም አፈር እንበል ይበጠስ....
በቃ እማማዬ ደኅና ዋይ
የደሜ ምንጭ የሕይወቴ ማይ
የማኅፀን የእትብቴ አዋይ
አሜን፥ ቃል ስምድር ለሰማይ
ዓይኔ ዓይንሽንም አያይ።

፲፱፻፺፫ ሎንዶን

# ሊማ-ሊሞ

የሰማይ የምድሩ ኬላ፣ የየብስ የጠፈሩ ዋልታ
አይበገር የአለት ጣራ፣ አይመከተው መከታ
ሊማ-ሊሞ አድማስ ሰበሩ፣ በጐማ ፈለግ ይፈታ?
በትሬንታ እግር ይረታ?....
ሊማ-ሊሞ የቁም እርሙ፣ ሰማይ-አዘል ሊማ-ሊሞ
ከንፉ ከነካሰማው ዘሞ
ከጠፈር ውሃ ገድቦ፣ ለየብስ እንደማገር ቆሞ
ተጠማዝዞ ተጠምጥሞ
ከጽንፍ ጽንፍ አረምሞ
ከደባርቅ እስከ አዲ አርቃይ
አለት ከደመና በላይ
አዘንብሎ እንደ ሰማይ
እንደጠፈር ሽቅብ ሲታይ፤
ጉም አጥልቆ እንደቀሚሱ
ፀሐዩን እንዳንገት ልብሱ
ተከናንቦ ተሸላልሞ
ተንደላቆ ሊማ-ሊሞ፤
ጨረር ባደመቀው ጭጋግ
ዙሪያ ዘርፉን እንደጎዳግ
በንዳድ ሀሩር ምድጃ



ፍም አንጥፎ እንደ ሥጋጃ፤
ሰማዩን ቁልቁል ዘንጥፎ
በብብቱ ጉም ታቅፎ
የአድማሳቱን ፍንጣቂ፣ ለእግሩ መርገጫ አርከፍክፎ፣
እንደፍካሬ ኢየሱስ ቃል፣ እንደሙታን የግዞት ሕግ
ተውተብትቦ ተጥለፍልፎ፣ ተቆላልፎ እንደዛር ድግ
በምድር በሰማይ ዳር ድንበር፣ በሕዋው ዓለም ክልል ጥግ
በሲዖል ጠፍር መሰላል፣ የብስ ከጠፈር ታድሞ
ጥጉን እንደራእዩ አውታር፣ ከነአክናፉ ቁልቁል ዘሞ
እንደእንጦርጦስ በር አጥር፣ በአለት ናዳ ተረምርሞ
የጉም ክናዱን እንደጣር፣ ወደ ምድር ማጎፀን ቆልምሞ
እንደባቢሎን ግንብ አጥር፣ ቋንቋ ለቋንቋ አሳድሞ
እልበገር አልደፈር፣ አልሰበር ያለን ከርሞ
ሊማ-ሊሞ የቁም-እርሙ፣ ጠፈር-አዘል ሊማ-ሊሞ
ዛሬ እንደሰለት ሃጅ ፈለግ፣ በግብረ ጉንዳን ተተልሞ
ሰማይ ከምድር ተደላድሎ፣ ተኮትኩቶ ተከርክሞ
በዲማሚት ተፈልፍሎ፣ ድልድይ ይሁን ሊማ-ሊሞ?

ለፈረደ ዘሪሁን - ፲፱፻፷፫ - ተከዜ

# ጎል!

ያንዱ ደስታ ላንዱ ዋይታ፣....
እሰየው ጎል! .... እረገኝ ጎል!
ያንዱ ገነት ላንዱ ሲያል።
እንዲያ ነው ጎል አባ ቁርጡ
ያንን ሁዳድ ሙሉ ጀግና፣ ሲገላግለው ከምጡ። ....
አጫዋቹ ያፉን ፊሽካ፣ ሲነፋ ሲል ገና ሲያሾል
ሠራዊቱ ተሽቀዳድሞ፣ ከቅምጡ ሲኮለኮል
ዓይንና እጁ ከነነፍሱ፣ ብን ብሎ ሲንጠለጠል
ከአራጋቢው ጨርቅ ጋራ፣ ብትን ሲል ሲንጀለጀል
ልቡ ከኳስ ቀድሞ በሮ፣ ሽቅብ ሲጐን ሲሽቆለቆል
በገና እግር የተለጋ፣ የፊኛ ሩር ሲድቦለቦል
በሁለት ማዕዘን መካከል፣ ሾልኮ ተውዘግዝጐ ሲዶል
"ጎል!" ይባላል፣ እንዲያ ነው ጎል!....

ከዚያማ ጎል አባ ቁርጡ
ያንን ሁዳድ ሙሉ ጀግና፣ ከገላገለው ከምጡ....
ምኑ ቅጡ! ምኑ ቅጡ!
ውጥንቅጡ፣ ብሽቅጥቅጡ
የጠርሙስ ስባሪ ጉርጡ
የቡጢው ናዳ የፍልጡ
የተቺ አግቦ ብጥብጡ



የፈላስማው መብለጥለጡ
የታዛቢው ማሽቃበጡ
የእንካ ስላንቲያው ሽሙጡ
የእንካ እንጠጣው ጭልጥልጡ
ያፍና የጥፊ ድጡ
የሆድ ቁስል ፍርጥርጡ
ምኑ ቅጡ፣ ምኑ ቅጡ! ....
የተነፋ ሩር ተጉኖ፣ በእንጨት መካከል ባለፈ
ስንቱ ጉድ ከተለፈፈ
'ያራዳ ጐበዝ' በከንቱ፣ እስከዚህ ከተማረረ
'ጀግና' እንዲህ ከተዋገረ
በነገር ከተዋቀረ
እከደከ! ማለት እንጂ፣ አንደዜም ጎል! እንዴም እረግ!
እበሽ ለእበሽ ሲጠራረግ
መቸስ ሌላ ምን ሲደረግ?
ፊኛ በእንጨት ውል በገባ
'ጐበዝ' አጉል እየባባ
ነገሩ እንዲህ ከጠነባ
አፍና ደም ከተቃባ.....
ጭንቅላት እንደኳስ ሞልቶ፣ በኳስ ተሳክሮ ቢታወር

እርስ በርሱ ቢሰባበር
እረግ! እያልን የጎል መከር
ዝም ብለን ከማየት በቀር
አያስችለን የሉ ነገር፥
የተነፋ ኩር ማባረር።....
ያንዱ ዋይታ ላንዱ ደስታ፥ እሰየው ጎል! እረገኝ ጎል!
ያንዱ ገነት ላንዱ ሲዖል።

ለኳስ 'አርበኛ' - ፲፱፻፷



# አዴ አዳዩ

አዴ አዳዩ እሙ-ምኔቴ
የትውልድ መስታዮቴ
የዘመን ቅርሴ መክሊቴ
የዕድሜ አንቀልባዩ፥ ሞግዚቴ
ቀን ማገረሽ አንቺ እጣዩ
ጃጀሽ አሉኝ አዴ አዳዩ፤....
በሥጋትሽ ተንጠልጥዩ
በአንገትሽ ማተብ ታዝዩ
በዓይንሽ ጢሎሽ ተንጠልጥዩ
በጮጮሽ ተሞካሽቼ፥ በጉርሻሽ ውሽን ተብዩ
በእንጉቻሽ ተከባክቤ፥ በእንክኮሽ ተደላድዩ፤
ካፍ ከወጣ አፋፍ ነው ሲባል
ለካሰ ነገር ይገለማል፤
አዴ አዳዩ የአባዩ እናት
ለምን ይሆን ያሉሽ አያትጳ
ባፍ ዝምድናሽን ሲያቀርቢት
ስምሽን ሦስት እጥፍ ያራቁት?
ከዚህ ወዲያ ምን ይበሉ
አይሉት ነገር ብለውኝ፥ ዋ ዕድሌ አለመታደሉ
የአንቀልባ ማውረጃ እርካቤን፥ አዳዩን ጃጅተሻል አሉ።

የዓይንሽ ብሌን ያ ብረቱ
ያ የመለኮት ስለቱ
ካለማወቄ ያገደኝ
ከምድሯ እሳት ያፈለኝ፤
የእጅሽ ድባብ የሙቀቱ
የፍቅርሽ ንቃት ፍጥነቱ
መዳፍ ዳሰሳሽ ድቀቱ
ተግ-ብር ያለ ሥጋቱ፤
ከውድቀት አፋፍ ያቀፈኝ
ከጋሬጣ የጋረደኝ፣
ያ እጅሽ የልጅነት ክንፌ
ጣትሽ የድሆሽ መርገፌ፤
አዳዬ መዳፍሽ ዘርፌ
የትውልድ እም-አእላፌ
የዓለም መሻገሪያ ጠንፌ
ቀን ማገሪሽ አንቺ እጣዬ
ጃጅተሻል አሉኝ አዳዬ።
የዘመን አጥር አጠረን?
የዕድሜ ግድግዳ ጋረደን?
ሳንጣላ ሳንኳረፍ፣ የትውልድ ማገር ለየን?
ጊዜ ለጊዜ ነው እንጂ፣ ዓይን ለዓይን አላሳይ አለን?....
አዴ-አዳዬ እመ-ምኔቴ



የትውልድ መስታየቴ
የዘመን ቅርሴ መክሊቴ
የዕድሜ አንቀልባዬ፣ ሞግዚቴ
የሕፃን ዓለም አጥላዬ
መከዳ መካበቻዬ፣
በቃ ላንቺ ወዮ አልልም፣ ይብላኝልኝ፣ ወየው እኔን
ሞተሽ ሳለ ግማሽ ኖረሽ፣ በእስትንፋስሽ ግርሻ ሳጤን
በበድን ሕይወትሽ ዋገምት፣ በቁምሽ ግማሽ አሰከሬን፣
ላልገፋው በዕድሜሽ ዕድሜዬን
ጊዜሽ ላይወሰን ዘመኔን
በስምሽ ሰይሜ ሰሜን፣
እዎን ይብላኝልኝ እኔን
ወረቴ በምድር ለቀረው፣ ያንቺ ሲዛመት በሰማይ
ከእንግዲህ ቋንቋ ለቋንቋ፣ ላንጣጣም ላንወያይ
ባንቺ ገበያ ላልገበይ፣ ላላገግም ባንቺ ሚሳይ
ዕቁብ ለዕቁብ ላንጣጣ፣ ላልሞካሽ ባንቺ ጠባይ
ዐመል ለዐመል ላንወያይ፣ ዕድሌ ዕድልሽን ላያይ
መቀነትሽ ላይመጥነኝ፣ ላትዘልቂ በኔ አደባባይ፣
ያንቺስ አካቷል አዳዬ፣ ይብላኝልኝ ለኔው አዋይ።
ይብላኝልኝ አዴ አዳዬ፣ ውለታሽን ላልከፈልኩት
በወዝሽ መጥናቴን እንጂ፣ መጠንጠኔን ላልተማርኩት።
አቀርቅሮ ምድር ዓለም፣ ዓይንሽ አፈር ሲቆረቁር

ሕልምሽ ሲቃ ሲያፍተለትል፣ ሃሳብሽ ጣር ሲቦረቡር፣
ጣትሽ ጉድፍ ሲያጉደፈድፍ፣ ሕሊናሽ ቁልቁል ሲያተኩር
አልፎ አልፎ እንኳን ቀና አትዪ
የኔን ቀሪ ዓለም ዘብ-እረብ፣ እስለምልሜን እንዳታዪ፣....
አዴ አዳዬ እመ-ምኔቴ
የቅድመ ፍጥረት ምክንያቴ፣
የሕይወት አማጭ ሰበቤ
የመኖር ክብካብ ድባቤ፣
ያንቺማ አካቷል እንግዲህ፣ የጊዜአችን ኬላ በሩ
የዘመን ግድብ ድንበሩ
የትውልድ አጥር ማገሩ
አምባ ከአምባ ከፍሎ አግዞን፣ የናት ባዳ ሆኖ አድባሩ፣
ታድመን እንዳልተጣመርን፣ ተሸልቶ እጣሽ ከእጣዬ
ተቆራርጠን ተገንጥለን፣ ባይተዋር ሆነን አዳዬ፤
በዕድሜ ናዳ ተገድቦ፣ የፍቅርሽ ሙቀት ጠልቆ
የሥጋትሽ ምንጩ ደርቆ
ያይንሽ ጨረር ሰሉ ባርቆ
ብርሃን-ወሰፈንጥሩ ዳሽቆ፣
የስሜት ጮራሽ ዳለጠ
የዕድሜሽ ውጋጋን ሟሰጠ።



አዴ አዳዬ እመ-ምኔቴ
የትውልድ መስታየቴ
የዘመን ቅርሴ መከሊቴ
የዕድሜ እንቀልባዬ ሞግዚቴ
ቀን ማገረሽ አንቺ እጣዬ
ጃጀሽ አሉኝ አዴ አዳዬ።

አዎን፣ በትውልድ ኬላ፣ የዕድሜ ሕመምሽ እኔ አያመኝ
ቂም እንዳዘለ አበዳሪ፣ ካጥር ማዶ ነው እሚጠቅሰኝ፣
ላንተም ቀን አለህ እያለኝ፣ ላልረሳው እያስታወሰኝ።
"ጊዜ የጊዜ ነው እንጂ፣ አንቺ እኔ ነሽ፣ እኔ አንቺ ነኝ"
ብልሽ፣ ላንደበት ወግ በቀር፣ እኔም አንቺም አንጠቀም
ሕመሜን ላትታመሚ፣ ሕመምሽን ላልታመም፣
የዘመን አጥር ክፍሎናል፣ አውቀነዋል፣ አንደለል
ታድያን ጊዜ የጊዜ እንጂ፣ ድሮም የዘለቄታ አደል።....
እና፣ የነገ ጥሪዬን፣ ዛሬ በጥሪሽ አየሁት
አዴ አዳዬ እመ-ምኔቴ፣ ጭንቄን በጭንቅሽ ለየሁት፤
እንጂ፣ ካንቺ አልካፈልም
እኔ ቁሰልሽን አልቆስልም
ጣርሽን አልጣጣርም፣
በጉልበትሽ እንደጠናሁ፣ አንቺ በጉልበቴ አትጠኚም
በወዝሽ እንደለመለምኩ፣ በወዜ አትለመልሚም
ቁቤ ያንቺን መንጠቅ እንጂ፣ ዕዳ መክፈሉን አያውቅም

በጉርሻሽ መጥናቱንም በቀር፣ መጠንጠኑን ከቶ አያይም፣
አዴ አዳዬ ብቻሽን ነሽ
ጣር እሚካፈልም የለሽ።....
ክናድሽን እንደ አለት ላይ ዛፍ፣ ቅርንጫፉን ለጭራሮ
ቦና እራቁቶት ተንጨፍርሮ
ለማገዶ ተሠንጥሮ፣
ስዛው ተሟጦ እንደ ሁዳድ
ተንጋሎ በሀጋይ ምጣድ
አረሀ ሥራ-ሥሩን ነድሎ፣ አጋልጦት ለቀትር ንዳድ፣
የዘመን ሀሩር በስለት
ግንዱን አክስሎት በግለት፣
ክንፍሽ ዘሞ እንደዛር ጥላ፣ መዳፍሽ እርሮ እንደኩበት
ጣትሽ እንደአሞራ ኩምቢ፣ ጥፍርሽ እንደጥፍሩ ጉጠት፣....
ስሜ እንኳ እንዲያ የምትወጂው፣ እንደምሥጢር ግር ሲልሽ
እንቆቅልሽ ሲሆንብሽ
ገጥታዬ ሲያሳስትሽ
ትዝታው ሲያስበረግግሽ
ሃሳብ እንደትንፋሽ ሲያጥርሽ
'ጥም እንደቁም ነገር ሲያንቅሽ'፣
ውሃ ስትይ የስንቅ ውሃ፣ ለግብር፣ለጣረ-ሞት ምስሽ
ለመንፈሴ ፋታ ልስጥ፣ ትዝታሽ እንዳያገረሽ
ከንፈሬን ጉንጭሽ አድርጌ፣ ከጭንቀትሽ በዚህ ልሸሽ



ሳትሞቺ ግማሽ ሙት ፊትሽን፣ በከንፈር ተሰናብቼ
ጣርሽን በዚህ ሸኝቼ
የወግ የይስሙላ አድርጌ፣ እፎይ ብዬ ፋታ አግኝቼ
መንፈሴን አስተባብዬ፣ ዕንባዬን በዚህ ገትቼ፤
ተሰናበትኩሽ አዳዬ፣ የትውልድ መስታዮቴ
የዘመን ቅርሴ መክሲቴ፣ የዕድሜ አንቀልባ እሙ-ምኔቴ፤
ተሰናበትኩሽ አዳዬ፣ በፍትሃት በከንፈር ጉዞ
በግማሽ ሙት ግማሽ ሙሾ፣ በይስሙላ አሰገንዞ፣
ብር ትር ይል የነበረ፡ የደምሽ ሙቀት ቀዝቅዞ
ሽው እልም ይል የነበረ፣ የገጽሽ ውጋጋን በልዞ
የፈገግታሽ መንጸባርቅ፣ ጥርስሽ ፈልሶ፣ ተመዝምዞ
የትዝታሽ ንቃት ፈዞ
የስሜትሽ ብርሃን ቦዞ፣
ክስል አፈር መስል ቆዳሽ፣ በዕድሜሽ ገጣባ ተተልሞ
የእልፊት ትዝታ መዝገብሽ፣ በአልሞት ባይ ተስፋ ታግሞ፣
ብሌንሽ ቅስሙ ዶልድሞ
በዕድሜ-ምሽት ተጭለምልሞ
በሕይወት ምጥ ተረምርሞ፣
በደቂቅ ነፍሳት ውትብትብ፣ ክቅድመ ዓለም ተጠንጥነሽ፣
በእልፍ-አእላፍ ምእተ-ዓመታት፣ የትውልዴ ድልድይ ሆነሽ
ሰው በመሆን ኪነ-ሰበብ፣ ከዘመን ዘመን አሻግረሽ፣
በጥንተ-ፍጥረት አንቀልባ፣ በዕንስ የፍሬ ዘር ፀዳል

የአጥንቴ ካብ መሰላሌ፣ በተፈጥሮ ምግባረ ቃል፤
እጣሽ ዞሮ ተዳረሰ፣ ቀንሽ ከቀንሽ ተጣባ
አድፍጦ አስታምሞ አዝግሞ፣ ያው ወደ ምድረ-ከርስ አምባ፣
አዴ አዳዬ እመ-ምኔቴ፣ ትከሻሽ ሞት አረበበ
የትውልድ መስታየቴ፣ በረቂቅ ጥሪ ተሳበ፣....
ጥላው በአናትሽ አንዣቦ
በእርግብግቢትሽ ተከቦ
በሕሊናሽ ጕሮ ጠልቆ፣ በአንደበትሽ አኮብኩቦ፣
በሌጣ ጀርባሽ ተጭኖ፣ ፊትሽን ቁልቁል አስተኩሮ
ፍቃድሽን፣ ምኞትሽን፣ የሕልምሽን ቋት ሠርሥሮ
ከዘር እንደተጣባ ዛር፣ በአስትንፋስሽ ፅላት አድሮ
እንደደራሽ ሙላት ቁልቁል፣ ተንደርድሮ አንደርድሮ፣
ከፅለት ፅለት እየጠራሽ፣ እየሳበሽ ወደ ጥንፉ
የፅድሜሽ ልጓም በጁ ወድቆ፣ ተካቶ ሕልውናሽ በእርፉ
ከጥንተ ዓለም መንታ ጉያው፣ ሊያዞርሽ ከፅንፍ እፅንፉ
ሊያከናንብሽ በከንፉ፣....
አንቺም በቦዘ ብሌንሽ፣ እርቀሽ እያስተዋልሺኝ
በግማሽ አስከሬን ጣትሽ፣ በልማድ ብቻ እያሰስሺኝ
አዴ አዳዬ አላይህ አልሺኝ!
በበድን እየዳሰስሺኝ
በደነዘዘ ደመ-ነፍስ፣ ቃትተሽ እያድበሰበስሺኝ፣
በርቱእ ሕልው ልቦና፣ አጥርተሽ አላውቅህ አልሺኝ።....
አዴ አዳዬ አላይህ አልሺኝ።



አይሉት ነገር አይባል
ካፍ ከወጣ አፋፍ ነውና፣ ነገር ይሳሳል ይሰፍፋል
ደርሶ ካፍ-አፍ ይገለማል
ይቀላል አጉል ይነፍሳል፣
ያልተናገሩትም እንደሁ፣ ያው ነገር በሆድ ይቆርጣል፣
ይሻላል ማሰላሰሉ
ሳንጣላ መኳረፉ፣ አብሰልስሎ መብሰልሰሉ፤....
ዋ የጊዜ ኬላ በሩ
የትውልድ አጥር ማገሩ፣ ድንበር አለማሻገሩ፤
ዋ ፅድሌ አለመታደሉ
የአንቀልባ ማውረጃ እርካቤን፣ አዳዬን ጃጅተሻል አሉ፤
አዴ አዳዬ እመ-ምኔቴን
የትውልድ መስታየቴን
የሕይወት አማጭ ሰበቤን
የመኖር መርገፍ ድባቤን
ዘመን ከዘመን አጠረን
የፅድሜ ግድግዳ ጋረደን
የፅትብታችን ግድብ ለየን።....
አዴ አዳዬ ብቻሽን ነሽ
ሞት እሚካፈልም የለሽ።

ለአዴና ለጎሮምቲ ጉቴ ዳኛ - (፲፱፻፷ - ቦሎ)

# የት አባቱ ሞትም ይሙት!

እባካችሁ ዘመዶቼ፥ ስሞት ሞትም አብሮኝ ይሙት
በሳቅ በደስታ ግደሉት
በሃሴት በዕልልታ ውገሩት
ከእጥንቴ በታች ቅበሩት፤
እባካችሁ ዘመዶቼ፥ ለሞት የልብ ልብ አትስጡት
ናቁት አጥላሉት አውግዙት
በሙሾ ግነን አትበሉት
በሞቴ፥ እንዳታስደስቱት።
እንደ ዶርዜ ወንድሞቼ
በሳቅ ታጅቤ ኮርቼ
ሞቴን በዘፈን ሞልቼ
በዳንኪራ ሰበቃና፥ በዘፈን ሆይታ አካትቼ
በሠርጌ ብቀበር ሞቼ
አፀድቅ ነበር ባትረሱ
በእንባ ውሌን ባታፈርሱ።

እባካችሁ ዘመዶቼ፥ በሳቅ ጉዞ ፍታት ፍቱኝ
በሙሾ ዋይታ አታጅሉኝ፤
እናቴም ፊትሽ አይክሰል
በአልልታ ብርሃን ይንበልበል፤



በእረፍቴ እንዳታፌዥብኝ፥
በሠርጌ እንዳታለቅሽብኝ።
ገጽሽ በጭንቅ አይወረስ
ልብሽ በኃዘን አይላበስ
በሆድሽ ሞት አይፀነስ
ዕንባ ባይንሽ አይቋጠር
የሞት ቅስሙ እንዲሰበር።
አዎን፥ አደራ፥ አደራችሁ፥ የሙት ውሌን ተቀበሉኝ
ደስታዬን ተካፈሉኝ
ለንስሃ ሞት አደለም፥ ለፍሥሐ እረፍት አብቁኝ፤
በዶርዜ እስክስታ አሰቀብሩኝ
በአልልታው ጉዞ አሳጅቡኝ
በጠሩ ችቦ አሳጥሩኝ፥
ጭብጨባችሁ በስልቱ ይውረድ
ዛፍ ቅጠሉም አብሮ እስኪረግድ፥
ሀገር ምድሩ ያቅራራ
ሀሴት ነው ይበል፣ ጀቢራ
ሠርጌ ነው፥ ይምታ ዳንኪራ።
እንዲህ ስሜት ሲፍለቀለቅ፥ ሲፈነድቅ ሲግል ሃሞት
ቱማታው ሲዋጥ በላቦት

ሆይታ በሆይታ ሲራኮት
ማሳሰፊያ መግቢያ ሲያጣ፥ ፍርሃት ገበናው ሲራቆት
መቃረቢያ ፍንጭ ሲያጣ፥ በእልልታ ሲወገር ብሶት....
ብቻ ነው፥ ሞት ራሱ እሚሞት።
እባካችሁ ዘመዶቼ ሰሞት፥ ሞትም አብሮኝ ይሙት!
በእልልታችሁ ግደሉት
በዳንኪራችሁ ውገሩት
ከአጥንቴ በታች ቅበሩት።

፲፱፻፷፫ - ዶርዜ ሠፈር



## ሰቆቃው ጴጥሮስ

### ከጴጥሮስ - ያቺን ሰዓት ቴአትር

እየ፥ ምነው እመ ብርሃን? ኢትዮጵያን ጨከንሽባት?
ምነው ቀኝሽን ረሳሻት?
እስከመቼ ድረስ እንዲህ፥ መቀነትሽን ታጠብቂባት?
ልቦናሽን ታዞሪባት?
ፈተናዋን፥ ሰቀቀንዋን፥ ጣሯን ይበቃል ሳትያት?
አላንቺ እኮ ማንም የላት....
አውሮጳ እንደሁ ትናጋዋን፥ በፋሽስታዊ ነቀርሳ
ታርሳ፥ ተምሳ፥ በሰብሳ
ሂትለራዊ እባጭ ጫንቃዋን፥ እንደኮረብታ ተጭኗት፥
ቀና ብላ እውነት እንዳታይ፥ አንገቷን ቁልቁል ጠምዝዟት
ነፍሷን ድጦ ያሰበረከካት
ሥልጡን ብኩን መፃጉዕ ናት፤....
እና፥ ፈርቼ እንዳልባክን፥ ሲርቀኝ የኃይልሽ ውጋጋን
አንቺ ካጠገቤ አትራቂ፥ በርታ በይኝ እመ ብርሃን
ቃል ኪዳኔን እንዳልረሳት፥ እንዳልዘነጋት ኢትዮጵያን።
አዎን፥ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እሸሸግበት ጥግ አጣሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ፥

እማማ ኢትዮጵያን መንፈሴ፥ ተፈትቶ እንዳይከዳት ሠጋሁ....
አዋጅ፥ የምሥራች ብዬ፥ የትብት ምግቤን ገድፌ
ከናቴ ማኅፀን አልፌ
በኢትዮጵያ ማኅፀን አርፌ፥
ከአፈርዋ አጥንቴን ቀፍፌ
ደሜን ከደሟ አጠንፍፌ
ከወዟ ወዜን ቀፍፌ
በሕፃን እግሬ ድኼባት፥ በሕልም አከናፌ ከንፌ
እረኝነቴን በሰብሷ፥ በምድሯ ሳብ አሳልፌ
ከጫጩትና ከጥጃ፥ ከግልገል ጋር ተቃቅፌ፤
በጋው የእረኛ አደባባይ፥ ክረምት እንደወዙ ፍሳሽ
በገጠር የደመና ዳስ፥ በገደል ሸለቆ አዳራሽ
ከቆቅና ከሚዳቋ፥ ከኾርግራ ጠረን ለተሻሽ፥
በወንዝ አፋፍ ሐረግ ዝላይ፥ መወርወር መንጠልጠል ጢሎሽ
ከፍልፈል ጋር ሩጫ ስገጥም፥ ከቀበሮ ድብብቆሽ
ከናዳ ጫፍ ሣር አጨዳ፥ ለግት ሳሜ ትንሽ ግጦሽ
ለጥጃዬ የሌት ግርዶሽ
ለጥማድ በሬዎች ራት፥ ለማታቸው ትንሽ ድርቆሽ፥
ለግልገሌ ካውሬ ከለል
እማሳው ሥር ጕጆ መትከል
ለፀሐይ የሾላ ጠለል፥ ለዝናብ የገሳ ጠለል፥
ውሎ የንብ ቀፎ ማሰስ፥ ያበባ እምቡጥ ሲፈነዳ



የግጦሽ ሣር ሲለመልም፥ ሲለማሩ ሰደድ ሜዳ
አዝመራው ጣል ከንበል ሲል፥ ከብቱ ለሆራ ሲነዳ
ፈረስ ግልቢያ ለሽመጥጥ፥ ከወፎች ዜማ ስቀዳ
ልቤ በንፋስ ተንሳፎ፥ በዋሽንት ዋይታ ሲከዳ....
ያቺን ነው ኢትዮጵያ የምላት
እመ ብርሃን እረሳሻት?
ያችን የልጅነት ምሥራች? የሕፃንነት ብሥራት
የሣቅ የፍንደቃ ዘመን፥ የምኞት የተስፋ ብፅአት
ያቺን የልጅነት እናት?
አዛኚቱ እንዴት ብለሽ፥ ጥርሶችሽን ትነክሽባት?

ሰሜን በሰምሽ ሰይሜ፥ ባገልግሎትሽ ሰዋትት
ከዜማ ቤት እቅኔ ቤት፥ ከድጓ ቤት አመዳሕፍት፥
ካንቺ ተቆራኝታ ዕድሌ፥ ካንቺ ተቆራኝታ ነፍሴ
ከቀፈፋ ደጀ ለሳም፥ ከቤተ ልሔም ቅዳሴ፤
አኮ፥ ቀፎ፥ ዳባ ለብሶ
ቅኔ ዘርፎ ግሥ ገሦ
መቅደሰ አጥኖ፥ ማኅሌት ቆሞ
በልብሰ ተክህኖ አጊጦ፥ በብር አክሊል ተሸልሞ
እመ ብርሃን ያንቺ ጽላት፥ ነፍሴ ላይ በሳት ታትሞ
የመናኒው ያባ ተድላ፥ ረድ ሆኜ አብሮኝ ታድሞ፥
ሕይወቴ እምነትሽን ጸንሶ

ሥጋ ፈቃዴ ተድሶ
ለሕንፃሽ መዲና ቆሞ፥ ለክብርሽ ድባብ ምሰሶ፤
ስሜን በስምሽ ሰይሜ፥ ሆነሽኝ የእምነቴ ፋኖስ
ለዋዜማሽ ግሸን ማርያም፥ ለክብርሽ ደብረ ሊባኖስ
ስሮጥ፥ በወንበሩ አኖርሺኝ፥ በአንበሳው በቅዱስ ማርቆስ፤
ታዲያን ዛሬ ኢትዮጵያ ስትወድቅ፥ ከምትሰጪኝ ለፍርሃት ጠበ
ምነው በረኝነት ዕድሜ፥ ዓይኔን በጉጣት የሎስ
የጋኔል ጥንብ አንሳ ከንፎ፥ ወርዶ በጭለማ በርኖስ።
ባክሽ እመ ብርሃን ይብቃሽ፥ ባክሽ ምስለ ፍቁር ወልዳ
ጽናት ስጪኝ እንድካፈል፥ የእናቴን የኢትዮጵያን ፍዳ፤
ከነከሳት መርዝ እንድቀምስ፥ ከነደደችበት እቶን
የሷን ሞት እኔ እንድሞታት፥ ገላዋ ገላዬ እንዲሆን።....
አዎን፥ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ።....

ሕፃን ሆኜ የአርግብ ጫጩት፥ አንዳንዴ ራብ ሲያዳክማት
ችጋር ከጉጆዋ ገፍቶ፥ እዛፍ ግርጌ ሲጥላት
እናቷ በርራ ደርሳላት
በአክናፏ ሙቀት ታቅፋት
እፍ እያለች ግንባሯ ላይ፥ ሕይወት ስትተነፍስባት
ወዲያው ነፍስ ትዘራለች
ሽር-ብር-ትር እያለች።
ባክሽ አንቺም አትራቂብኝ
እመ ብርሃን እናቴ፥ ትንፋሽሽን እፍ በዪብኝ



ፅናትሽን እፍ በዪብኝ፥
ወይም ይቺን የሞት ጽዋ፥ ጥላዋ ነፍሴን ካፈናት
እንዳልጠጣት አሳልፊያት
መራራ ከንፏን ገንጥለሽ፥ ቀጠሮ፥ ቃልዋን ግደፊያት፤....
አለዚያም ጽናትሽን ስጪኝ፥ ልጠጣው ኪዳን-ውሉን
የኔ ፈቃድ እምነትሽ ነው፥ ያንቺ ፈቃድ ብቻ ይሁን።
እንደጳውሎስ እንድጸና፥ በፍርሃት እንዳልታሰር
በውስጤ ከሚታገለኝ፥ በሥጋ አውሬ እንዳልታወር
ለየዕለቱ ሞት እንዳልሰንፍ
የኪዳኔ ቃል እንዳይነጥፍ
ቃልሽ በሕሊናዬ ዲብ፥ ኃይልሽ በሕዋሴ ይረፍ።
ፍርሃት ቢያረብብኝም፥ አንቺ ካለሽኝ አልሠጋም
ኩርትም ብዬ እችልበት፥ እሸሸግበት አይጠፋም
የግማደ መስቀሌን ጉጥ፥ እታገስበት አላጣም፥
አለዚያማ ብቻዬን ነኝ፥ ኢትዮጵያም አላንቺ የላት
አንቺ አፅኝኝ እንድጸናላት።
አስርጪብኝ የእምነት ቀንጃ፥ ለሥጋቴ አጣማጅ አቻ
ለጭንቀቴ-መቀነቻ።....
አዎን፥ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እሸሸግበት ጥግ አጣሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ....

፲፱፻፰፭ - ቀበና

# እንቅልፍ ነው እሚያስወስድህ

“ዝም አልኳቸው ዝም ይበሉኝ
ትቻቸዋለሁ ይተዉኝ
አልነካቸውም አይንኩኝ”
ብለህ፥ ተገልለህ ርቀህ
እውነት ይተውኛል ብለህ
እንዴት ተሰፋ ታደርጋለህ?!....
ተሰፋ አርገህስ ምን ልትሆን፥ ወይስ ተሰፋው ምን ሲሆንህ?
እንቅልፍ እንጂ እሚያስወስድህ።

“አልጠራቸውም አይጥሩኝ
አይንኩኝ ስሜን አያንሱኝ”
ብለህ እንዴት ትመኛለህ፥ እንደማይተዉህ ስታውቀው
የተወጋ በቅቶት ቢኛ፥ የወጋ መች እንቅልፍ አለው
የጅምሩን ካልጨረሰው?
የተበደለ ቢችልም
ቢሸሽግም ቢደብቅም
የበደለ ዝም አይልም።

እንዴት አስችሎት ዝም ይበል? ለፍልፎ ከማስለፍለፉ
አደል እንዴ የሱ ቤዛ፥ የበደሉ ጥቅም የግፉ
ሰላም መንሳት አደል ትርፉ?....
ዝምማ ካለ ጉድ ፈላ



ነገር በጤና ሲብላላ
እያደር ሲጣራ ኋላ
ግፉ ይፋ ይሆናላ!....
ሰላምማ ከለገሠህ
ሕመምህ እየታወሰህ
ትዝታ እየቀሰቀሰህ
የሕሊናህ ሚዛን ረግቶ፥ ጉዱ ሁሉ ኩልል ሲል
ያደፈረሰው ሲያጠልል
እግዜር ያሳያችሁ ብለህ፥ ፍረዱኝ ዳኙኝ እንዳትል
ከነአካቴው ሳይጨርስህ
ምን ቢሆን ሰላም አይሰጥህ።

እሱስ ቢሆን ያለትክሉ፥ ያላጥንቱ የሰላም ውርስ
ከቶ የማያውቀውን ቅርስ
ይሰጠኝ ብትል የት ይሆናል
ያልተዘራ መች ይፀቅላል?
የጓሮ ጉመን ሲያጢላ
አጥፊ ትሉን እንዲያፈላ
እንዲያው በነገረ ቀደም፥ እንደሱስ ሰሙን ቢለፍፍ
ሰላምን የሰጠህ መስሎህ፥ በጉጉት ስታስፈስፍ
ተለሳልሰህ እንደቃተትክ፥ ተስፋ አርገህ እንዳትል እርፍ።

እና ዘበት ነው ጥረትህ
በከንቱ ተሰፋ ማድረግህ
ላያዋጣ መመኘትህ
የሰላም ቅዠት ማየትህ
ምን ልትሆን? ምን ሊሆንህ?....
ይቅርብህ። በኔ ይሁንብህ
እንቅልፍ ነው እሚያሰወሰድህ።

ለኤድዋርዶ ሞንድላን - (፲፱፻፶፱ - ዳሬ ሰላም)



## እሳት ወይ አበባ

እና፣ እንደኔና እንዳንቺው፣ የውበት ዓይኑን የታወረ
እግረ ሕሊናው የከረረ፣
ባሕረ-ሃሳቡን ያልታደለ
የውበት ዓይኑ የሰለለ
ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፣ አበባ እኮ አደለም አለ።
ያልታደለ።

---

ሌት ከዋክብቱ እንደፀደይ
አጥለቅልቆን በቀይ አደይ፣
ሰማዩ ሥጋጃ አጥልቆ
ተሽለምልሞ አንፀባርቆ
ፈክቶ፣ አሸብርቆ ደምቆ
በአዝመራ፣ በአጥቢያ ዐፀድ ሰፍኖ
በዓደይ አዝርእት ተከሽኖ
በእንቁጣጣሽ ሰብል ታጥኖ
ኢዮሃ አበባዬ ሆኖ፣
ጨረቃዋ ከቆባዋ፣ ከሽልምልሚት እምቡጧ
ጧ ብላ ከሰንኮፈንዋ፣ ተንዠርግጎ የእንኩይ ቡጧ፣
ድንግል ጽጌ-ረዳ ፈልቃ
ፍልቅልቂት ድምብል ቦቃ.....

ተንሠራፍታ የአበባ ጮርቃ፥
ታድያን ብሌት የጠጠረ
ባሕረ-ሃሳቡ የከረረ
የውበት ዓይኑን የታወረ
ልበ-ሕሲናው የሰለሰ
አይ፥ አበባ አደሰም አለ
አይ፥ እሳት አደለም አለ
ያልታደሰ። ....
ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፥ እሳት አደል ብሎ ካደ
እቶን በዓይኑ እየነደደ።
ከዋክብቱ እንደችቦ
በነበልባል ወርቀ ዘቦ
ከፅንፍ ፅንፍ አውሰብልቦ
ደመራው እየተመመ
እየፋመ እየጋመ፥
ደመና እንደ ንዳድ ሲነድ
መንጸባርቅ ሰደድ ሲወርድ
በራሪ ኮከብ ተኩሶ
በአድማሳት እሳት ለኩሶ....
ይኸ እንደኔና እንዳንቺው፥ የውበት ዓይኑ የሰለለ
ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፥ እሳት እኮ አደለም አለ፥
ያልታደለ፤....

---



ይቅር ብቻ አንናገርም፥
እኔና አንቺ አንወያይም፥
ለውይይት አልታደልንም
እንዲያው ዝም እንጂ፥ ዝም ....ዝም።
አበባ እንሆን ወይም እሳት
ተጠምደን በምኞት ቅጣት
ሰመመን ባጫረው መዓት
ዕድሜአችንን እንዳማጥናት.....
እሳት እንሆን ወይ አበባ
በሕቅ-እንቅ ስንባባ
ባከነች ልጅነታችን፥ እየቃተትን ስናነባ።....
ፈራን፤ አዎን ፍቅር ፈራን፥
የነፍስን እንደበት ዘጋን፥
የዕድሜ ጠብታችንን ምጥ፥ የጣር ፅንሳችንን ልሣን፥
ልጅነት የሰገሠንን
በመለኮት የቀባንን
በእሳቱ ያጠመቀንን
የፍቅር አምላክ በጥበቡ፥ በሥልጣን ያላበሰንን
ፈራን፥ አዎን እውነት ፈራን
የስሜት እስትንፋስ ነሳን።

---

ብቻ ስይቶ ላይለየን
በእንፋሎት ላብ እያጠነን፥

ዓይን ለዓይን እየገደበን
ወይ አቅርቦ ላያቀርበን
በይሉኝታ አጥር እያጠረን
በእሉ ቧልታ እየለየን
በይስሙላ እየከፈለን፥
እሳት ሳንሆን ወይ አበባ
ተገድበን እምባ ለእምባ....
እኔና አንቺ አንናገርም
ቢያመንም እንወያይም
እንዲያው እርጭ፥ ጭጭ፥ ዝም።
በቃሽ ትዝታሽን ማሪኝ
የሕልም-ሕመምሽን ታረቂኝ፥....
ዓይንሽ ዓይኔን ሙት እንዳለኝ፤ ሰመመን ተግሣፅ ከሰማ
ሙት እንዳሉት ከሞተማ
ሂድ ቅር ሲሉት ከቀረማ
ይሉኝታ ካደመጠማ
ሲነቀፍ ከታዘዘማ
እሜን፥ ይቅር እንግዲያማ፥
ይቅር የወፎቹም ዜማ፤
ይቅር ጨረቃንም እናይ
ከቶ ላም አለኝ በሰማይ
ብኩን አይጨበጥ ሚሳይ



አይቀርም እንጂ ከቀረ፥ ይቅር ሲሉት ከቀረማ
አይሞትም እንጂ ከሞተ፥ ሙት እንዳሉት ከሞተማ፤....
እማን አልነበረም ያማ።
በይ ሕመምሽን ታረቂኝ
ሰቀቀንሽን ተማጸኚኝ
ሰመመንሽን ይቅር በዪኝ
እምትምሪኝ ከሆነማ፥ ማሪኝ፥ ትዝታሽን ማሪኝ፤....

---

ምነው ታድያን ድምፅሽ ራቀ?
ምነው ልሣንሽ ረቀቀ?....
የዓይንሽ ብርሃን ቀለስ አለ፥ የእንባ ወዝ እንዳቋጠረ
ቃጥቶ እንደተውተረተረ
የመከራ፥ የጭንቅ የምጥ፥ ስልባቦት እንዳቀረረ
የደም ወዝ እንደነዘረ
እንደተሰቀቀ ቀረ?....
ምነው እንባሽን በጠረኩት
ምነው ወዝሽን በዳሰስኩት
ምነው ያይንሽን ውጋጋን፥ ነበልባሉን በቀረብኩት
መንጸባርቁን በሞቅኩት....
ምንም እንኳን ባልደርስብሽ፥ ባልቀርብሽ፥ በሃሳብ አንቅቼ
በእስትንፋስ ተንጠራርቼ
ብደርስብሽ፥ ብዳስስሽ፥ የነፍሴን ሕዋስ ዘርግቼ

የረቀቀብኝ ፈለግሽን፣ ጠረንሽን በምጥ አሽትቼ
እንደጽላት ፋናሽ ግርጌ፣ ገጼን ግንባሬን ደፍቼ፣
የተሳለምኩብሽ ትቢያ፣ እሳት አትሆን ወይ አበባ
ያለፍቅር እንባሽ ላይረባ
ያለስመመን ወለባ
ቡጡ ካልተንዠረገገ፣ ካልተፍለቀለቀ ቅስሙ
የነበልባልሽ የፍሙ
የቆባሽ የስልምልሙ
የብሌንሽ የመብራቱ
የወለፈንጥርሽ የእሳቱ
የገጽሽ የእቶን ግማዱ
የፍላፃሽ የንዳዱ......
አረ ይብቃን መቃጠሉ፣ በዓይን ወላፈን መለብለቡ
ያለፈርጁ ያለባሕሉ፣ እሳት አይጭር ሰው በቀልቡ
ፍም አዝሎ ላይዘልቅ ልቡ፣
አጉል ምን አቀጣጠለን
አስቀድሞ ሳያድለን?
በስመመን ሟሟን እንጂ፣ በመውደድ ለምልሙ አላለን።....
ድባብ እንደራቃት ቆሌ
ባህር እንደገባ አሞሌ
እንዲያው በሕልም አባይ ገነን፤ ለቅዠት መራወጥ ፎሌ
አረ ወዲያ ይብቃን ይቅር



ይኽ የዓይን አዋጅ ብር ትር
ወዝ አይወጣው ድብን እርር......
አበባ አንሆን ወይም እሳት
ተቅበዝብዘን በሃላብ ምትሐት
ለጽድቅ አልበቃን ለኃጢአት
ለነፍስ ወይ ለሥጋ ብፅዓት
ወድቀን በሕልም ዓለም ቅጣት
ፈርሰን በስመመን መዓት....
ታዲያን ምን መናገሪያ አለን? ድዳው ልባችን ዋይ ይበል!
ዕውር ነፍሳችን ይንበልበል
እስትንፋሳችን ይቃጠል
እንጂ፣..... እኛማ ተረግመን
መቼ መነጋገሪያ አለን?
የእርግማን ቢሆን ነው እምን፣ እንጂ ከየት መጣ ዐመሉ
ላንዲት ፋታ ሳንጠቀም፣ በደስታ ጒሕ በፀበሉ
በብርሃኑ በፀዳሉ
ለእሉ ቧልታ ለስም ብቻ፣ ለይስሙላ መደለሉ?
የተደሰትን ማስመሰሉ
ለማስመሰል መታለሉ?
በፍቅራችን መዋሸቱ
በነፍሳችን መዶለቱ? በፍቅራችን ግፍ መዋሉ?
እርግማን እንጂ ትርጓሙ

ሌላ ምን ሊባል ነው ሰው?
አንቺም የወግ ገባር ሆነሽ፣ እኔም የይሉኝታ ባሪያ
የልብን ወሰፈንጥር ጮራ፣ ደፍነን ለሃሜት መደለያ
የመውደድን ቆባ ኪላ፣ የፍሥሃን መጥለቅለቂያ
የሲቃን የምሥራች በር፣ የእልልታውን መታበያ
የፍቅርን እቶን ሰንከፈን፣ የጣር የምጡን ገበያ
የነፍስን የእርግብግቢት ፍንጭ፣ የምጣችንን ማጥለያ፤
የመውደድን ቆባ ገፍፈን
ሽሉን በአመዳይ ለብልበን
ዲካውን በጢስ አፍነን
አውተፍትፈን፣ አድበስብሰን፣ አንገዋለን ምሰን ቀብረን
ከቶ ለኛ እንዳይታደግ
እንዳያብብ እንዳያሠርግ
የመውደድን አምላክ ፈለግ
ቀብረን በይሰሙላ በወግ
እልተረገምንም ካልንማ፣ ሞት እንጂ ሕይወት ካላየን
ያለፀጥታም ድምፅ የለን....
ባያድለን.... ባያድለን።....
ያውም ይኸ አልበቃ ብሎን፣ ሞትን እንደፍቅር ፀንሰን
የወግ የማዕረግ እጣቢ፣ የጉራ መሰዋዕት ሆነን
መውደድን በሰም ገንዘን
በይሰሙላ ጢስ አፍነን



ላፍ ዳረጉት ፍቅርን ከደን
ውቃቢያቸው አምላካቸው፣ ያይብናል እንላለን!
ይባላል፣ አዎን ይባላል
"ይታደጿል እንጂ መቸስ፣ ዕድልን መች ይታገሿል?" ....
መውደድ ለሞት አደገድጐ
ለዕድር ወግ ለዕቁብ ለሸንጐ
ለተዝካር ለፍትወት ድርጐ
ለአደባባይ ይምሰል ልቅሶ
ለእውነት ውጦ ለሃሰት ቀምሶ
ለይሉኝታ ተለባብሶ፤....
እልተረገምንም ካልንማ፣ ሞት እንጂ ሕይወት ካላየን
ያለፀጥታም ድምፅ የለን
ባያድለን.... ባያድለን።....
አንቺም ከሌላ ጋር ብትውይ፣ እኔም ከሌላ ጋር ብውል
ባምሳያ እንጂ ላንቺው ሥዕል
የኔ ልኬ ካንቺ ላያልፍ
በሌላ አካል አንቺን ለማቅፍ፣
ሌላዪቱን ባንቺ አምሳያ
የሥጋ ምሴን ልወጣ፣ ያንቺን ሕመም በሷ ሳቢያ፣
በገላዋ አንቺን እያየሁ
በዓይኗ ዓይንሽን እያሰብሁ
በጠረኗ አንቺን እያሰስኩ

በአካልዋ አንቺን እየዳሰስኩ
ስምሽን ከስሟ እያሳከርኩ
በእስትንፋሷ እያነበነብኩ
አንቺን በሷ ውስጥ ካቀፍኩ
በማኀፀኗ አንቺን ከፀነስኩ፥
በሰው ቅርፅ አንቺን አንጬ
በሰው ጭንቅ አንቺን አምጬ
እሷ ያንቺ ቋት ሆነቺኝ
በሥጋዋ አንቺን ሰጠችኝ፤
እያየሁ እሷን ሳላያት
እያቀፍኩ እሷን ሳላቅፋት
አንቺን አይቼ በሷ አካል....
አንቺን አቅፌ በሷ አምሳል
እያየሽው የግፍ ግፌን
በሰው ኃጢአት መዋሌን
ዕቃ አድርጌ መጠቀሜን
በሰው ሥጋ አንቺን ማቀፌን....
ምነው ደርሶብሽ አይተሽው
የኔን ግፍ በሰው ውለሽው
የፍትወት ግብር ልትከፍዪ፥ የፈጸምኩትን ፈጽመሽ
በሰው አካል እኔን አቅፈሽ
በሰው ጭንቀት እኔን ፀንሰሽ፤



መውደድን ለወግ ማገዱ
ፍቅርን ለቧልት መካዱ
ሳንደሰት ደስ እንዳለን
ሰይስሙላ አስመስለን
ውቃቢያቸው አምላካቸው፥ ያይብናል አንላለን!....
አልተረገምንም ካልሽማ፥ ሞት እንጂ ፍቅር ካላየን
ያሰፀጥታም ድምፅ የለን።
እሳት ሳንሆን ወይ አበባ
ዘር ነሰቶን ለወግ ገለባ
ፍሬ አጥተን ለወሬ አባባ
ሰጉጉት ሽል ሰናደባ፥
አበባ አንሆን ወይም እሳት
ተስለምልመን በእውነት ፍርሃት
ሳንኖር በሙት ሕይወት ሥጋት
ወይ ሳንሞት በቁም-ሞት ፍትሐት
ተይዘን በሃሳብ-እታምጣ
በ-አይነግሩት የቁም ስቅል ፅጣ
ከቶ ሳያሸት ባጨጨ
ሳይጠጣ በመነጨ
ሳይፈጠር በተቀጨ፤....
የኛን ከቶ አይወለድ ፅንስ
አፍ አይነካው የጽላት ጥቅስ

የሕመም የሰመመን ውርስ
የኛን ሾላ በድፍን ቅርስ
እኔና አንቺ አንወያይም፥
በሞት አፍ ብናገግምም
በምጥ ጦር ብንሰበርም
ዝም እንጂ አንነጋገርም
እንናገረው የለንም።
ምኞት ብቻ ነው እሚርበን
ላናገኘው ላያጠግበን፤
ዕጣችን በጣር ታግሞ
በዘለዓለም አረምሞ፥
እሳት እንሆን ወይ አበባ
እንዲያው በልብ የምጥ እንባ
ተከናንበን ሰናደባ
ተሸሽገን ሰናነባ....
ዓይኔ አንቺን፥ ያንቺ እኔን ሲሰብ
ለዓይነ-ሥጋሽ የዉፍ ምግብ
ላናገኘው ላንጠግብ
ያንቺ እኔን የኔ አንቺን ሲያርብ.....
ልጅነትሽን ሳታካብች፥ ዕድሜሽን ምን ሳትሠሪበት
አባከንሺው ባከንሽበት፥
ልጅነቴን ሳላካብት፥ ዕድሜዬን ምን ሳልሠራበት



አባከንኩት ባከንኩበት፤
እግዜር የሰጠኝን ዕድሜ
ሰንጀባረር አጣጥሜ
አበባዬን ላቤን ወዜን
የልጅነት ቆባ ቁቤን
ምን አረኩት? ምን አረግሺው?
አባከንኩት፥ አባከንሺው፥
ባከንሽበት፥ ባከንኩበት።
ተሰፋና ምኞት ለጸጋሽ፥ ማዕጠንቱን ብቻ ሳውቅበት
ነፍሴን ሰነፍስሽ መሰዋዕት፥ ግዳይ ሰጥል ባደግሁበት
ሰሞገስሽ ሃሌ-ሉያ፥ ለእድባርሽ በሰገድኩበት
ሳንፈጠር በሞትንበት
ሳናብብ በረገፍንበት
ሳንጠና ባረጀንበት
አበባ ወይንም እሳት፥ መሆኑን ብቻ አጣንበት።....

---

ታድያን እንደኔና እንዳንቺው፥ የውበት ዓይኑን የታወረ
እግረ ሕሊናው የከረረ
ባሕረ-ሃሳቡን ያልታደለ
የውበት ዓይኑ የሰለለ
ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፥ አበባ እኮ አደለም አለ።
ያልታደሰ።....

ሌት ከዋክብቱ እንደፀደይ
አጥለቅልቆን በቀይ አደይ
ሰማዩ ሥጋጃ አጥልቆ
ተሽለምልሞ እንጸባርቆ
ፈክቶ፣ አሸብርቆ ደምቆ
በአዝመራ፣ በአጥቢያ ፀፀድ ሰፍና
የዓደይ አዝርእት ተከሽና
በዕንቁጣጣሽ ሰብል ታጥና
ኢዮሃ አበባዬ ሆና፣
ጨረቃዋ ከቆባዋ፣ ከሽልምልሚት እምቡጧ
ጧ ብላ ከሰንኮፈንዋ፣ ተንዠርግጎ የእንኮይ ቡጧ፣
ድንግል ጽጌ-ረዳ ፈልቃ
ፍልቅልቂት ድምቡል ቦቃ.....
ተንሠራፍታ የአበባ ጮርቃ፣
ታድያን ብሌኑ የጠጠረ
ባሕረ-ሃሳቡ የከረረ
የውበት ዓይኑን የታወረ
ልበ-ሕሊናው የሰለለ
አይ፣ አበባ አይደለም አለ፤
አይ፣ እሳት አይደለም አለ፤
ያልታደለ።....
ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፣ እሳት አደል ብሎ ካደ



እቶን በዓይኑ እየነደደ።
ከዋክብቱ እንደችቦ
በነበልባል ወርቀ ዘቦ
ከፅንፍ ፅንፍ እውለብልቦ
ደመራው እየተመመ
እየፋመ እየጋመ
ደመና እንደንዳድ ሲነድ
መንጸባርቅ ሰደድ ሲወርድ፣
በራሪ ኮከብ ተኩሶ
በእድማሳት እሳት ለኩሶ....
ይኸ እንደኔና እንዳንቺው፣ የውበት ዓይኑ የሰለለ
ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፣ እሳት እኮ አደለም አለ፣
ያልታደለ።....

---

ይቅር ብቻ አንናገርም፣
እኔና አንቺ አንወያይም፤
ለውይይት አልታደልንም
እንዲያው ዝም፣ እንዲያው ዝም.... ዝም።
አበባ አንሆን ወይም እሳት
ተጠምደን በምኞት ቅጣት
ሰመመን ባጫረው መዓት
ዕድሜአችንን እንዳማጥናት፤....

እሳት እንሆን ወይ አበባ

በሕቅ እንቅ ስንባባ

ባክነች ልጅነታችን፥ እየቃተትን ስናነባ።

ሳንፈጠር በሞትንባት

ሳናብብ በረገፍንባት

ሳንጠና ባረጀንባት

አበባ ወይንም እሳት፥ መሆኑን ብቻ አጣንባት።

ለአሳምነው ገብረ ወልድ - (፲፱፻፹ - አራት ኪሎ)



## እስቀመጡህ አሉ!

እኮ ስምህን ማን ብለው?

አሁንም "የሉሉ አባት" ነው?....

ወይስ አዲስ ቀየሩልህ? ሰየሙህ ዳግም አጥምቀው?

እንደ አንኮል ማንጠልጠያ፥ በጥሰው ሌላ ቀጥለው?

"እስቀመጡህ" ብለው አሉኝ፥ በል እሰቲ ይኸ አማርኛ ነው?

አንተና እኔ የምናውቀው?

ወይስ ዘመኑ ወሰደው?....

እኔማ አላመንኳቸውም፥ በዚህ በቋንቋ ጋጡወጥ

ለማጥላላት ለሚሽሚጠጥ

"የሉሉ አባት-የሉሉ እናት"፥ ብለን ስንቆለማመጥ

ፍቅራችንን ለማንጓጠጥ

ትዳራችን እንዲናወጥ

ልጃችን ቅስሙ እንዲቆረጥ

የተደረገ ዘዴ ነው፥ ቀንተው የሠሩት መበለጥ

እንጂ ተቀመጥክስ ቢሉኝ፥፥ምንህ ምኗ ላይ ሊቀመጥ?

ደሞስ ስምህን ማን ሊሉት ፥

አሁንም "የሉሉ አባት" ነው፥ ወይስ ቆርጠው ሊቀጥሉት?

"እስቀመጡህ ብለው አሉኝ"

አጉል ነግረውኝ ላይጠቅሙኝ

ሊያሳዝኑኝ፥ ሊያስተክዙኝ....

እኔማ አላምንም እልኳቸው፣ ለአፌ እንኳን እንዳልላሳት
ለምን ደስ ይበለው ጠላት፣
መዘባበቻ እያረገ፣ ለምን ይሳቅ በኔ ጥቃት
አንተም ሃሰት ነው በላቸው፣ እባክህን የሉሉ አባት።
እስቀመጡህ ብለው ቢሉኝ፣ ጥላ ድባቤ ተደፋ
አለኝታዬ እዋዩ ጠፋ
ቀንም የሃሜቱ ሹክሹክታ፣ ሌት ብቸኝነቱ ከፋ
ቀየአችንም ቀዘቀዘ፣ ጎጆአችንም ነፋስ መታው
ሉሉም ጥርጣሬ በዛው
የኔንም ተስፋ ዕድሜ ገባው፣
ንብረታችን ወሬ ንዶት
ትዳራችን ቆፈን ውጦት
ስሜቴም ወዙ ተጣጣ
መካበቻዬ ዋስ ቢያጣ፤
መመኪያዬ ተከተተ
ዕጣ ክፍሌ ተሸለተ
ገበናዬ ተራቆተ፤
እባክህን የሉሉ አባት፣ እኔን ባትምር ስሜን ማረኝ
መታወቂያ መጠሪያዬን ስሜን ብቻ ይቅር በለኝ
ባይሆን የሙት ሚስት ይበሉኝ፣ የቅምጥ ሚስት አታሰኘኝ፤....
ጥሞናህ እንኳ ቢሸሸኝ
ልቦናህ ባያስታውሰኝ



በስም እኮ የሉሉ እናት ነኝ።
እና ባክህ ተለመነኝ
ስሜን እንኳ አታሳድፈኝ፣
የሙት ሚስት ነው እሚሻለኝ
የቅምጥ ሚስት አታሰኘኝ።

እዎን በኔ ይሁንብህ
እኔና ሉሉ ነን ስምህ
ከኛ ወዲያ ማን ሊያውቅልህ?
ብትሞትስ እንደኛው ያህል፣ ካንተ ሞት ማ ሊጋራልህ?
እንደኛው ሆድ ማ ሊባባ?
እንደኛው እንባ የማ እንባ?
እንደኛው እንጀት ማ ቆርጦት?
እንደኛው እጦት የማ እጦት?
እና በኔ ይሁንብህ
የኔም የሉሉም ነው ስምህ።

የቅምጥ ልጅ፣ የቅምጥ ሚስት፣ መባል ሽታው እያስጠጋም
የእውነት ሞት ግን ከቶ አይገማም
ቅስም ሰብሮ አይቀረናም ,
የስም ሞት ነው ክብርን እሚያም።

ያም ሆኖ እኔ አልተቀበልኩም
ነገራቸውን አልዋጥኩም
ምንም በግትር አንደበት፣ እስቀመጡህ ብለው ቢሉም
እስካሁን በጆሮዬ እንጂ፣ በልቦናዬ አልሰማሁም።

ምንም ቢሆን የሉሉ አባት፥ ውስት እንዳመቸው ደማ
ግርዶሽ እንዳወዛው ሲናር፥ እንደ ወዶ ገባ ኮርማ
ተነስ ሲባል ብድግ የሚል፥ ተኛ ሲባል የሚተኛ
በዳረጐት እንደፋፋ፥ የፍርፋሪ ሉሰኛ
ጉልበቱን ለጉርሻ ግብር፥ እንደሸጠ ቀለብተኛ
አደለም ብዬ ክጃለሁ። ነገሩ ባይዋጥልኝ፥
እመኚብኝ ብለኸኛል፥ እወቅልኝ ባታውቅብኝ
ባይሆን የሞትን ክንድ እንጂ፥ ውርደት ማቀፍ አይሆንልኝ
ዋሽቼ እንደሁ የሉሉ አባት፥ ዋሾ ብለህ መስክርብኝ።
መስክርብኝ የሉሉ አባት፥ ባንተ እምኜ አልሰሳሰስ
ምን አባቱ እርሜን ላውጣ፥ እምነት ቢሞት አይታደስ
አሳማ ነው እንጂ ጨዋ፥ ወደ ትፋቱ አይመለስ
ያስቀመጡህ ቢያስቀምጡህ፥ ልቤ ነው እንጂ እውነት አትፈርስ።
የተሰማውስ ቢሰማ
በነጋሪት ቢያስተጋቡት፥ ባፍ ሹክሽክታ ቢገለማ
ስም እንጂ ፍቅር አይገማ።

፲፱፻፷፩ - አምቦ



# አ ባ ይ

አባይ የምድር ዓለም ሲሳይ
የቅድመ-ጠቢባን አዋይ
አባይ የጥቁር ዘር ብሥራት
የኢትዮጵያ ደም የኩሽ እናት
የዓለም ሥልጣኔ ምስማክ
ከጣና በር እስከ ካርናክ
በጡትሽ እቅፍ እንዲላክ
ለራህ ለፀሐዩ ግማድ፥ ለጣሀ ለከዋክብት አምላክ
ከጥንተ-ፍጡራን ጮራ፥ የመነጨሽ ከኩሽ አብራክ።
አባይ የምድረ-ኩሽ መኩሪያ
በቅድመ-ታሪክሽ ጥርጊያ
ከደም-ቢያ እስከ ኑ-ቢያ
ከሜምፌስ እስከሜሮኤ
በሥልጣኔሽ ትንሣኤ
ከዴልታሽ እስከ ዴር-ሡልጣን
ከኡመ-ራህ እስከ ኡመ-ዱርማን፤
አባይ የአቴስ የጡቶች ግት
ለዓለም የሥልጣኔ እምብርት፤
ጥቁር አባይ የጥቁር ምንጭ
የካም የሥልጣኔ ፍንጭ፤

አንቺ የምድረ ዓለም ሲሳይ
በረሃውን ጥሰሽ ግዳይ
ሰሃራን እንዳከርማ ተልም
ሰንጥቀሽው በወዝሽ ደም፥
በጥበብሽ ሥርው-ፍና
አንቅተሽ ባንቀልባሽ አዝለሽ፥ የቅድመ ታሪክን ዝና
የራምሴስን አበ-ሲሞቦል፥ የመነስን ልዕልና
በአልፋ የአልሙጋን ሐውልት፥ የቢያ-ሃንኬን ፍልስፍና
በኮማምቦ የሶባቃን፥ በናፖታም የኤዛና
ፊላኤ የአቴስን ምኩራብ፥ በልቅጸር የአሞንን ዜና።
አባይ ታላቅ ቅድሙ-ተስፋ
የኪነት ጉባኤ አልፋ፥
ረቂቅ አባይ ያንቺ መገን
ምጥቀትሽ አይተንተን፥
የእጅ ማስነሻሽ በረከት
ግብርሽ ከአድማሳት ሲከትት
መንጣስያሽ ከዕለት ዕለት
መሻገሪያሽ ካመት-ዓመት
በመስዋዕት ሲወድቅልሽ
በዝማሜ ሲፈስልሽ
በመመለክ በመመስገን
ጽላትሽ ከዘመን ዘመን



በአዝርእት አበቅቴሽ ሲታጠን
አቤት አባይ ላንቺ መገን።
አባይ ረቂቅ የጠቢብ ዘንግ
የከዋክብትን ሠልፍ ደርግ
የጨረቃን ጉዞ ፈለግ
አስቀምረሽ በጠቢብ ዘንድ
በፍሳሽሽ ውጣ ውረድ
በሙላትሽ ሚዛን ረገድ
የሰማይን ጥርጊያ መንገድ፥
የጊዜ መለኪያ ሰዓት፥ ዘኒት ባንቺ ተቀምራ
ከቴቤስ እስከዳንዳራ
ብሥራትሽን እንደደመራ
ሥልጣኔሽ እንዳበራ፥
የመጽሐፈ-ሙታን ዜና
አድርጕሽ ቅድሙ-ገናና
ዛሬ ወራቱ ራቀና
ምድረ-ዓለም ያንቺን አድናቆት
ፈለጉን መሻት ተስኖት
እንዲህ ባንቺ መንከራተት
ታሪክ ወሮታሽ ጠፍቶበት
ትላንት በባዕድ ጨኸት
ዛሬም ባላዋቂ ሁከት

ቋንቋ ለቋንቋ ቢራራቅ
የቅድሚያሽ ንድፍ ላይፋቅ
እዚህ ደማም እዚያ ተማም
መባልሽ ብቻ ባይበቃም
የቅርሰሽ ጭብጥ ይዞታ
ሆሄታሽ እስካልተፈታ፤
አባይ ፋናሽ የሕልም ርቅ
ፈለግሽም ቢሆን ደቂቅ
እንዴት እንዴት ነበር ብለን
ካልደረስንበት ፈልፍለን፥
የጥንቷ አባይ እንዴት ትሆን
አባይ-አቢይ አባይ-ግዮን
ከምንጯ የጥበብ ሳሎን
ግሪክ ፋርስና ባቢሎን
ጭረው በቀዱበት ሰሞን፤
አባይ የአማልክት አንቀልባ
የቤተ-ጥበባት አምባ
ከኩሽ የቅድመ-አበው ብሁል
ከተራራሽ እናት ቁልቁል
የሰው ዘር የታሪክ-ፊደል፥ ገና ከፅንሱ ሲረቀቅ
ሲሰይም የእትብቱን ቆባ፥ ምጥቀቱን ለማንጸባረቅ
ዘለዓለሙን ለማሳወቅ
እስከሜዲተራኒያ፥ ጢስ እሳትሽ ሲፍለቀለቅ፥
ዓባይ አቢይ፥ ዓባይ ግዮን



ለአማልክቶች አምላክ ለአሞን
የኪነት ምንጩ እምትሆን፤
ለኦሩስ ርቱእ አክናፋት
ለነዳዮናይሶስ አባት
ከእምብርትሽ የፀሐይ አምላክ፥ ተቀስቶ በሰማያት
ያረበበብሽ እንደ እሳት፤
ጥቁር አባይ የጥቁር ምንጭ
የካም የሥልጣኔ ፍንጭ
የቅድመ ታሪክሽ ጥርጊያ
ከደም-ቢያ እስከ ኑ-ቢያ፥
የኢትዮጲስ ደም የኩሽ እናት
አባይ የጥቁር ዘር ብሥራት
የዓለም ሥልጣኔ ምስማክ
ከጣና በር እስከ ካርናክ
በጡትሽ እቅፍ እንዲላክ
ለራህ ለፀሐዩ ግማድ፥ ለጣህ ለከዋክብት አምላክ
ከጥንተ-ፍጡራን ጮራ፥ የመነጨሽ ከኩሽ አብራክ፤
ለሃራን እንደምሁር ተልም
ያለመለምሽ በወዝሽ ደም፥
የቅድመ-ጠቢባን አዋይ
አባይ የምድር ዓለም ሲሳይ።

ለየኔታ እሥረስ የኔሰው - (፲፱፻፷፬-ቴቤስ፡ ሙታን-ከተማ)

# መ ሄ ዴ ነ ው

ባር ባር አለ ሆዴ፣ ልቤ መሬት ለቆ
ሊያከንፈኝ እንዳይሆን፣ አለግብሩ መጥቆ
አለአለተዳደጉ፣ አለባህሉ ወድቆ።
ሸው እልም ሸው እልም፣ ልቤ ወፌ-ይላላ
በመስተፋቅር ቀስት፣ በሮሮ ምህላ
እንደደመና አክናፍ፣ እንደጮራው ጥላ
ሸው እልም ሸው እልም፣ ሸው እልም ይላላ።
ነሽጠው፣ ሽፈጠ፣ ሄደ ሸመጠጠ
በመስተፋቅር ጦር፣ በሮሮ አመለጠ።

፲፱፻፹ - ቤልግሬድ



# ዶ ጋ ሊ

ምፅዋ አፋፍ ላይ ምጥ - ፅዋ
ዶጋሊ-ግለት ሀሩርዋ
ከአለት ፍርኩታ ከጫፍዋ
ቆሟል ቃፊር ጠባቂዋ....
ዋ!
ምነው ብቻህን አሉላ
በንዳድ እምትቆላ!
"ቱርክ-ፓሻው" ኩሩ አበሻ
ብቻህን በእሳት ፍል ዋሻ
ግንባርክን እንዳኮሰተርክ፣ አቅጣጫህን ሳታላቅቅ
በዶጋሊ ጣር ብርቅርቅ
ዕፁብ ድንቅ አሉላ ዕፁብ ድንቅ፤
በዚያ በምጥ-ጽዋህ ንዳድ፣ በዚያ በአዱሊስ እሳት ጭንቅ
በእቶን ጥሩር፣ በምድር ፍም ትጥቅ
ቃፊርክን ሳታፈራርቅ
ምነው አሉላ ብቻህን፤ ብቻህን እምትጠብቅ....

፲፱፻፹፫ - ጉርጉስም

## ቦረን (የሙርቲ-ጸሎት-ጥሪ)

፣ ሃይ ሃይ!
ጸጥታ ይሁን....
አንተ የሠራህ ሁሉን
አምላክ ጋዳን ባርክ፤
ጋዳን ባርክ አምላክ
ጋዳ-ሉባን ባርክ፥
ሃሳብን አጥና
ፈረስን አቅና
አምቦሳን አጥባ
ጊደሩን አርባ
ኮርማውን አሰባ
ምድሪቱን አጽድቅ
ጠላትን አድቅቅ
ዝሆን-ጐሽ አድቅቅ
ጦርን አቅናልን
ግዳይ ጣልልን
ምርኮን አግባልን
ማርዳውን አጥልል
ጸጋን ለኛ አክል
ሥርዓቱን አውል



በዐሉን ዐድል
በዐሉን ዐድል....
ቀጥል!
፣ ሃይ ሃይ!
ጸጥታ ይሁን....

ለማዳ ጋልማ - አባ ጋዳ - (፲፱፻፰፱ - ዲሬ)

# ው ሸ ታ ም

እሷ የደም እሳት የላት!
እኮ! ትዝታ'ኮ ለካ፥ ክቶውኑ ቅድስት ናት
ምንም ሕመም እይሰማት
እሷን፥ የእግዜር ፍቅር እንጂ፥ የሰው እሳቱም አይሞቃት!
ብቁ ናት ለካ ፍጹም ናት።
እነሱራፌል ኪሩቤል፥ በእሳት ሠረገላ ወርደው
በመለኮት ብርሃን አቅፈው
በአክናፋት አኮቴት ቀዝፈው
በኅብር አዝለው አንከባክበው
ሰባቱን ሰማያት መጥቀው
ሽቅብ ይዘው፥ ሽቅብ ይዘው....
እዎ ትዝታ'ኮ ለካ
በሥጋዌ ልቡሰ ሕመም፥ ሳትወሰን ሳትለካ
በምድር ሰሜት ሳትነካ
በሰው መውደድ ሳትረካ
ቅዱስ መንፈስ ያላበሳት
ብቁ ናት፥ ለካስ ፍጹም ናት
የሰው እሳት እማይሞቃት!
ከመላእክት ጋር እብራ፥ ክንፍ አውጥታ ተፈትልካ
ምንም ምንም ሳትነካ



በቃች! ትዝታ'ኮ ለካ
ሰው አደለችም ቅዱስ ናት
የሰው ንዳድ እማይሞቃት።

ብቁ ነች እዎ፥ ፍጹም ነች፥
ምን ያረጋል.... ሰው አደለች።
እሷ የደም እሳት የላት
እውነት የእውነት.... ውሸታም ናት።

፲፱፻፷፱ - ሰድሰት ኪሎ

## ከ ፋ

ትኩስ፥ የቡናው ሚሳይ ከተማ
ያባ ጂፋር፥ ያባ ቡና፥ ያባ ጂማ
ከፋ፤ የምንጩ እልጋ ከተራሮች ማማ
ከቀይ መስኖ ማጎፀን፥ የቀይ አፈር ግርማ፤
ከፋ፤ ምድረ ዘለዓለም-አዝመራ
ጥቁር ቡና፥ ውሀ-ጠይም ዘር ሲያደራ
ከፋ፤ "ኮፊ" ሞክሼው፥ በአቦሉ ጀባ ሲጠራ
ረዳው በነጌኔ ተራ
የከፋ ወዝ፥ የቡና መገኑ
ጉሙ፥ ዝናብ እቀፍ ደኑ
ጭጋግ ከንፋ፥ ደመና ወሰኑ፤
ያደን ምድር፥ አውሬ ከንፋስ ሲያጋፋ
ባባ ጂፋር፥ በጀግና አገር፥ ከፋ፤
የቀጭኔው ምጡቅ ግርማ
የእሳት ዓይኑ፥ የነዳልጋ አንበሳው ጋማ
በሌሊት ጥሪ ሲያሰማ
ከፋ፥ ያባ ጂፋር፥ ያባ ቡና፥ ያባ ጂማ
በንጋት አቦል ሲያጠማ
ትኩስ፥ የቡናው ሚሳይ ከተማ።

፲፱፻፺፱ - ጂማ



## "እሳት ዐመድ ወለደ"

"እባቴስ ወንድ ወለድኩ ይበል!
ወለድኩ ይበል ይልቅ፥ በቃ፥
በምላሱ እሚያመረቃ!
ወኔው በአረቄ እሚነቃ
ልቡን በቧልት እሚደቃ
በሤራ በነገር አሽሙር
'በታክት በእንትሪግ' እዙር
ሳሮጥ ሳሽከረክር ሳዞር
በብልጠት ባንደበት ንቃት፥ በመስሎ አስመስሎ መኖር
ሴቷን በነገር መብለጥለጥ፥ ጋስሞታን በምላስ ጦር
ሁሏን ረትቼ አሸንፌ፥ በምጸት ወግ፥ በጌጥ፥ በ'እሞር'፥
ሲነጋ እንደአመድ አፋሽ ገል
ሲመሽ እንደሽንቁር በርሜል
የእግቦ ጢስ በማንቃረሩ
ወሬ በማንሸራሸሩ
ተሞልቶ በመተርተሩ፥
ነፋስ ጠብቶ እየር ታልቦ
የነገር ረሃብ ተርቦ
ጉድ በማናፈስ ተስቦ

ከዚህ ቀድቶ እዚያ ዘንቦ
ውሀ እንደማይቋጥር ገንቦ....

ላባቴ ተወልጄለት፣ ቅምጥል የልቡ ኩራት
ግሥላ የወኔው እሳት
ይመካ እንጂ ይንቀባረር
ይሞካሽ እንጂ ይገደር
የዘር ወጉ እንዳይደፈር
ደርሼለት እሱን መሰል
በተከለው እሚከተል
አባቴስ ወንድ ወለድኩ ይበል።

መሰል ወራሽ ተካሁ ይበል፣ የዘር ቅርሱን የሚያስፋፋ
ድል የሚመታ ሰተቴ፣ በነገር በአሽሙር ልፈፋ
በአግቦ እንደቅኔ ዘረፋ
በሽሙጥ ባፍ ዘለፋ፣
ይበል እንጂ 'እኔም ወንድ ወለድኩ
ባፍ እሚበልጠኝ አደረስኩ
በነገር እሚጥል ፈጠርኩ፣
ያባት ልጅ ያዘው ቅምጥል'
የደሙ ትክል የወኔው ሽል፣
ፈጠርኩ ይበል ቀበዝባዛ፣ እንደእዙሪት እሚፈትል
በምላስ ቀስት አነጣጥሮ፣ ቂም በልቦና እሚተክል
ደም በደም እሚያስተጣጥብ፣ ወገን ከወገን እሚያክል
እንደሥራ-ሥር ደብተራ፣ ላንቃው መርዝ እሚያቀላቅል



ውጋቱ ዘር እሚያጣጥል
እንደጦስ እሚደበልል
እንደዛር ውላጅ አሽሮ
ያጥንት ሰባሪ አቅሮ
እንደበቱ እንደወስፈንጥር፣ ሾሎ ባስተናግር ቅጠል
አፈ-ጊንጥ ያብሾ ጡት ልጅ፣ ጥላ ወጊ ቀትረ-ፍልፈል
አሰሳልሶ እንደወላፈን፣ አሽልቦ ሲንበለበል
በከንፈር ፈግታ ከንፎ፣ ባፉ ጥላ-ወግቶ እሚገል፣
ደም-መራሽ ልጅ፣ ያፋፍ ላይ ድጥ፣ መስክ መሳይ ያሽሙር ደለል
የወሬ ማንፈሻ ጋሻ፣ ደርሼለት እሱን መሰል
በተከለው እሚከተል....
አባቴስ ወንድ ወለድኩ ይበል!"

'ለተማሩ' - ለማይምሩ አፈ-ሊቃውንት - (፲፱፻፷፩ - አዲሳባ)

# ሐ ረ ር

ሐረር፥ የግንብ-አጥር ማኅደር
ያባአደሬ ያባድር በር።
ድባብ ሦራ
ቀደምት የከተሞች አባወራ።
አምባ ዙሪያ-ክብ መንደር
ከሸዋ በር ፋልአና በር፥
ሐረር ጀጐል የሁሉ ዕድር
በአትክልት ሆነ በጫት እግር
የጥጋብ የሲሳይ ምድር፥
ከዱክ በር እስከቡዳ በር፥ በአምስት ደጅ የምታጋፍር
ተትረፍርፋ ስትመግብ፥ ቀኗን ከአታክልቷ ቅጥር
ሌቷን በጨረቃ ችቦ፥ ጥላ ለአያ-ጅቦ ግብር።
ሐረር፥ ሸንጐሽ ሁሉን አቀፍ
በበተስኪያን በመስጊድ ሠልፍ
በጂጂጋ ኮረብቶች ዘርፍ
በአጥሮችሽ ቅስቶች መርገፍ
በነራምቦው ብዕር ንድፍ
በሸንኬ ወሸባ እቅፍ
የተንቈጠቈጥሽ መንደር
ሐረር፥ የግንብ አጥር ማኅደር



ያባአደሬ ያባድር በር።
ድባብ ሦራ
ቀደምት የከተሞች አባወራ።

ለከበበው አሻግሬ - (፲፱፻፷፭ - ሐረር)

# እውነት አሁን አንቺ እሷ ነሽ!

እሷ ነኝ በዪኝ ግድ የለም!....
ሁሉ ላፍ አልተፈጠረም
ቢሉም አፍ አይለው የለም።
ልወቀውና ላውጣ እርሜን፣
የስንት ዘመን ረሃቤን
ልጋረጠው በዓይንሽ ዓይኔን።
ልጅነቴን የዳኸኩበት፣ የስንት ዘመን ፈለጌ
በናፍቆት ቋት ተሰግስጌ
በጣር በምጥ አደግድጌ
በእግረ ሕሊና ጠርጌ
በትዝታ በዳሰሳ፣ በፈለግሽ የናዳ ዳር
ስዋትት ስማስን በጣር
ዛሬ ያገኘሁሽ ባሣር
በስንት ዘመን የዕድሜ ምጥ
እውነት አንቺ እሷ ነሽ እርግጥ?!
መምሰልማ ትመስያለሽ
ማከልማ ታክያለሽ
የደም ግባቷን ተላብሰሽ
መጠሪያዋን ተሰይመሽ....
ያቺን የኔን....ያቺን የኔን



የኔን የመጀመሪያዬን
የጥንቴን የልጅነቴን
የስንት ዘመን ሕመሜን
የሕልም ዓለም ስመመኔን
የት አረግሻት? የት ደበቅሻት?
ዋጥሻት?....
አጥንቷን በአጥንትሽ ለብሰሽ
ወዟን በላቦትሽ ታጥነሽ
በልጅነቷ ልጅ ሆነሽ
ገጿን በግንባርሽ ነድፈሽ
አበቧን አደብዝዘሽ
መልኳን በመልክሽ አክስለሽ
ቡቃያዋን በዕድሜሽ ውጠሽ
በስም ብቻ እሷን ሆነሽ
ማነሽ? እውነት አንቺ ማነሽ
እኮ ንገሪኝ እሷ ነሽ?

ግድየለም ንገሪኝ ሐቁን
እርግጥ አንቺ እሷ ነሽ አሁን!
ንገሪኝና ላውጣ እርሜን

የሰንት ዘመን ረሃቤን
የጋረጠው ዓይንሽ ዓይኔን
እርግጡን ብቻ የሐቄን
የሰማይ የምድር እውነቱን
የቁርጡን የእርሙን የእቅጩን
በይ እሰቲ አንቺ እቧ ነሽ አሁን?!

፲፱፻፺፰ - አዳማ



## በራ፤ የመስቀል ደመራ

የአደይ ችቦ እየፋመ፥ እየጋመ
ኢዮሃ እያሰገመገመ እየተመመ
የመስቀል ደመራ
በራ።
በራ የአዲስ ዘመን ችቦ
በመስከረም ላብል አብቦ
ከዋከብቱን ፈነጠቀ
ርችቱን አንጸባረቀ
ተኳለ አዲስ ደመቀ
መስኩን በቀለም አዝርእት፥ በጥበብ አጥለቀለቀ
ሽለቆው ተንቆጠቆጠ፥ ተራራው አሸበረቀ
ኢዮሃ ኢዮሃ አበባዬ! ምድር ሕይወት አፈለቀ።
ነጋ፥ የአዲስ ዘመን ችቦ
ፈካ፥ ፀደይ አረብቦ
ሌሊቱ እንደጎሕ ቀደደ፥ ጨለማው እንደቀን ጠራ
እንደውቅያኖስ ዕፀዋት፥ እንደጠፈር ኮከብ ደራ
ምድር ሥጋጃ ለበሰ፥ የጌጥ አልባሳት ተቀባ
ሰማይ በእልልታ እስተጋባ
ኢዮሃ መስከረም ጠባ።
ነጋ፥ የአዲስ ዘመን ችቦ፥ ምድር ሕይወት አፈለቀች

የምሥራች አዝርእቷን፥ አዲስ ቡቃያ ወለደች
የአደይ አበባን ለገሠች
ለአዲስ ዘመን አዲስ ብርሃን፥ አዲስ መስከረም ገበየች።
ነጋ፥ የአዲስ ዘመን ችቦ
ፈካ፤ ፀደይ አረብቦ
በራ፥
የመስቀል ደመራ።

መስከረም - ፲፱፻፷፫ - መስቀል አደባባይ



# ጌ ራ

ጌራ ነበልባል ዘለላ
እንደመንጸባርቅ ጥላ
ሽልም ሽፋልሽ ሲያጠላ፤
ጌራ የፈተና መከር
የቁንጅና ራዕይ በር
እድብተሽ እንዳረሀ ደለል
በልብ እሳት ለመዋለል
ሰቀቀን እስኪዘነበል
ጣር ለጣር ለመቀላቀል
ድንገት ደርሰሽ ለመንጣለል፤
ጌራ የልጅነት ፍቅር
ድብቅ የዕድሜ ልክ ምሥጢር
አይሆንም እንጂ ቢሆንሽ
ነፍሳችን ይኳረፍ እባክሽ።
ጌራ የኪሩቤል እሳት
በኛ በሙታን ሕዋሳት
ተግ ሲል ያይንሽ እልባት
ልብ እያየ ልብን ሲያጧት
ማቀርቀር እንጂ መደፋት
በማን ልብ ቆመው ሊያይዋት!

በግልምጫ ስታመንን
አይታ ስታስደፋ ቀልብን
እንደመለኮት እንቅታ፣ ሳትበደል እምትከንን።
ማስጣር እንጂ እሷ ሳትጥር
ያየን እንደበላዔ-ሰብእ፣ እንጂ እንደ እሙ-ብርሃን ሳትምር
አትተውም ጌራ አትለቅም
መኩነን በቀር አታውቅም
እሙ-ብርሃን ትምሰል እንጂ፣ እንደ እሙ-ብርሃን አትምርም፣
እንኳንና ሰው ብኩን፣ መለኮት ወርዶ ቢያበራ
ከቶም አትለቅና ጌራ
እንዲያው እንደዘልማዱ፣ በእንቅልፍ ልብ እንጣራ
ነቅተን በቅዠት እናውራ።
በጥረት ጌራን ከታደግን
ከእርካንዋም ከቶ ከታገድን
ለብቻ የመከራመት፣ የዕድሜ ጥሻ ነው የለመድን።
እንደጮራ ድንገት ሰርቃ
በጥሻ ዋሻችን ጠልቃ
ወዲያው እንደመብረቅ መጥቃ
በቁም ስታቃዠን አውቃ፣
በቃን እንል ነበር ጣሯ፣ ይበቃን ነበር ብትተወን
ችላ መቻል ብታስችለን
የልብ ውጋት ሳትዋጋ



በሕልም ቤት ሳታናጋ።....
ብቻ ጌራ
ነችና የሕልም እንጀራ
የምትመጣ ሳትጠራ
ሂጅ ሳትባል የምትሄድ፣ የምትመነጠቅ በርራ
እኛስ ይብላኝልን ለኛ። መከራመቻችን ፈርሶ
ድንገት ከሙት-ዓለም ዋሻ፣ ገበናችን ተገርስሶ
እንገት እንኳ እምንደፋበት፣ መተፋፈሪያ እስክናጣ
እንደዘመናይ ባላንጣ
በማታምንበት እጋልጣ፤
የዕድሜ ወዛችን ፈሰሰ
ልጅነታችን ቀነሰ
አሰበርግጋ ብትነድፈን
አጋልጣ ብትሠወረን።
ተይ አንል አትሠወሪ
ስሚ አንል በሕልም ጥሪ
ወይ ፈጽመሽ አንል ቅሪ
"ነፍስ ሳይግል ነው እሚነድ?
ሞት ሳይሞቱት ነው እሚለመድ?"
ብላን ብቻ ብላን ትቅር
እንዲያው እንዲሁ እንደ ምሥጢር
እንዲያው እንዲሁ ሳትምረን

እንዲያው እንዲሁ ሳትተወን
እንቅልፋችንን ሳትቸረን
አንቅታ እንድትኲንነን።
ጌራ፥
ያረቀቀሽ የአምላክ ሥራ፤
ጌራ፥ የቁም ሕልም እንጀራ፤
ጌራ፥ የዲበ-ኵሉ ጡብ
የሕዋው ፈተና ክቡብ
የመስኮት ቅጣት ዕቁብ፤
ጌራ የሰቀቀን ጽዋ
"ዓይጥ በበላ ነው ዳዋ
እሚበራይ እሚሰዋ"
ብላን ብቻ ብላን ትቅር።
"ላይችል አይሰጥ" ብላን ሰውር።
የነፍስን ንዳድ ላትሞቃት
የልብን ዋይታ ላትሰማት
የብሌንን ምጥ ላታያት
ምን ላይተርፈን ምን ላይተርፋት
ብንወድም ወደድን እንልም?
ብንነድም ነደድን እንልም? ...
ምንም ሳንተነፍስ ኩርትም!?
ጌራ የውብ-ዓለም ብቁ



እስከዚህ ነው ኑሮ ጭንቁ
ጌራ ይህ ነው የዕድሜ ብሩቁ?
ምኞት ናዳ-ድጥ ነው ትጥቁ?
የዕድሜ ብኩን ጣር ነው ስንቁ?
ጌራ የሕልም-ዓለም ደለል
ትዝታሽ ሞልቶ ሲቆለል
ሲቃ ነው እሚኮለኮል።
ጌራ የእቶን-ፍም ዘለላ
ከገጽሽ የእሳት ከለላ
ሽልም ሽፋልሽ ሲያጠላ
እንደመንጸባርቅ ጥላ
ተግ አትበይ ባይንሽ እልባት
ልብ እያየ ልብን ቢያጧት
የእዝን ቋት ላይተካላት
ማቀርቀር እንጂ መደፋት።

ጌራ የመከራ መከር
የቁንጅና ራዕይ በር
ሕልም አይቻለሁ ልናገር።
አንቺ ስትሰቂ እኛ ስንበር
ስንቀርብሽ እየሸሸሽን፥ ሸሽተሽ በማታውቂው አገር
ስንርቅሽ ተግ እያልሽብን፥ ረግጠን ከማናውቀው ጠፈር

እንቺ ታጅበሽ ስትበሪ፥ የኛ ክንፍ ሲሰባበር
እንቺ እንድያሽን ስትርቂ፥ እኛ ስንወድቅ እኛ ስንቀር!
ፍቺልን ጌራ ፍቺልን፥ ሰው አይከርምም ሕልም ጉርሶ
በቅዠት ጠረንሽን ዳሰሶ
በሽውታ-ተስፋ ደርሶ
ቀን በቁሙ ካልጸለየ፥ ጌራ ያንቺን ኪራራይሶ?
ምነው ያንቺስ ሩካቤ አቅም
ከኛ እንጂ ወደእኛ አይዘልቅም?
ሲላመዱለት እይለምድም?
ሽቅብ ከራቀበት ወርዶ
እንደሰው ለሰው ተጠምዶ
በፍቅር እምላክ ተገዶ!
ፍቺልን ፍቺልን ጌራ
ቀልብ እንዲህ ለጣር ተድራ
ከሕልውናችን ሰብራ
ያለዕጣችን ተሰባጥራ
እንደሰሞነኛ ካህን፥ ነግ በእንቅልፉ ጣዕም ወድቆ
ያለሱባዔ በምኞት፥ በተስፋ እግሩ ብቻ ፀድቆ
ያልደረሰበትን ደርሶ፥ ያላወቀበትን አውቆ
በሰመመን መሰብ ብቻ፥ ከነፍሱ ረሃብ ተላቆ
በፍስሐ ተፍለቅልቆ
እንደአራስ ነፍስ ፈንድቆ



ከረፈደ ኋላ ከርሞ፥ ነፍሱን ሲቃ ከማስወረር
ከቶ ሳይነቃ እንደሚቀር
ዓይነቱ ነው የኛም መከር?
ፍቺልን ጌራ ፍቺልን፥ ቀን ታልሞ ሌት ታልሞ
ፍዳን ቃትቶ አጣጥሞ
አይተረጉሙት ሕልም ነን፥ የሚደበቅ ተረምርሞ
እንደሰሞነኛው ካህን፥ ከንጋት ቅዠት ጋር ወድሞ?
በተስፋ እንደተዘረጋ
ለመከራው ከሚያነጋ
የማይነቃ የሚረጋ
ዓይነት ነው ጌራ ፍቺልን? ማግረሺን በሕልም ጉጆ
ጌራ ብርሃን ጌራ ቆንጆ
ለተስፋችን ዕዳ ሆንነው?
'እኛ ለኛ እንኾነው እልነው?'
ሌት በቅዠት ተሰትረን
ቀኑን በስቀቀን ታንቀን
ዕድሜአችን በምኞት ታጥራ
ፍቅር እንደዜ ነው እሚገል፥ እኛ ስንቴ እንሙት ጌራ?
ውላችን በውሉ ላይኖር
ተነጣጥለን ለመባከን፥ ለመንከራተት ለመዞር
ተጣምረን ላንከራረም
ተቈራኝተን ላንታደም

ላይነጋልን ላናጨልም
ላንዳበል ላናገግም
መባከን ከሆነ ፍቺው፣ ብኩን ከብኩን እይሠምርም?!
ጌራ የስቃይ ስያሜ
ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ዕድሜ
'ተስፋ' ብንል ብለሽ 'እርሜ'
የተንከራተተውን ሕልም
የተቅጠለጠለውን ቅስም
ስናታክት ስናደክም፣
ብራቅ ዳዕሩን ተርክኮት፣ እንደማይነድ ያድባር ዋርካ
በቁም ሞተን ስናወካ
ፈተናሽ ታልፎ ላይበቃ
በቅዠት ላናመረቃ።
ጌራ ብኩን ጌራ ብካይ
ጌራ ከንቱ ጣር አሰልላይ
ጌራ የሕልም ዓለም ሰቃይ፤
ጌራ ሰቀቀን መከራ
በቅዠት ከምንጣራ
አይሆንም እንጂ ቢሆንሽ
ነፍሳችን ይኳረፍ እባክሽ።
በቁም ቅዠት እንወያይ
በምኞት ጣር እንተያይ
ይብቃን ደህና ዋይ፣ ደህና ዋይ።



ጌራ ነበልባል ዘለላ
እንደመንጸባርቅ ጥላ
ሽልም ሽፋልሽ ሲያጠላ።
ጌራ የፈተና መከር
የቁንጅና ራዕይ በር
እድብተሽ እንደአረሀ ደለል
በልብ እሳት ለመዋለል
ሰቀቀን እንዲዘነበል
ጣር-ሰጣር ለመቀላቀል
ድንገት ደርሰሽ ለመንጣሰል፣
በለዘብታ ለማመነን
እንደመለኮት አንቅተሽ፣ ሳትበደይ ለመኰነን።
ጌራ-ሽልም ጌራ-ስውር
ገጸ-ረቂቅ ልበ-ነብር
እመ-ብርሃን መሰል ጌራ፤ እንደ እመ-ብርሃን እማትምር
ሽሽግ የዕድሜ ልክ ምሥጢር
ጌራ የልጅነት ፍቅር....
አይሆንም እንጂ ቢሆንሽ
ነፍሳችን ይኳረፍ እባክሽ።

፲፱፻፹፩ - ፓሪስ

## ማይጨው

የማን እንደበት ነው ማይጨው
ያንቺን ሲአል የሚነግረው?
በማን የብዕር ቃል-ደም ነው
ታሪክሽ የሚነደፈው?
ማይጨው እግዚኦ ላንቺ ቆሌ
አገር ውሀ-ገባ-አሞሌ
የሆነብሽ የእሳት ምፅዓት
በነጭ አረመኔ መዓት
የመድኃኔ ዓለም ቀን ቅጣት፣
እንዲህ ነበር ብዬ ላልጥር
ያንቺን መቅሰፍት ያንቺን ዕድር
ላይጽፈው የሟች ሰው ብዕር፤
ያንቺን የአርባ ዓመት ቂም በቀል
ያንቺን ዕብሪት ያንቺን በደል
አስቀድሞ እንደተባለው
"እግዚአብሔርና ታሪክ" ነው
ፍላፃሽን የሚጽፈው
ፍርድሽን የሚቋቋመው፥....
ያገር ጐበዛዝ ያገር ወንድ
በነጭ አረመኔ ሞገድ፥



ያገር ሕፃን ያገር ወላድ
በእቶን የመርዝ እሳት ንዳድ፥
እንደፍካሬ ኢየሱስ ቃል
በፋሽስት ሲአል ሲጣል፥....
ማይጨው እግዚኦ ላንቺ ቆሌ
አገር ውሀ-ገባ-አሞሌ
የሆነብሽ የእሳት ምፅዓት
የነጭ አረመኔ መዓት
በሟች ብዕር ላይቀመር
የመቅሰፍትሽ ሲአል ድንበር
"በእግዚአብሔር-በታሪክ" በቀር
በቁም ሮሮ ላይሠፈር
ላይመጠን ላይነገር።
በማን እንደበት ነው ማይጨው
በማን የብዕር-ቃል-ደም ነው
ሲአልሽ የሚነደፈው?

፲፱፻፺፰ - ማይጨው

# ድሬ-ዳዋ

ዲሬ-ዳዎ ድሬ-ዳዋ
የምሥራቅ አድባር ጥላዋ
ላገር ጕሣ ድምር ጽዋ
ኅብረ-ጠባይ ማጥለያዋ፤
ድሬ-ዳዋ ውስጠ-ደማቅ
ሽፍንፍን እንደአባድር ጨርቅ፥ ብልጭልጭ እንደሩቅ ምሥራቅ
ያውራ ጕዳናሽ ዛፍ ጥላ፥ ጋርዶሽ ከንዳድሽ ብራቅ፥
ድሬ-ዳዋ ዲሬ-ዳዎ፥ የማእጠንትሽ ወዝ ብርጉዱ
ውል-ውል ሲል በቀትር፥ ከላጋር በር ማልካ ጃብዱ
ከጋንዳ ቆሬ ካዚራ
ከአፋታ-ኢሳ ቃፌራ
ከማጋላ ጋንዳ-ጋራ፤
በረድ ሲል ጥላሽ ሲወርድ፥ ቆሌሽ ቀይሮ ሲወጣ
በሽርጥ በሻሽ በቁምጣ
በመለዮ በባርኔጣ
በየጉድባሽ ጫት ሲለጣ፥
ጣይ ያደከመው ወፈፌሽ፥ 'አራራ' ጥሎት ሲንጣጣ፥
ብሌኑ እንደኅሽ-ግት ደምቆ
በንዳድሽ ግለት ሞቆ
ጉድ ከየእንደበቱ ፈልቆ



ሰንቱ ቋንቋ ተድብለቅልቆ፥
ከትምባሆሽ ሡረት ጨምቆ
ጫት ከአብሾሽ ወዝ ተማጥቆ
ድሬ ምድረ-ላቦት ዘፍቆ፤
ድሬ-ዳዋ ቁሉቢ በር
የሰንቱ ዘር የእኩል እገር
ዲሬ-ዳዎ ድሬ-ዳዋ
የምሥራቅ አድባር ጥላዋ
ላገር ጕሣ ድምር ጽዋ
ኅብረ-ጠባይ ማጥለያዋ።

፲፱፻፷፭ - ድሬ-ዳዋ

# ተወኝ

ላታስታምም አትመመኝ
ላትወስደኝ አታንጠልጥለኝ
ይቅር፣ አንጀቴን ቁረጠኝ
ጋሽዬ፣ አልወድሽም በለኝ።
እጅ እጅ አልበል አታባክነኝ
ባክህ፣ ወንድ ነው ቆራጡ፣ እንትፍ-እርግፍ አርገህ ተወኝ።
አየህ፣ እንዳንተ አባት አለኝ
ሴት በወለድኩ ተዋረድኩ፣ ረከስኩ ቀለልኩ እሚለኝ፣
እኔም እንዳንተ እህት አለኝ
ሥጋሽን ሳይሆን ልብሽን፣ ከፍተሽ ጥለሽ ነው እምትለኝ
እና ተወኝ፣ ባክህ ተወኝ፤
እንዳንተ እኔም አለኝ እናት
የሴት ቁንጮ እምመስላት
ጎረቤት ፊት እምታፍር፣ እንዲህ ሆነችልሽ ሲሏት!....
እና፣ እልሆንሽም በለኝ
ባክህ እንጀቴን ቁረጠኝ....
ፍቅር እንደሁ የኔ ይበቃል፣ ላንተም ለኔም እኔው ልውደድ
ከዘመድ ግንባር ደብቄ፣ እኔ የብቻዬን ልንደድ፣
ብቻ፣ ከወጥመድህ ለየኝ
አልችልህም፣ ንቀህ ማረኝ



ካንተም ከስሜም ከቤቴም፣ ያጣሁ ብኩን አታድርገኝ፣
ባክህ፣ አንጀቴን ቁረጠኝ
ተወኝ፣ ተወኝ፣ ተወኝ።

፲፱፻፺፯ - ኒው-ዮርክ

# ድንቅም አደል?

እስቲ ሰው ሞልቶ ባገሩ....
ተትረፍርፎ በየበሩ....
እያንዳንዱ በየግሉ
እንደዘበናይ ዕድሉ
ተገንጥሎ ለበኩሉ
ለየፊናው ለየቅሉ
ከነፍስ ወከፍ መደበሩ
አንድ ራሱን መሰወሩ
ለብቻው መነጋገሩ
ከጥላው መመካከሩ
በነፍስ ወከፍ መደበሩ
ከሕልሙ መመሳከሩ፤....

ብቸኝነት ውጦት ሁሉ
ለፍሬም ባይሆን ለቃሉ
የተሰፋን ችቦ መሳሉ፥
ለውኑም ባይሆን ላመሉ
እንደዘበናይ ዕድሉ
በምኞት ሉስ መዋለሉ፤
"ከዘመድ ከወዳጅ ጠለል"
ከስንቱ 'መዓት' መካከል



ለየብቻው በመገንጠል
በሕልም ዓለም ለመንጠልጠል
ተደባብቆ ሲብሰለሰል
ጉድም አደል? ድንቅም አደል?....

'ለብቸኞች' - ፲፱፻፺፱ -አዲሳባ

# አብረን ዝም እንበል

ከሰው መንጋ እንገንጠል
ለአንድ እፍታ እንኳ እንገለል
በእፎይታ ጥላ እንጠለል
ዝም ብለን አብረን ዝም እንበል።
ምነው እዋሽ ማዶ ቆቃ፣ እሸለቆው ግርጌ ሸሽተን
የቆቃን ለቆቃ ሰምተን
ሲቃውን ሲሰብቀው አይተን
ሰቀቀኑን ተወያይተን
የምሽት ጀምበር ቢውጠን?....
ወሀ እንደዱታ ሲተምም፣ በድን ሸለቆ ሲናገር
በሰማይ ፈረስ ተጭኖ፣ ከእፅናፍ አፅናፍ ሲንደረደር
ሲያጉተመትም ሲያስገመግም፣ በዓይነ-ሕሊና ለመመሰከር
ሳንጨነቅ ሳንገደር
ለማንም ምንም ሳናዋይ፣ ሳንናገር ሳንጋገር
ከዓይንሽ ከልብሽ ከልቤ፣ አዋሽ ማዶ አብረን እንብረር።

አዋሽ ማዶ እብረን እንውረድ
አጉል ነው ብለንም ሳንፈርድ
ድንቅም ነው ሳንል ሳንወድ
ዝም ብለን አብረን ብንወርድ....



ከሰው መንጋ ተለይተን
ከጠረኑ ተነጥለን
ከጉምጉምታው ተገንጥለን
ከኳኳታው ብንከለል....
ከላንቃው ከድምፁ ሸሽተን፣ በእፎይታ ጥላ እንጠለል
በቆይታ፣ በፀጥታ፣ ዝም ብለን አብረን.... ዝም እንበል።....
መቸስ አይሆንም ካልሽ .... ቅሪ
ግድየለም አትገደሪ
ልቦናሽ በመተረልሽ፣ ባላደረብሽ እደሪ፤
ተስፋ መቀነት ነው መቸም
የሰው ልብ አይችለው የለም ....
ብቻ ዳግመኛ ሞት ሳንሞት፣ አዲስ ቀን ሳይጨልምብን
ድፍን ደመና ሳይቋጥር፣ ክረምት ውርጅት ሳይወርድብን
ኮከባችንን ሳንጠራ፣ ሳንቆጥርባት ሳትቆጥርብን
ሞራችንን ሳናስነብብ፤ ሳናሳያት ሳታይብን
ጨረቃን መስክሪ ሳንል፣ ሳናውቅባት ሳታውቅብን
እዋሽ ማዶ ቆቃ በርረን፣ ባክሽ ጀምበር ትጥለቅብን።....
ወሀ እንደዱታ ሲተምም፣ በድን ሸለቆ ሲናገር
በሰማይ ፈረስ ተጭኖ፣ ከአፅናፍ አፅናፍ ሲንደረደር
ሲያጉተመትም ሲያስገመግም፣ በዓይነ-ሕሊና ለመመስከር

ሳንጨነቅ ሳንገደር
ለማንም ምንም ሳናዋይ፥ ሳንናገር ሳንጋገር
ከዓይንሽ ከልብሽ ከልቤ፥ አዋሽ ማዶ አብረን እንብረር።
ከሰው ኳኳታ እንነጠል
ለአንድ አፍታ እንኳ እንገለል
በእፎይታ ጥላ እንጠለል
ዝም ብለን አብረን ዝም እንበል።

፲፱፻፸፭ - ቆቃ



# አ ሥ መ ራ

ምነው ሁሉ እንዳንቺ አሥመራ
እንደከተሞች መዲና፣ አቀያየሱ ቢጠራ፤
ያውራ ጐዳናሽ ጠለላ፣ ሁሉን በአክናፉ እየጠራ
አሥር ሰዓት ላይ ሲደራ
ለመንገደኛሽ መዝናኛ፣ ሲያጠላ ሲያብብ ሲያፈራ፤
ምነው ሁሉ እንዳንቺ አሥመራ
አደባባይ ሲያነጥፉ
አድባራትና መስጊዱን፥ ካቴድራሉን በየረድፉ
ገበያውን በየመልኩ፥ እንዳውታር እያሰለፉ
በወግ እየደረደሩ
በሥምረት እያሠመሩ
በውበት እያዳበሩ
እያሳመሩ ቢያደሩ፤
በየክፍሉ በየበሩ፥ በየመልኩ በየተራ
ፋናሱን እንደደመራ
ቡና ቤቱን እንደሥራ
ምነው ሁሉ እንዳንቺ አሥመራ
እንደከተሞች መዲና፥ አቀያየሱ ቢጠራ።

፲፱፻፸፰ - አሥመራ

# ወንድ ብቻውን ነው እሚያለቅስ

ከመዳጅ ከዘመድ ርቆ
አንጀቱን በአንጀቱ ታጥቆ
ተሸሽጐ ተገልሎ፣ ተሸማቆ ተሸምቆ
ከቤቱ-ሰው ተደብቆ
መሽቶ፣ የማታ ማታ ነው፣ ሌት ነው የወንድ ልጅ እንባው
ብቻውን ነው የሚፈታው።....
ብቻውን ነው የሚረታው።....
ችሎ፣ ውጦ፣ ተጨብጦ፣ ተማምጦ ተጣጥሮ
በሲቃ ገት ተወጥሮ
እንደደመና ተቋጥሮ
እውስጥ አንጀቱ ተቀብሮ ....
መሽቶ፣ ረፍዶ፣ ጀምበር ጠልቆ
የጨለማ ድባብ ወድቆ
በእንቅልፍ ጥላ ሲከበብ፣ በዝምታ ሲዋጥ አገር
ፍጡር ሁሉ ተሰለምልሞ፣ ብቸኝነት ብቻ ሲቀር....
የጓዳ የጓዳ፣ ማታ
ምድር አገሩ በእፎይታ
ዓይኑን በእንቅልፍ ሲያስፈታ
ሁሉ በእረፍት ዓለም ርቆ፣ ብቸኝነት ብቻ ሲቀርብ
ያኔ ነው ወንድ ዓይኑ የሚረጥብ
የብቻ፣ እንባ ወዙ እሚነጥብ።



ብቻውን ነው፣ ብቻውን ነው ....
የእንባ ጭለማ ለብሶ ነው
ወንድ ልጅ ወዙ እሚነጥበው።

ዕጣውን ለብቻው ቆርሶ
ብቻውን ሰቀቀን ጉርሶ
ብቻውን ጭለማ ለብሶ
ገበናውን ሣግ ሸፍኖ
ኩብሩን በሰቆቃ አፍኖ
ሌሊት፣ የማታ ማታ ነው
ሕቅ እንቁን እሚነጥበው
ኢሎሄውን እሚረግፈው ....
ከዓይኑ ብሌን ጫር ተመጦ
ከአንጀቱ ሲቃ ተቆርጦ
ደም አልሞ ፍም አምጦ
ከአፅመ-ወዙ እቶን ተፈልጦ
እንደጠፈር-ብሩቅ እምብርት
እንደእሳተ ገሞራ ግት
ሩቅ ነው ወንድ ልጅ እንባው
ደም ነው፣ ፍም ነው እሚያነባው!

ንጥረ ሕዋስ ነው ሰቆቃው
ረቂቅ ነው ምሥጢር ነው ጣሩ፥ ... ብቻውን ነው የሚፈታው፥
ብቻውን ነው የሚረታው።

ችሎ፥ ውጦ፥ ተጨብጦ፥ ሰቀቀኑን በሆዱ አጥሮ
በአንጀቱ ገበና ቀብሮ
ውሎ ጭጭ እፍን ብሎ፥ እንደደመና ተቋጥሮ
ጣሩን ውጦ ተጣጥሮ
በሲቃ ግት ተሰትሮ፥....
ከወዳጅ ከዘመድ ርቆ
ከቤተ-ሰው ተደብቆ
አንጀቱን በአንጀቱ ታጥቆ፥
ተሸሸጎ ተከናንቦ፥ ተሸግቶ ተሸምቆ....
የብቻ ብቸኝነቱ፥ የጭለማ ልብሱ እስኪደርስ
በዓይን እጥፉ ሃሞቱ እንዳይረከስ
ቅስሙ በገበያ እንዳይፈስ
ተገልሎ በእኩለ-ሌት፥ ወንድ ብቻውን ነው እሚያለቅሰው።

ለዘውዱ ሽዋዋልቶት - (፲፱፻፺፩ - አምቦ - ከልሌ)



# ት ዝ ታ

ዓይንህን በዓይኔ ፀንሼ፥ የቀስቱን ጮራ እንደቋጠርኩ
ሌሊት በሕልሜ አማምጬህ፥ ሕመምህን እየፈጠርኩ
ቀን ጥላህን እንደለበስኩ
የፍቅራችንን ነበልባል፥ በቁም ሰመመን እንዳቀፍኩ
ልብ ውስጥ እንዳዜሙት ሙሾ፥ የሲቃ ስልት እንዳቃጨልኩ
የነፍሴን የእሳት ዘለላ፥ ጉዳናህ ላይ እንዳነጠብኩ
እንደገደል ዳር ቄጠማ፥ የሥጋት እንባ እንደቃተትኩ
ሕይወቴን ላንተ እንዳሸለብኩ
ሕልምህን በጄ እንደዳሰስኩ
ያን የመጀመሪያ ሞቴን፥ በመሸ ቁጥር እንደሞትኩ
እስሁ፥ እንደብኩን መረብ፥ ትዝታህን እንዳጠመድኩ።

፲፱፻፺፱ - ጋርባ - ጉራቻ

# አዘቦን ዳግም አየኋት

**ዓይን ማየት ነውና እሚያቅ**

የብርሃን ዕድሜ አዚሙ እስኪያልቅ ....

ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ፥ ዳግም አዘቦን አየኋት

ዙሪያ ቅጽሯን አስተዋልኳት

አጠናኋት፥ አዳመጥኳት ....

ገርሮ ማዳመጥ ነው ከፍሉ

ተቀባይ ሕዋሱ እስካሉ ....

እና አዘቦን ሰማኋት

ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ፥ ተመልሼ አዳመጥኳት

እና ዛሬስ፥ እንኳን አልኳት ....

ያኔ ድምጿ ከሩቅ ነበር፥ እንደሟች ሳል ሲል የሚሰው

የልሳን ሲቃ ጥላ ነው

የከፉ ቀን የቅዠት ጣር፥ ብኹ እልሙ ነው እሚታየው

ያደባባይዋም ላይ ጭጋግ፥ የጥንብ አንሳ አክናፍ ብቻ ነው።

መሬቷ እንደዋረደ ስለት፥ ጥርሷ ሲፋጭ እንደ ደወል

ሰቆቃ እንጂ አኮ ድምፅ አደል!

ያዋራው ጥላ እንደጉም፥ ከጣራ በላይ ሲቃጨል

ሰው እንደ አይጥ በየጥሻው፥ ሲጥ ሲል እንደ ግንደ በል

ሰቆቃ እንጂ አኮ ድምፅ አደል። ....

ዛሬ ግን ጤና ይታያል



ሕፃናቱም ይቦርቃል

ከብቱም እንደልብ ይግጣል

ሰውም ያወጋል ይስቃል

"ዝ ኾነ ኾይኑ" እንኳን ይላል፤

ከየምድጃው ዳር እሳት፥ ከየጣራው ጢስ ይናኛል። ....

ዓይን ማየት ነውና እሚያቅ

የብርሃን ዕድሜ አዚሙ እስኪያልቅ

ዳግም አዘቦን አየኋት

ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ፥ ተመልሼ አስተዋልኳት

እና ዛሬስ እሰይ አልኳት።

፲፱፻፰፫ - መቀሌ

# እንዳይነግርህ እንዳች እውነት!

ደንስ ጉበዝ!  ደንስ ጀግና
ክራቫትክን አውልቅና
ሃሳብክን ልቀቀውና
ኮትክን ሸሚዝክን ጣልና
ርገጥ፣ ጨፍር፣ ደንስ ጀግና!

ያን የሙዚቃህን ናዳ፣ የኮንትራባሱን መብረቅ
ልቀቀውና ይድብለቅለቅ
ምድር በሆይታ ይጥለቅለቅ!
ምንም-ምንም እንዳታስብ፣ ሁሉን-ሁሉን እንድትረሳ
ደንስ! ካካታው ይነሳ
ጨፍር፣ ወለሉ እስኪበሳ ....

ሃይ-ሃይ! ዋይ! ሃይ-ሃይ! በልበት
የጃዝ ፋንፋር አንኳኳበት
ራስክን እንዳታስብበት
ሆ! በል እሪ! በል ምታበት
ፎክርበት፣ አቅራራበት
አናፋበት፣ ሸልልበት
የሲቃ ሳቅ እስካካበት
ሆያ-ሆዬ! በል ጨኸበት



ኡኡታህ መንኮራኩርክን፣ እስኪያስጥመው አንራበት
ጭንቅላትክን ግዘፍበት፣ ውቀጥበት፣ ውገርበት፣....
ዝግ ብሎማ ያስበ እንደሁ፣ ይነግርሃል እንዳች እውነት!

፲፱፻፹፫ - አዲሳባ

# የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ

ተስፋ ባጣ ምድሬ በዳ
ያንድ እውነት ይሆናል ዕዳ፤
እና ትንፋሼ አልሆነሽም፥ ሆኜብሽ መራር መካሪ
"ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ፤"
እውነት ላንቺ መች ተስፋ ናት፥ ጉስቁል ልሳንሽን ነክሳሽ
ክንድሽን ካዘለ ቅርስሽ፥ መጠላለፍ ሲሆን እጣሽ
ከእንግሊዝ የሞት አማልክት፥ መተናነቅ ሲሆን ድርሻሽ
መልመጥመጡ፤ መሽቆጥቆጡ፥ መስሎሽ ድንጉት የሚያዋጣሽ
የኔ እውነት ሆነብሽ ዕዳሽ። ....
ወራሪም ፈጣሪን ላያቅ
የጣለውን በስኳል እንጂ፥ ወድቋል ብሎ ግፋ ላያልቅ
መች ትተርፊያለሽ ኢትዮጵያ፥ ሕዋስሽ እብሮኝ ካልሠራ
አንገትሽ ብቻ መቅደላ፥ አፋፍ ወጥታ ብታበራ
የቀረው ሠራ-አከላትሽ፥ በየጥሻው ተዘርሮ
ከአባት በወረስሽው ንፍገት፥ ነብዞ ደንዝዞ ተቀብሮ
ባጉል ወጌሻ ታጅሎ
እጅና እግርሽ ታሽቶ ዝሎ
እኔን ለጥንብ አንሳ ጥሎ፤
ከደቀቀ ከደከመ፥ ክንድሽ አልነሣ ካለ
ሞት እንጂ ለኔስ ምን አለ? ....



ሆኖም ጉስቋላ አልምስልሽ፥ የሚያዝንልኝ አልፈልግም
ጠላትሽን በክንድሽ እንጂ፥ በእንባሽ ወዝ ባላሸንፍም
የልቤን ፍቅር በስተቀር፥ እማወርስሽም ውል የለኝ
የኮሶ ሻጭ ልጅ ደሃ ነኝ። ....
ደሞም ያላንቺ የለኝና
ድሌም የተስፋ ጉሕ ባይሆን፥ ከሞት ጋር ትግል ነውና
ከዚህ ሌላ ትእዝብት ውረሽ፥ ሳይነጋ እንዳስመሸሽብኝ
ጊዜና ትውልድ ይፍረደን፥ ሳልነቃ እንዳስረፈድሽብኝ።
ያም ሆኖ ለራስሽ እንጂ፥ ለኔ ከቶም አታልቅሺ
አንቺ ነሽ እንባ እምትሺ፤ ....
የእምነትሽ መተሣሰሪያ፤ ውልሽ ለተላቀቀብሽ
ላንቺ ነው እንባ እሚያስፈልግሽ።
እምነ፥ይኸን እወቁልኝ፥ ምስክር ሁኑኝ ስማዕታት
ለሷ ነው እንባ እሚያስፈልጋት።
ከጠላቶቼ ጭብጥ ውስጥ፥ ትንፋሼን በጄ ስነጥቃት
ሞቴን ከመንጋጋቸው ውስጥ፥ መንጭቄ እኔው ስሞታት
ላገሬ ብድር ልከፍላት
የነፈገቺኝን ፍቅር፥ በራሴ ሞት ልሰግሳት
ዳግም ከሞቴ ባንኜ፥ በመንፈስ ጣር ስሞግታት!....
ያኔ ነው እንባዋ የሚያጥራት።

ስለዚህ ለራስሽ እንጂ፣ ልቅሶሽ ለኔ ምን ሊረባ
ብቸኛ ምሬት ነው ኃይሉ፣ ወኔ መሰሰቢያው ነው እንባ።
እና ለራስሽ እዘኚ
እንጂ ከቶ ለኔ አትባክኚ። ....
ይልቅስ ተረት ልንገርሽ፣ የተላከ ከእንግሊዝ ዘንድ
እጅህን ስጥ አለኝ ፈረንጅ፣ እጅ ተይዞ ሊወሰድ፣
ምን እጅ አለው የእሳት ሰደድ?
አያውቅም ከንዱ እንደሚያነድ። ....
ዳዊት እንዲያ በበገናው፣ ማልቀስ ማላዘን መያዙ
ይኸ የጐልያድ ውላጅ፣ ቢበዛበት ነው መዘዙ
ምንጩ እንደአሸን እየፈላ፣ አገሩን ምድሩን ማንቀዙ
ቸግሮት ነው፣ መጋፈጡ፣ ከስንቱ መወናጨፉ
በባላንጣው ሳቢያ ምክንያት፣ የራሱን ወገን ማርገፉ። ....
ታድያ እንግዲህ አንቺ ኢትዮጵያ፣ እኛስ ልጆችሽ ምንድነን
አመንኩሽ ማለት የማንችል፣ ፍቅራችን የሚያስነውረን
ዕዳችን የሚያስፎክረን
ግፋችን የሚያስከብረን
ቅንነት የሚያሳፍረን፣ ቂማችን የሚያስደስተን
ኧረ ምንድነን? ምንድነን?
እሜከላ እሚያብብብን
ፍግ እሚስመልምብን፣



ከአረም ጋር ያፈራን ጊንጦች፣ ከእንክርዳድ ያልተለየን ዘር
ግርዱ ከምርቱ ተማጥቆ፣ ከቶ ያልተበራየን መከር
ምንድነን? ምንድነን እኮ?
አረጋዊውን ባንቀልባ፣ ከምንሸከም እንኮኮ
ጐልማሳውን ከወኔ ጣር፣ ካልፈታን ከፍርሃት ምርኮ
እንደወዶ ገባ ወደል፣ መጠለሉን ከሴት ታኮ ....
ካቃተን፣ ምንድነን እኮ? ...
አየሽ አንቺ እማማ ኢትዮጵያ፣ አየሽ አንቺ እናት ዓለም
ቃል የእምነት ዕዳ ነው እንጂ፣ ያባት የናት እኮ አደለም። ....

ያም ይቅርና መርዶ ላርዳሽ፣ ሰሚው እኔ እንደሰማሁት
እርም በልተሽ ከምትቀሪ፣ ስሚ፣ ገብርዬንም ማሉት። ....
እስቲ እንግዲህ በይ ፍረጂኝ፣ ከእንግዲህ እኔ ፍሬ አላይም?
"ዘርቶ መቃም ወልዶ መሳም"
አባባል ለኔ አይባልም?
እስቲ ገብርዬን መሰል ዘር፣ ፍሬው ከቶ አይለመልምም?
እኔስ ዘር ዘራሁ አልልም? ....
ምነው ፍንጭትክን ገብርዬ፣ ያን ፍንጭትክን አጨለሙት
እንደሬት ልግ አክሰሉት
እንደኮሶ አስመረሩት?
ከጡቶችሽ አትፍ ነጥቀው፣ ከማገዶንሽ ፍትር ቆርጠው
እውነትን ሲገሉ እንዲህ ነው፣ ፊገግታውን አጨልመው። ....

እስቲ እባክህን ንገርኝ፣ የዛሬን እንኳ ስቀህ ሙት
በዕድል ጥቀርሻ እንደለጀሉት
እንደወላድ ማሙንት ጡት
እርግማ ጉሳ እንደቀለሙት
ፈገግታህን እያጥቁሩት።
እምቢ በላቸው ንገርኝ፣ በእባት ሜራ እንዳስገዙሉት
በሙሃ እንዳሳገዱት
የንፍስህን ጮራ ብርሃን፣ ከገጽህ እንደቀበሩት
ዘለዓለም ላያወጡለሙት
ወንድምዬ እምቢ በላቸው፣ የዛሬን እንኳ ስቀህ ሙት። ....
ያለፈ ጥሬታችንን፣ ሳስታምመው ትዝ ሲለኝ
ከምከርነው ነገር ይልቅ፣ ያልምከርነው ነው እሚቆጨኝ።
እና በኔ ይሁንብህ፣ መሞህ፣ ስቀህ ተቀበለኝ
እኔም ላጥይህ እድምጠኝ ....
እጅህን ስጥ እለኝ ፈረንጅ፣ እጅ ተይዞ ሊወስድ
ምን እጅ አለው የእሳት ሰደድ?
እያውቅም ከንዴ እንደሚያንድ። ....

ለጓለማየሁ ቴዎድሮስ - (፲፱፻፶፮ - ደሴ)